የአምባጓሮ ውጤት
ገጽ 11

አብዝቶ ማሰብና መጨነቅን ማቆም
ገጽ 14

በፕላን የሚመሩና የማይፈርሱ ከተሞችን ለመገንባት
ገጽ 21

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
84ኛ ዓመት ቁጥር 088 ኅዳር 28 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# በአምስቱ አውሮፕላኖች አንበጣን፣ ግሪሳንና ተባዮችን ለመከላከል ትልቅ አቅም ፈጥረዋል


ፎቶ ሀዲስ አብርሃ
ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)

አስቴር ኤልያስ

አዲስ አበባ፡- የግብርና ሚኒስቴር የገዛቸው አምስት አውሮፕላኖች የአንበጣ መንጋን፣ የግሪሳ ወፍንና ድንበር ዘለል የሆኑ ተባዮች በሰብል ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ከመከላከል አኳያ ትልቅ አቅም ፈጥረዋል ሲሉ የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) አስታወቁ፡፡

ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) በተለይ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ ሚኒስቴሩ ቀደም ሲል የገዛቸው አምስት አውሮፕላኖች ትልቅ ኢንቨስትመንት ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ አውሮፕላኖቹ የጸረ ተባይ ኬሚካል ርጭት በማካሔድ የሰብል ምርቱን ከአንበጣ መንጋ እና ከግሪሳ ወፍ በመከላከል ረገድ ድርሻቸው የጎላ ነው፡፡ በተለይም ድንበር ዘለል የሆኑ ተባዮችን ለመከላከል የሚያስችል አቅም በመፍጠር በኩል ከፍተኛ ሚናቸውን እየተወጡ ነው፡፡

ሚኒስትሩ ግርማ (ዶ/ር)፤ በአንድ ወቅት በጣም በከፍተኛ ሁኔታ ኢትዮጵያን የአንበጣ መንጋ አጋጥሟት እንደነበር አውስተው፤ በወቅቱ የአንበጣውን መንጋ ለመከላከል የሚያስችል ጸረ ተባይ ኬሚካል የሚረጭ አውሮፕላን ባለመኖሩ ኢትዮጵያ አውሮፕላኖችን ከደቡብ አፍሪካ ጭምር በኪራይ መልክ አስመጥታ ትጠቀም እንደነበር ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ነች፤ ይህች ትልቅ ሀገር አብዛኛው

በአምስቱ አውሮፕላኖች… ወደ ገጽ 9 ዞሯል



# ከወርቅ ወርቅ የሆነ ገቢ

ወርቅነሽ ደምሰው

በተያዘው 2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ወደ ብሄራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠንም፤ ከወርቅ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪም መጨመሩ ይገለጻል፡፡

ከወርቅ ወርቅ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# በዓሉ ጥቃቅን ልዩነቶችን እየሰበኩ ማበጣበጥ ለሚፈልጉ አካላት ጥሩ ምላሽ የሚሰጥ ነው

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ጥቃቅን ልዩነቶችን እየሰበኩ ማበጣበጥ ለሚፈልጉ አካላት ጥሩ ምላሽ የሚሰጥ በዓል ነው ሲሉ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ ተናገሩ፡፡ በዓሉን በአርባ ምንጭ ከተማ ለማክበር ክልሉ ዝግጅቱን አጠናቆ እንግዶችን መቀበል መጀመሩንም ጠቁመዋል፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ዘንድሮ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ሲከበር የብሔር ብሔረሰቦችን መብት እና ጥቅም በማክበር ነጠላ ትርክቶችን አስወግዶ ገዢ ትርክትን ለማስረጽ ጥሩ አጋጣሚ በሚፈጥር መልኩ ነው፡፡ ከዚህ አኳያም በዓሉ ጥቃቅን ልዩነቶችን እየሰበኩ ማበጣበጥ ለሚፈልጉ አካላት ጥሩ ምላሽ የሚሰጥ ነው፡፡

በዓሉን በተለያዩ ዝግጅቶች ለማክበር ክልሉ ዝግጅቱን አጠናቆ እንግዶችን መቀበል መጀመሩን ተናግረው፤ በዓሉ በሚከበርበት የአርባ ምንጭ ከተማ በዓሉን ታሳቢ


አቶ ጥላሁን ከበደ

ያደረጉ ልማቶችን የማስተካከል እና የማሳመር ስራዎች መከናወናቸውን አመላክተዋል፡፡ በከተማዋ የተጀመሩ የኮሪደር ልማት ስራዎችም በዓሉ በሚከበርበት ቦታ ላይ

በዓሉ ጥቃቅን ልዩነቶችን ... ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# “የሕዝቡ ስቃይ እንዲያበቃና ሀገር ሰላም እንዲሆን ሰላማዊ መንገድን መርጠናል”

- ጃል ሰኚ ነጋሳ

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- የሕዝቡ ስቃይ እንዲያበቃና ሀገር ሰላም እንዲሆን የሰላምን መንገድ መምረጣቸውን የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት የቀድሞው ከፍተኛ አመራር ጃል ሰኚ ነጋሳ ገለጹ። የሰላም ስምምነቱ በሰላም እጦት ለተሰቃየው ሕዝብ እፎይታን እንደሚሰጥም ተገልጿል፡፡

ጃል ሰኚ ነጋሳ የሰላም ስምምነቱን አስመልክተው ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ሕዝቡ እርስ በእርስ በተፈጠረው ግጭት ብዙ ችግር አሳልፏል። በሰላም እጦት ተጎጂ የሆነው ሕዝብ ስቃይ እንዲያበቃ የሰላምን መንገድ መርጠናል፡፡

ሕዝቡ እርስ በእርስ ግጭት ሲሰቃይ ቆይቷል ያሉት ጃል ሰኚ፤ በቡድኑ መካከል በሚደረጉ ግጭቶች በገጠርና በጠረፍ አካባቢዎች የሚኖረው ሕዝብ ጥፋት አድርሷል ብለዋል።

ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ እየተባባሰ የመጣው ችግር የሰላም አማራጭ እንዲመርጡ ማድረጉን ጠቅሰው፤ በክልሉ ያለው ሁኔታ በጦር ሜዳ መፍትሔ እንደማያገኝ


ፎቶ ሀዲስ አብርሃ

መረዳታቸውን ተናግረዋል፡፡

በሕዝቡ ላይ እየተሠራ ያለውን ግፍ ከሕዝቡ መረዳት ይቻላል ያሉት ጃል ሰኚ፤ ሕዝቡ በማያገባው ጉዳይ

“የሕዝቡ ስቃይ ... ወደ ገጽ 9 ዞሯል





## የእጅ ስልክ ይዘው ሲያሽከረክሩ የተገኙ 28ሺህ አሽከርካሪዎች ተቀጡ

- በትራፊክ አደጋ የሚደርሰው የንብረት ጉዳት እየጨመረ ነው

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የእጅ ስልክ ይዘው ሲያሽከረክሩ የተገኙ 28ሺህ አሽከርካሪዎች መቀጣታቸውን የአዲስ አበባ ፖሊስ ትራፊክ ቁጥጥር መምሪያ ገለጸ፡፡ በትራፊክ አደጋ ምክንያት በንብረት ላይ የሚደርሰው ጉዳት እየጨመረ መምጣቱ ተጠቁሟል፡፡

በአዲስ አበባ ፖሊስ ትራፊክ ቁጥጥር መምሪያ የትራፊክ ሙያና ሕዝብ ግንዛቤ ዲቪዥን ኃላፊ ኢንስፔክተር ሰለሞን አዳነ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ በ2017 በጀት ዓመት ሶስት ወራትም 28ሺህ አሽከርካሪዎች የእጅ ስልክ ይዘው ሲያሽከረክሩ ፣ሰባት ሺህ 316 ከፍጥነት በላይ ያሽከረከሩ እንዲሁም ጠጥቶ በማሽከርከር የተያዙ 871 አሽከርካሪዎች ላይ ተገቢው ቅጣት ተላልፏል፡፡

የቴክኒክ ምርመራን ያላሟሉ ስድስት ሺህ 671 አሽከርካሪዎች ተገቢው ቅጣት የተላለፈባቸው መሆኑን ገልጸው፤ እንዲሁም 306 መንጃ ፈቃድ ሳይዙ ያሽከረከሩ ፣213 ሀሰተኛ መንጃ ፈቃድ ይዘው የተገኙ ፣ 45ሺህ ቀይ የትራፊክ መብራትን የጣሱ እና 24 ሺህ የደህንነት ቀበቶ ያልተጠቀሙ አሽከርካሪዎች መከሰሳቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ በየጊዜው በሚደርሰው የትራፊክ አደጋ ምክንያት በንብረት ላይ የሚደርሰው ጉዳት እየጨመረ መምጣቱን አመልክተው፤ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በትራፊክ አደጋ የተመዘገበው የንብረት ጉዳት 8 ሺህ 961 መድረሱን ተናግረዋል፡፡

አደጋው ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመሩ አሳሳቢ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ ይህ አሀዝ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር በቁጥር 708 ጭማሪ አሳይቷል ብለዋል።

በየጊዜው የሚጠፋው ህይወት ፣ የሚጎዳው አካልና የሚወድመው ንብረት የከተማችን አሳሳቢ ጉዳይ ነው ያሉት ኃላፊው፤ አደጋው በአሁኑ ጊዜ በከተማዋ የኮሪደር ልማት ላይ ሳይቀር ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በመሰራት ላይ ያለው የከተማዋ የኮሪደር ልማት የአደጋው ሰለባ መሆኑን ያስታወቁት ኢንስፔክተር ሰለሞን፤ በጅምር ያሉ አንዳንድ የግንባታ ቦታዎች ጭምር ውድመት እያጋጠማቸው መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

አሳሳቢውን የትራፊክ አደጋ ለመከላከል በየጊዜው በከተማዋ የትራፊክ ቁጥጥርና ክትትል እንደሚደረግ የገለጹት ኢንስፔክተር ሰለሞን፤ ሕግ ተላልፈው በተገኙ አሽከርካሪዎች ላይም ተገቢው የቅጣት ውሳኔ እየተላለፈ እንደሚገኝ አስታውቀዋል፡፡

በከተማችን በትራፊክ አደጋ ለሚደርሰው ህይወት መጥፋትና የንብረት ጉዳት መንስኤው ህግን አክብሮ ያለመንቀሳቀስ እንደሆነ የጠቆሙት ኃላፊው፤ የተጠቀሱት የክስ አይነቶች ለትራፊክ አደጋ መከሰት ዋንኛ መንስኤ ናቸው ተብለው የተለዩ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

በሩብ ዓመቱ በከተማዋ በሚገኙ ንፋስ ስልክ ላፍቶ፣አቃቂና ቦሌ ክፍለ ከተሞች ላይ ቁጥሩ የጨመረ የትራፊክ አደጋ መከሰቱን የገለጹት ኢንስፔክተር ሰለሞን፤ አራዳ ክፍለ ከተማ ደግሞ ምንም ሞት ያልተመዘገበበት እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በከተማዋ የትራፊክ መምሪያ በኩል ከክስና ቅጣት ያለፈ የግንዛቤ ማስጨበጫ ምክር እንደሚሰጥ የገለጹት ኃላፊው፤ አደጋ በሚበዛባቸው አካባቢዎችም ተጨማሪ ስምሪት በማድረግ ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገ ስለመሆኑ አስታውቀዋል፡፡

የትራፊክ አደጋን መቆጣጠር የአንድ ተቋም ኃላፊነት ብቻ አይደለም ያሉት ኢንስፔክተር ሰለሞን፤ እግረኞችንና የእምነት ተቋማትን ጨምሮ የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ችግሩን ለመታደግ ልዩ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

# በዓሉ ብዝኃነትና ኅብረ ብሔራዊ አንድነት የሚጠናከርበት ነው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የዘንድሮው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በዓል ብዝኃነት እና ኅብረ ብሔራዊ አንድነት የሚጠናከርበት መሆኑን የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ገለጹ፡፡

የአዲስ አበባ ምክር ቤት ለ19ኛ ጊዜ የሚከበረውን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በዓል "ሀገራዊ መግባባት ለህብረብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል አክብሯል፡፡

በወቅቱ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር እንደገለጹት፤ ዘንድሮ ለ19ኛ ጊዜ የሚከበረውን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን በዓል ታዳሚዎች እሴቶቻቸውን፣ባህሎቻቸውንና ልምዶቻቸውን በመለዋወጥ ብዝኃነትን እና ኅብረ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት የሚያጠናክሩበትና ስለ ዘላቂ ሰላምና እድገት የሚወያዩበት የኢትዮጵያውያን ቀን ነው፡፡

ኢትዮጵያ ብዝኃ ማንነት ካላቸው የዓለም ሀገራት መካከል አንዷ መሆኗን አመልክተው፤ ቀደም ባሉት ጊዜያት ብዝኃነትን በአግባቡ ከማስተናገድ እና ኅብረብሔራዊ አንድነት ከማጠናከር አንጻር ጉድለቶች መታየታቸውን ተናግረዋል።

በሀገሪቱ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ለመፍታትና አንድነትን ለማጠናከር ውይይትና ምክክር ወሳኝ መሆኑን አንስተው፤ በሀገራዊ ምክክር ሂደት ልዩነትን ማጥበብ እና የጋራ ሃሳብ በማፍለቅ ህብረብሔራዊ አንድነትን ማጠናከር እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡

አዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ቋንቋ፣ ባህልና አመለካከት ያለባት ሁሉም በህብር የሚኖሩባት ከተማ መሆኗን አንስተው፤ የተሰሩ የልማት ስራዎችም ከተማዋን አዲስ ገጽታ ያጎናጸፉና ሀገሪቱን የዕድገት ማሳያ እያደረጋት ይገኛል ብለዋል።



አቶ አገኘሁ ተሻገር



ከንቲባ አዳነች አቤቤ

ኅብረብሔራዊ አንድነትን በሚያጠናክሩ፣ ዘላቂ ሰላምን በሚያሰፍኑ ጉዳዮች ላይ የተጀመረው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የመሠረተ ልማት እንዲሁም ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ስራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል መልእክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የአዲስአበባከተማከንቲባአዳነችአቤቤበበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔረሰቦች፣ቋንቋዎች፣ባህሎች፣ ትውፊቶችና ወጎች ያሉባት ድንቅ ሀገር መሆኗን አንስተው፤ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ብዝኃነትን መገንባት ለሀገር እድገት ወሳኝ ነው ብለዋል፡፡

ባለፉት ጊዜያት ከብሔር ብሔረሰቦች መብት ጋር የሚነሱ ጥያቄዎችን ተከትሎ በተለያዩ አካባቢ ግጭቶች መከሰታቸውን አስታውሰው፤ የብሔሮች ፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን መከበሩ ጠንካራ መተሳሰብና አብሮነት ያሉባት ሀገር ለመገንባት የራሱን ድርሻ እንደሚያበረክት ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያዊያውያን ከሚያለያዩን ይልቅ አንድ የሚያደርጉን ይበዛሉ፡፡ ያሉንን ልዩነቶች እንደ ጌጥና ጉልበት መጠቀም ይኖርብናል ያሉት ከንቲባዋ፤ አንድነታችንን በጠንካራ መሠረት ላይ በመጣል ለቀጣይ ትውልድ ሀገረ ግንባታ ስንቅ ማስተላለፍ ይኖርብናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አዲስ አበባ ለኅብረ ብሔራዊነት ማሳያ የሆነች ትልቋ የኢትዮጵያውያን ቤት እንደሆነች ገልጸው፤ ለአንድነት ሳንካ የሆኑትን ለይተን በማስወገድ እና አካታችነትን በመከተል አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ብቻ ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያውያን ምቹ እንድትሆን የሚሰሩ ተግባራት ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል፡፡

# ሴቶች በኢነርጂው ዘርፍ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲያሳድጉ እየተሠራ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ሴቶች በኢነርጂው ዘርፍ ያላቸውን ተሳትፎ በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እየተሰራ ነው ሲል የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጅነር ሱልጣን ወሊ (ዶ/ር)፤ የኢትዮጵያ ሴቶች በኢነርጂ ማህበር፤ በኢነርጂ ዘርፍ ስኬት ላስመዘገቡ ሴቶች የእውቅና መርሃ-ግብር ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ሴቶች በኢነርጂው ዘርፍ ያላቸውን ተሳትፎ በማሳደግ ኢኮኖሚያዊ እድገትን እውን ለማድረግና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እየተሰራ ነው።

ሴቶች በኢነርጂው ዘርፉ እንዲሳተፉ ማበረታታት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማሳለጥና ሀገራዊ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ስለሚጠቅም ወደ አመራርነት የማምጣትና ተሳትፏቸውን የማሳደግ ስራ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

እየተሰራ ባለው የኢነርጂ ተደራሽነት አብዛኛውን ጊዜ ተጠቃሚ የሚሆኑት እናቶችና ሕፃናት ናቸው፤ እናቶች በኢነርጂ ዘርፍ ያላቸውን ተጠቃሚነት ይበልጥ ለማሳደግ በዘርፉ ተሳትፏቸውን የማሳደግ ስራ እየተሰራ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኢነርጂ የእናቶችን ጤና ለመጠበቅ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፤ የእናቶች ጤንነትን ለመጠበቅ ንፁህ ምድጃዎችን ተደራሽ የማድረግ ስራ በትኩረት እየተሰራ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ኢነርጂ ለማንኛውም ሀገራዊ የልማት እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆነ ግብዓት ነው፤ ኢትዮጵያ ያላትን የኢነርጂ አቅም በመጠቀም ሁለተናዊ እድገት ለማምጣት እየሰራች መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሴቶች የኢነርጂ ማህበር ፕሬዚዳንት ወይዘሮ አደይ ጌታቸው በበኩላቸው፤በኢነርጂው ዘርፍ ሴቶች ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ የእኩልነት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ለዘለቄታዊ ሀገር ልማት ወሳኝ ነው፡፡



ወይዘሮ አደይ ጌታቸው



ኢንጅነር ሱልጣን ወሊ (ዶ/ር)

በዘርፉ የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ፣ማበረታታትና ባላቸው አቅም ላይ ኢንቨስት ማድረግ ኢኮኖሚያዊ እድገትን እውን ለማድረግ ይጠቅማል ነው ያሉት፡፡

በአፍሪካ አህጉር በኢነርጂ ዘርፍ ሴቶች ያላቸው ተሳትፎ ከወንዶች አንፃር ሲታይ አነስተኛ ነው ያሉት ወይዘሮ አደይ፤ ምክንያቱም ሴቶች ወደ ዘርፉ እንዳይገቡ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ያሉ በመሆኑ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ዘርፉ ለሴቶች ከባድ ተደርጎ በማህበረሰቡ ዘንድ በመታሰቡ፤ ታዳጊ ሴቶች ሙያውን በአግባቡ እንዳያውቁት በርካት ተግዳሮቶች መኖራቸው የሴቶችን ተሳትፎ በዘርፉ ላይ አናሳ አድርጎታል ሲሉም ገልጸዋል።

ማህበሩ ያለውን ተግዳሮት በመረዳት ለጠንካራና ለታታሪ ሴቶች ትኩረት የመስጠት ፤ በተለይም ታዳጊ ሴቶች ወደ ዘርፉ እንዲገቡ እውቅና በመስጠትና ታሪክን የመቀየር ስራ እየሰራ እንደሚገኝም ተናግረዋል፡፡

የኢትጵያ ሴቶች በኢነርጂ ማህበር፤ ሴቶች በኢነርጂ ዘርፍ ያላቸውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ ላለፉት አራት ዓመታት እየሰራ ነው፤ እየሰራ ያለውን ስራም አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ወይዘሮ አደይ ጠቁመዋል፡፡



አህመድ መሃመድ

## ፌስቲቫሉ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት መካከል አንድነትንና ትብብርን የሚያጠናክር ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- ሁለተኛው የምሥራቅ አፍሪካ የጥበብና ባህል ፌስቲቫል በሀገራቱ መካከል አንድነትንና ትብብርን የሚያጠናክር መሆኑን የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ገለጸ።

ፌስቲቫሉ "ጥበብና ባህል ለቀጣናዊ ትብብር" በሚል መሪ ቃል ከጥር 15 እስከ 18 በአዲስ አበባ እንደሚካሄድም ተገልጿል።

የፌስቲቫሉን ዝግጅት አስመልክቶ የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ከምሥራቅ አፍሪካ ባሕል ፌስቲቫል ተሳታፊዎች ጋር ተወያይቷል። በወቅቱ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የሥራ አመራር ሥራ አስፈፃሚ አህመድ መሃመድ እንደገለጹት፤ በፌስቲቫሉ ባህላዊ ክዋኔዎችን፣ ፊልምና ሙዚቃዎች የሚቀርቡበት ነው።

ምሥራቅ አፍሪካ የቋንቋና የባህል ብዝሃነት ያለበት አካባቢ ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቀጣናው በተለያዩ ታሪካዊ ክስተቶች ምክንያት ግጭቶችና መለያየት እንዲሁም ኋላ ቀርነት ያለበት መሆኑን አመልክተዋል፡፡

እነዚህን ሕዝቦች የሚያግባቡና ትስስራቸውን የሚያጠናክሩ የባህልና የኪነ ጥበብ ሥራዎች በፌስቲቫሉ እንደሚቀርቡ ጠቁመው፤ የፌስቲቫሉ ዓላማም የቀጣናውን ሕዝቦች ማቀራረብ፣ ማስተዋወቅና የባህል ልውውጥ እንዲኖር ምቹ ዕድል መፍጠር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ፌስቲቫሉ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት መካከል አንድነትንና ትብብርን በሚያጠናክር መልኩ ይከናወናል ብለዋል።

ሥራ አስፈፃሚው ፤ ከሦስት ዓመት በፊት በአዲስ አበባ ከተማ የተዘጋጀው አንደኛው የምሥራቅ አፍሪካ የባሕልና ኪነ ጥበብ ፌስቲቫል የሀገራቱን ትስስርና የባሕል ትውውቅ ያጎለበተ ነበር። ፌስቲቫሉ በተከታታይ መዘጋጀቱ እየጎለበተ የመጣውን አንድነትን ለማጠናከር አስተዋጽኦው የጎላ እንደሆነ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የፌስቲቫሉ ተሳታፊና አዘጋጅ መሆኗ ያላትን የባሕል ጥልቀት አጉልታ ለማውጣት መልካም አጋጣሚ ስለመሆኑም ተናግረው፤ በባሕል እና ቱሪዝም ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግም እንደሚረዳ አንስተዋል።

ከቀጣናው ሀገራት አምባሳደሮች ጋር ለመወያየት በተዘጋጀው መድረክ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ዴኤታ ነፊሳ አልማህዲን እንደገለጹት፤ ፌስቲቫሉ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን ትስስር ለማጠናከር ያለመ ነው።

ፌስቲቫሉን ኢትዮጵያ ማስተናገዷ የሀገሪቱን ባህል አጉልቶ ለማሳየት እንደሚያስችል ጠቁመው፤ ፌስቲቫሉ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት የሚሰባሰቡበት አጋጣሚን ይፈጥራል ነው ያሉት።

የኬንያ፣ የጅቡቲ እና የሱዳን ኤምባሲ ተወካዮች በውይይቱ ላይ ተሳትፈዋል። የውይይቱ ዋና አላማም ለፌስቲቫሉ መደረግ ያለባቸውን ዝግጅቶች ለመለየት ሲሆን፤ የመጀመሪያው የምሥራቅ አፍሪካ የጥበባትና ባህል ፌስቲቫል በ2014 ዓ.ም በወዳጅነት ፓርክ መካሄዱ ይታወሳል።

# በኦሮሚያ ክልል ለበጋ መስኖ ልማት ከ15 ሺህ በላይ የውሃ መሳቢያ ፓምፖች ተሰራጩ

ራስወርቅ ሙሉጌታ



አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ለበጋ መስኖ ልማት ከ15 ሺ በላይ የውሃ መሳቢያ ፓምፖች ለአርሶ አደሩ መሰራጨታቸውን የክልሉ መስኖና አርብቶ አደር ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ኃላፊ ኢንጅነር ግርማ ረጋሳ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ በዘንድሮው ዓመት ከ22 ሺህ በላይ የውሃ መሳቢያ ለአርሶ አደሩ ፓንፖችን ለማሰራጨት ታቅዶ እስካሁን ከ15 ሺህ በላይ ፓንፖችን ለማሰራጨት ተችሏል። እነዚህን በመጠቀም አርሶ አደሩ ከወንዞች፣ከሀይቆችና ከከተሩ ውሃዎች ለበጋ ለመስኖ ልማት የውሃ አማራጭ እንዲያገኝ እየተደረገ ነው።

ለአርሶ አደሩ የተሰራጩት የውሃ መሳቢያ ሞተሮችም በክልሉ ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ለተያዘው ግብ መሳካት የጎላ ፋይዳ እንዳላቸው ነው የተናገሩት፡፡

በባህላዊ መንገድ የሚጠቀምባቸውን የመስኖ አውታሮች፤ የወንዝ ቅየሳ በመስራት። የወንዝ ውሃ ተደራሽ በማይሆንባቸው አካባቢዎች ደግሞ በተለያየ መጠን አነስተኛ የውሃ ጉድጓዶችን በማዘጋጀት እንዲጠቀሙ የማድረግ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል ብለዋል።

አብዛኛው አርሶ አደር የባህላዊ መስኖ አጠቃቀምን የሚከተል በመሆኑ በተወሰነ ደረጃ የውሃ እጥረት ይገጥማል የሚል ስጋት አለ ያሉት ኢንጅነር ረጋሳ ፤ይህንንም ለመቅረፍ በአንድ በኩል ህብረተሰቡ ውሃን በአግባቡ እንዲጠቀም ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎች እየተከናወኑ ሲሆን፤ በሌላ በኩል አመራሩም ያሉትን የውሃ አማራጮች በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል እየተንቀሳቀሰ መሆኑን አስረድተዋል'።

ኃላፊው እንዳብራሩት፤ በዘንድሮው ዓመት በበጋ መስኖ ለማልማት የታቀደው ስንዴ ላይ ትኩረት በማድረግ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ለማልማት ነው። ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ማልማት የተቻለው ሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ነበር። ዘንድሮ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር ተጨማሪ ለማልማት ሲታቀድ ከባለፈው ዓመት ልምድ በመቅሰም ሲሆን፤ ለዚህ የሚበቃ ዝግጅት ለማድረግም ሲሰራ ቆይቷል።

እስካሁን ለተዘጋጁት መሬቶች በቂ የዘርና የማዳበሪያ አቅርቦት በመዘጋጀቱ በግብርና ቢሮ በኩል ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ በአርሶ አደሩም በኩልም ላለፉት ዓመታት የነበሩ ልምዶችን በመቀመር በበጋ መስኖ ልማት ያለው ተሳታፊነትና አጠቃቀም እየተሻሻለ መምጣቱን ገልጸዋል።

ይህም ሆኖ ክልሉ ካለው ስፋት አኳያ ሁሉንም ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ለማዳረስ የተወሰነ ክፍተት ሊፈጠር ይችላል የሚል ስጋት መኖሩን ጠቁመው፤ ይህንንም ከግምት በማስገባት ስራው እንዳይስተጓጎል በቅርበት ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውንም አመልክተዋል።

ክልሉ ከአለው የቆዳ ስፋት፤ ለበጋ መስኖ ልማት ከአለው ምቹነት፤ በውሃ ሀብት እና በመሳሰሉት አቅሞች ምክንያት የበጋ መስኖ ልማት በስፋት እንደሚካሄድ ጠቁመዋል፡፡

# በባህር ዳር ከተማ 22 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ኮሪደር ልማት ለማካሄድ ታቅዶ እየተሠራ ነው

ነፃነት አሰሙ



አዲስ አበባ፡- በባህር ዳር ከተማ 22 ነጥብ አምስት ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የኮሪደር ልማት ለመስራት ታቅዶ ከዚህ ውስጥ ሶስት ኪሎ ሜትሩን ለማጠናቀቅ ጥብቅ ክትትል እየተደረገ እንደሆነ በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ገለጸ፡፡

በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የከተማና መሰረተ ልማት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ተሻገር አዳሙ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ በከተማዋ 22 ነጥብ አምስት ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የኮሪደር ልማት ለማከናወን ታቅዶ አሁን ላይ ሶስት ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የኮሪደር ልማት ስራ ተጀምሮ እየተፋጠነ ነው፡፡

የሶስት ኪሎ ሜትር የኮሪደር ልማት ስራው ከተጀመረ ሁለት ወራት ማስቆጠሩን አስታውሰው፤ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በአጭር ጊዜያት ለማጠናቀቅ ሰፊ ክትትል እየተደረገ እንዳለ አስረድተዋል፡፡

በዋናነትም የኮሪደር ልማቱ ወደ ሶስት ሜትር የሚሆን ስፋት ያለው የሳይክል መንገድ በሁለቱም አቅጣጫ እንደሚኖረው፣ ከአምስት እስከ ስምንት ሜትር ስፋት የሚደርስ የእግረኛ መንገድ፣ ከሶስት እስከ አራት ነጥብ አምስት የሚሆን አረንጓዴ ቦታ፣ የሳይክልና የባስ ማቆሚያዎች ፣ አልፎ አልፎ የፈጣን ምግብ መስተንግዶ አገልግሎት መስጫዎች፣ የሕዝብ መዝናኛዎች እንዲሁም ፋውንቴኖች እንደሚኖሩትም ጠቅሰዋል፡፡

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በተለይም የመብራት፣ ውሃና የቴሌኮም አገልግሎት መስጫዎች መስመሮች አሁን ብቻ ሳይሆን የወደፊቱንም ታሳቢ ያደረገ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ስራዎች መጠናቀቃቸውን አመልክተዋል፡፡

በተጨማሪም ከስራ እድል ፈጠራ አንፃር ኮሪደር ልማቱ መልካም አጋጣሚ መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህ የሶስት ኪሎ ሜትር ስራ ብቻ እንኳ ከ750 በላይ ለሚሆኑ ሰዎች የስራ እድል ተፈጥሯል ብለዋል፡፡

የአካባቢውን ማህበረሰብ የስራ ባህል ከማዳበር አንፃርም አስተዋፅኦ እንዳለው ጠቁመው፤ ቀን ብቻ ሳይሆን ምሽቱን ጨምሮ በሶስት ፈረቃ 18 ሰአት እየተሰራ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር ለባለሀብቶች በጨረታ የሚተላለፉ የቢዝነስ ቦታዎች እንደተፈጠሩ ገልፀው፤ይህም ከተማውን ከማልማት አኳያ አስተዋፅኦ እንዳለው ጠቁመዋል፡፡ ጎን ለጎንም የአጥር ዲዛይን፣ የህንፃዎች ቀለም፣ የህንፃዎች መብራት እንዲሁም የመንገድ መብራት ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

አብዛኞቹ ህንፃዎችና ቤቶች ከመንገድ ዳር ርቀታቸውን ጠብቀው ከመሰራታቸው አኳያም አስተዳደሩ ሙሉ በሙሉ በልማቱ ምክንያት ከአካባቢው የሚነሳ ሰው እንደሌለም ጠቅሰዋል፡፡

ከካሳም አኳያ የጥቂት ሰዎች የአጥር ክፍያ እንደሚኖርባቸው ገልፀው፤ ከዛ ባሻገር ማህበረሰቡ አጥሩን እንዴት ልጠር፣ ደጁን እንዴት ላሳምር በሚል እያገዛቸው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ባህር ዳር ከተማ ከዚህ በፊት ውብ እንደሆነች ያስታወሱት ሥራ አስኪያጁ፤ አሁን ደሞ በኮሪደር ልማቱ የማፈራረስና የመቆፋፈር ስራው የበለጠ ለማስዋብና መንገዶቿን ለማስፋፋት ነውና የኮሪደር ልማቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ህብረተሰቡ በትዕግስት እንዲጠብቅ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በቀጣይ ደግሞ አምስት ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የኮሪደር ልማት ስራ ለማከናወን መታቀዱን የገለፁት ሥራ አስኪያጁ፤ ቀሪዎቹ ኪሎ ሜትሮችም የገንዘብ አቅማቸው እየታየ እንደሚቀጥሉ ጠቁመዋል፡፡

# የዘመን እንግዳ

# «የስድስት መርከቦች ግዥ መፈጸሙ 94 በመቶ የሚደርሰውን የሀገሪቱን የወጪ ገቢ ጭነት ለማሳለጥ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል»

ዶክተር በሪሶ አመሎ
የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ



**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ በተያዘው በጀት ዓመት የስድስት የጭነት መርከቦች የግዢ ሂደት በዚህ ዓመት እንደሚጠናቀቅ አመልክቷል። የእነዚህ መርከቦች ግዥ እያደገ የመጣውን የሀገሪቱን የገቢና ወጪ ንግድ ለማሳለጥ ትልቅ አቅም እንደሚፈጥር አስታውቋል።

ለመሆኑ የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ከየት ተነስቶ የት ደረሰ ? በአሁኑ ወቅትስ ያለው አጠቃላይ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል ለሚሉት እና ሌሎችም ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡን የተቋሙን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር በሪሶ አመሎ አነጋግረን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፤- የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አመሰራረት የተቋቋመበት ዓላማ ምንድን ነው ?**

**ዶ/ር በሪሶ፤-** ተቋሙ የተቋቋመበትን ዓላማ ከማንሳቴ በፊት ስለ አመሰራረቱ ትንሽ ልግለጽ። የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ፤ በሎጀስቲክስ አገልግሎት ዘርፍ በተናጠል ሲንቀሳቀሱ የነበሩትን ሶስት ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ አክስዮን ማሕበር፣ የባሕርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅትና የደረቅ ወደብ አግልግሎት ድርጅቶችን በማዋሀድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 255/2004 የተቋቋመ የመንግስት የልማት ድርጅት ነው። መስከረም 2007 ዓ.ም ደግሞ የቀድሞው ኮሜት ትራንስፖርት አክሲዮን ማሕበር ድርጅቱን ተቀላቅሏል።

የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት መጋቢት አንድ ቀን 1956 ዓ.ም በብር 50,000 (ሃምሳ ሺ) መነሻ ካፒታል የተቋቋመ ሲሆን ይህ ዕለት ለኢትዮጵያ ዘመናዊ የባሕር ትራንስፖርት አገልግሎት የመሰረት ድንጋይ የተጣለበት ነበር ማለት ይቻላል።

የንግድ መርከብ ሲቋቋም የአሜሪካው ታውረስ ኢንቨስትመንት 51 ከመቶ እንዲሁም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የገንዘብ ሚኒስቴር ደግሞ 49 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። መጋቢት 18 ቀን 1956 ዓ.ም የድርጅቱ ካፒታል ወደ 375,000 (ሶስት መቶ ሰባ አምስት ሺ) ብር እንዲያድግ ተደረገ። በዚህ ጊዜም ነበር የመጀመሪያዎቹ ሶስት መርከቦች ማለትም ንግስተ ሳባ፣ የይሁዳ አንበሳ እና ላሊበላ የተባሉት መርከቦች የተገነቡት።

በዚህም መሰረት ድርጅቱ በእነኚህ ሶስት መርከቦች በ1958 ዓ.ም ሥራውን በይፋ ጀመረ። ድርጅቱ በ1959 ዓ.ም፣ በ1960 እና በ1961 ዓ.ም በተከታታይ አዱሊስ፣ ጣና ሐይቅ እና አሸንጌ የተባሉትን ተጨማሪ መርከቦች በመግዛት በአስተማማኝ መሰረት ጉዞውን አጠናክሮ ለመቀጠል ችሏል።

የባሕር ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት ከውህደት በፊት ያለውን ታሪክ ስናይ፤ የገቢና ወጪ ንግድ ዝውውርን ለማቀላጠፍ ሚያዚያ 1960 ዓ.ም በ500,000 ብር መነሻ ካፒታል ነበር የተቋቋመው። ድርጅቱ የሀገራችን ገቢና ወጪ እቃዎች ሲስተናገዱ በነበሩባቸው ወደቦች ሁሉ በመገኘት ሀገራዊ ኃላፊነቱን ተወጥቷል። ድርጅቱ ከኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት በፊት በዋናነት ከወደብ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶቹን በአሰብ ወደብ በኩል ሲያከናውን ነበር።

የኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት ተከትሎ የሀገራችን ገቢና ወጪ እቃዎች በሙሉ በጅቡቲ ወደብ በኩል ማስተናገድ ሲጀመር፤ ራሱን በወደብ መሳሪያዎች፣ በሰው ኃይልና በአሰራር በማደራጀት ከባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን ይሰጥ ነበር። ድርጅቱ በዋናነት ዕቃዎችን ከመርከብ የማውረድና የመጫን አገልግሎት፣ ዕቃዎችን በባሕር ወደብ አመች በሆነ ቦታ ወይም መጋዘን በጊዜያዊነት አደራጅቶ የማቆየት ሥራዎች፣ የየብስ ትራንስፖርት አገልግሎትና የትራንዚት ሥራዎችን ለበርካታ ዓመታት ያከናውን ነበር።

የደረቅ ወደብ አገልግሎትን ስንመለከት፤ በወቅቱ በአገሪቱ የሚካሄደው የወጪና የገቢ ንግድ እንቅስቃሴ አብዛኛው የሚስተናገደው በጅቡቲ በኩል ብቻ ነበር። በመሆኑም ከዚህ ጋር ተያይዞ ያለውን የወደብ መጨናነቅና ወደሀገር ውስጥ የሚገቡ እቃዎች በወደብ ላይ የሚኖራቸውን የረጅም ጊዜ ቆይታ መቀነስ አስፈላጊ ነበር።

ይህንን ችግር ለማቃለል ብሎም ለዚህ አገልግሎት እየዋለ ያለውን የውጭ ምንዛሪ ለመቀነስ እንዲቻል በአገሪቱ ክልል ወሰን ውስጥ የደረቅ ወደብ አገልግሎት ማቋቋም ያስፈልግ ነበር። ይህም በመንግስት በመታመኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 136/1999 መሰረት የደረቅ ወደብ አገልግሎት ድርጅት እንዲቋቋም ተደረገ። ድርጅቱ ከጥር ወር 2000 ዓ.ም ጀምሮ ቢሮ የማደራጀትና መዋቅር የማዘጋጀት፣ የሰው ኃይል የማሟላት፣ እንዲሁም የተለያዩ መመሪያዎችን በመቅረፅ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቶ በ2001 ዓ.ም ሥራውን ጀመረ።

የኮሜት ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር፤ በደንብ ቁጥር 193/86 የተቋቋመና በዋናነት በትራንስፖርት ዘርፍ እና ሌሎች ተጓዳኝ የልማት ሥራዎች ብዙ ተወዳዳሪዎች ባሉበት የኢኮኖሚ ዘርፍ የሚገኝ ተቋም ነው። ተቋሙ በተሰማራበት የንግድ ዘርፍ መስከ ውድድሩን በመቋቋም አትራፊ በመሆን ሕልውናውን አስጠብቆ የቆየ አንጋፋ ድርጅትም ነበር።

**አዲስ ዘመን ፡- ተቋማቱ ን ወደ አንድ በማምጣት ማንቀሳቀስ ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነበር ?**

**ዶ/ር በሪሶ ፡-** በወቅቱ በሀገሪቱ ከነበረው ኢኮኖሚያዊ እድገት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሥርዓት መገንባት አስፈላጊነቱ የሚያጠያይቅ አልነበረም። በመሆኑም እነዚህ በተናጠል ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ተቋማት መቀናጀት ተገቢ ስለነበር በተደረገው ከፍተኛ የመንግስት ድጋፍና ውሳኔ በባሕርና ሎጀስቲክስ ዘርፍ በተናጠል ሲንቀሳቀሱ የቆዩትን ድርጅቶች በ2004 ዓ.ም ለማዋሃድ ተችሏል። የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት (ኢባትሎ) የሚል ስያሜ በመያዝ በሶስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ስራውን ጀመረ። በዚህ ሁኔታ እየሰራ ከቆየ በኋላ በሚያዚያ 2008 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ የመቋቋሚያ ካፒታሉ ከነበረበት ሶስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ወደ ሀያ ቢሊዮን ብር እንዲያድግ ተደርጓል።

**አዲስ ዘመን ፡- ተቋሙ እንዲያከናውን የተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነቶች ምን ምን ነበሩ ?**

**ዶ/ር በሪሶ ፡-** ተቋሙ የተሰጠው ኃላፊነት በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ቁልፍ ሚና ያላቸው ናቸው ለማለት ይቻላል። ዝርዝር ለማድረግ ያክል፤ በጠረፍ አካባቢ፣ በዓለም አቀፍ ባሕሮች እና በሀገር ውስጥ የውሃ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤ የዕቃ አስተላላፊነት ውክልና፤ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት፤ የመርከብ ውክልና እና የአየር ውክልና አገልግሎት መስጠት፤ ለወጪና ገቢ ዕቃዎች የስቴቨዶሪንግ፤ ሾር ሃንድሊንግ፤ የወደብ፤ የመጋዘን እና ሌሎች የሎጀስቲክስ አገልግሎቶች መሰጠት፤ የኮንቴይነር ማስተናገጃና ማከማቻ አገልግሎት መስጠት፤ የወደብ ይዞታዎችን ማልማት፤ ማስተዳደርና አገልግሎት መስጠት፤ የማሪታይም ዘርፍ የሙያ ክህሎት ማሳደጊያ የሰው ኃይል ልማትና ስልጠና ማዕከል ማቋቋምና ማስተዳደር፤ የሃገሪቱን የገቢና የወጪ ንግድ ፍላጎት በማጥናት የማሪታይምና ትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን ብቃት ለማጎልበት የሚያስችል የቴክኖሎጂ አቅም ማሳደግ፤ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ ናቸው።

**ባለፉት አራት ዓመታት ድርጅቱ ባከናወናቸው ሥራዎች የተገኙ ውጤቶች በአንፃራዊነት ሲታይ አመርቂ ናቸው። ስለዚህም እንደ ማሳያ ያለፉትን አራት ተከታታይ ዓመታት የገቢ መጠን በምሳሌነት መውሰድ ይቻላል**

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ተቋሙ እንዲያከናውነው ከተሰጠው ተልዕኮ መካከል የሀገር ውስጥ የውሃ ትራንስፖርትን ማስፋፋት አንዱ ነው። በዚህም ረገድ የጣና ሐይቅ ትራንስፖርት ድርጅትን ከሕዳር ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ ከክልሉ መንግስት የልማት ድርጅት በመረከብ ውህደቱን ወደ አምስት አድርሶታል። ይህ የሀገር ውስጥ የውሃ ትራንስፖርት ጅማሮም ጣና ሐይቅ ላይ ብቻ ሳይሆን በታላቁ የሕዳሴ ግድብ፣ ባሮ፣ አባያ እና ሌሎች ለውሃ ትራንስፖርት አመቺነት ባላቸው ስፍራዎች ሁሉ በማስፋፋት ረገድ ዓይነተኛ ሚና የሚጫወት ነው። በዚህ ረገድም በቀጣይ የሚከናወኑ በርካታ ሥራዎች ይኖራሉ።

**አዲስ ዘመን፡-ባለፉት ዓመታት እንደ ተቋም ከተያዘው አቅድ አኳያና እንደ ሀገር ከታሰበው አንጻር ምን ያህል ውጤታማ መሆን ተችሏል ?**

**ዶ/ር በሪሶ ፡-** ምን ያህል ወጤታማ ሆኗል ? የሚለውን ለመገምገም በቅድሚያ የተቋቋመበትን ዓላማ ማየቱ ተገቢ ነው። የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ የሀገራችንን የኢኮኖሚ ዕድገት ለመደገፍ የሎጀስቲክስ አቅርቦቱን ዘመናዊ፤ ቀልጣፋ እና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን ለማድረግ ጠንካራና ብቃት ያለው የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ የተቋቋመ የልማት ድርጅት ነው። ከዚህ አኳያ ድርጅቱ በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ መስክ የሚሰጣቸውን ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶች በዕቅድ በመምራት የተሳካ አፈጻጸም እያስመዘገበ ነው ለማለት የሚያስደፍሩ ሥራዎችን ለማከናወን ተችሏል።

ባለፉት አራት ዓመታት ድርጅቱ ባከናወናቸው ሥራዎች የተገኙ ውጤቶች በአንፃራዊነት ሲታይ አመርቂ ናቸው። ለዚህም እንደ ማሳያ ያለፉትን አራት ተከታታይ ዓመታት የገቢ መጠን በምሳሌነት መውሰድ ይቻላል። ዓመታዊ የገቢ መጠን በ2013 ዓ.ም. 29 ነጥብ 80 ቢሊዮን ብር፤ በ2014 ዓ.ም. 51 ነጥብ 38 ቢሊዮን ብር፤ በ2015 ዓ.ም. 42 ነጥብ 73 ቢሊዮን ብር፤ በ2016 ዓ.ም 57 ነጥብ 14 ቢሊየን ብር በላይ ዓመታዊ ገቢ አግኝቷል። በተመሳሳይ ለውጤታማነቱ አንዱ ማሳያ የሚሆነውን የጭነት መጠንም ያለፉትን አራት ዓመታት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «የስድስት መርከቦች ግዥ...



ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ስንመለከት፤- በባሕር የተጓጓዘ ገቢ ጭነት በ2013 ዓ.ም. 4,814,206 ቶን፤ በ2014 ዓ.ም. 3,616,343 ቶን፤ 2015 ዓ.ም 2,965,542፤ እንዲሁም በ 2016 ዓ.ም ከአራት ሚሊየን 590 ሺህ ቶን በላይ የጭነት አገልግሎት ማከናወን ተችሏል።

በዚህ ረገድ በተለይም በ2016 በጀት ዓመት በርካታ ዓለማቀፍና አገር አቀፍ ደረጃ የተከሰቱ ችግሮች መኖራቸው ይታወቃል። እነዚህን ችግሮች በመቋቋም ከላይ የተዘረዘሩትን ስኬቶች ማስመዝገብ ችሏል። ብሎም ሌሎች ተግባራትንም በማከናወን በበጀት ዓመቱ በእቅድ የተቀመጡትን በአግባቡ ለማጠናቀቅ መብቃቱ እንደ ትልቅ ስኬት የሚወሰድ ነው።

**አዲስ ዘመን፤- የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ለአጠቃለይ ሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገት የሚኖረው ፋይዳ እንዴት ይገለጻል ?**

**ዶ/ር በሪሶ፤-** ተቋሙ አጠቃላይ ለሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገት እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ በዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተከሰቱ ያሉ ነገሮችን ማየትም ተገቢ ነው። ዓለማችን ከሁለት ዓመታት በላይ ከቆየው የሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት ኢኮኖሚያዊ ጫና ሳትላቀቅ እና ከአንድ ዓመት በፊት የተቀሰቀሰው የእስራኤል ሐማስ ጦርነት በመካከለኛው ምስራቅ አጠቃላይ የንግድም ሆነ የመርከቦች እንቅስቃሴ ላይ ጉልህ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል።

በየመን የሁቲ ታጣቂዎች በጦርነቱ ለሐማስ ድጋፍ ለማድረግ በሚል የንግድ መርከቦች በኤደን ባህረ-ሰላጤ እንዳይንቀሳቀሱ ጥቃት በማድረስ ላይ ይገኛሉ:: በዚህ ምክንያት የምርቶች እንቅስቃሴ በጉልህ የተስተጓጎለበት ወቅት ከመሆኑም በላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለብዙ አገራት ፈተና የሆነ ከፍተኛ የዋጋ ንረትም ተፈጥሯል:: ይህም ከባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ጋር ያለው ተዛምዶ ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን ኢባትሎም ሆነ በዘርፉ የተሰማሩ ግዙፍ ዓለማቀፍ ተቋማት የተፈተኑበት ክስተት ሆኖ ዛሬም ድረስ ቀጥሏል::

በሌላ በኩል የዓለም የነዳጅ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ እያሻቀበ ባለበት በዚህ ወቅት ለአጭር ጊዜ ቀንሶ የነበረው የኮንቴነር ማጓጓዣ ዋጋ በእጅጉ እየጨመረ ይገኛል:: እነዚህና መሰል ዓለማቀፋዊ ተጽኖዎች ለመቋቋም የሎጀስቲክስ አቅምን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሰፊ ጥረቶች በተቋም ደረጃ ሲደረጉ የቆዩ ሲሆን ከነዚህም መካከል የድርጅቱን በባሕር የማጓጓዝ አቅም ለማሳደግና በቀጠናው ያለውን ድርሻ ለማሻሻል ግዙፍ መርከቦች ለመግዛት ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል:: ከዚህ በተጨማሪም የ205 ከባድ ተሽከርካሪዎች ግዢ ለማከናወን በእቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል::

የደረቅ ወደቦችን አቅም ከማሳደግ አኳያ ነባር ወደቦችን የማስፋፋት ሥራዎች ተከናውነዋል፤ የድርጅቱን አደረጃጀት በማሻሻል የመዋቅር ጥናት አጸድቆ እንዲተገበር አድርጓል:: እነዚህንና ሌሎች መሰል የተጀመሩ ጥረቶች ከግብ ለማድረስ ኢባትሎ በ2017 በጀት ዓመት የተለያዩ ኢላማዎችንና እነዚህን ዒላማዎች ለማሳካት የሚረዱ ዝርዝር ተግባራትን ለመፈፀም የሚያስችል ዕቅድ አዘጋጅቷል::

ይህ እቅድ ሲዘጋጅ ከአገራዊ የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ጋር በማዛመድ ከ2016 በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባር ላይ የሚውል የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ (2016 ዓ.ም እስከ 2020 ዓ.ም) መነሻ የተደረገ ሲሆን በዚሁ አግባብ የ2017 በጀት ዓመት የኦፕሬሽንና የፋይናንስ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በስራ አመራር ቦርድ እንዲጸድቅ ተደርጓል::

የኢትዮጵያ ባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ስራውን በጀመረበት ዓመት ዓመታት ብሎም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የነበረው አቅም ሲታይ መርከቦች የነበራቸውን ከሶስት ሺህ እስከ 18ሺ የመጫን አቅም እያሳደገ በመምጣት ከ28 ሺህ እስከ 63 ሺ ቶን የመጫን አቅም ያላቸው መርከቦች ባለቤት ለመሆን በቅቷል:: አሁን ላይ ድርጅቱ ስምንት የደረቅ ወደብና ተርሚናሎች አሉት፣ በተጨማሪ በቂ የወደብ መሳሪያዎች እና ብዙ ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎች ያሉት ሲሆን፤ ተደራሽነቱ እና ጭነት የማንሳት አቅሙም ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ መጥቷል::

**በዚህ ረገድ በተለይም በ2016 በጀት ዓመት በርካታ ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ደረጃ የተከሰቱ ችግሮች መኖራቸው ይታወቃል። እነዚህን ችግሮች በመቋቋም ከላይ የተዘረዘሩትን ስኬቶች ማስመዝገብ ችሏል**

በተጨማሪም ተቋሙ የአገልግሎት አድማሱን በማስፋትም የላቁ ውጤቶችን እያስመዘገበም ይገኛል:: ዛሬ ላይ እየሰጣቸው ያሉ የአገልግሎት አይነቶችንም ስንመለከት በኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ የሀገሪቷን ገቢና ወጪ ጭነቶች በብቸኝነት በማጓጓዝ ለአስመጪና ላኪዎች የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት የሚሰጥ መንግስታዊ ተቋም ነው:: ይህም ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ በግልጽ የሚያመላክት ነው።

**አዲስ ዘመን ፤- የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ የተቀመጠለትን ዓላማ ከማሳካት አኳያ በሰው ሀብት እና በሌሎች ግብአቶች ያለበት ሁኔታ እንዴት ይገለጻል ?**

**ዶ/ር በሪሶ ፤-** የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ከ 3000 በላይ ቋሚ ሰራተኞች ያሉት ሲሆን እነዚህ ከባሕር እስከ የብስ በላቀ ትጋትና በእረፍት የለሽም መንፈስ ስራቸውን የሚያከናውኑ ናቸው:: ተቋሙ እነዚህን ሰራተኞች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃትና በታማኝነት እንዲወጡ ለማስቻልም በየወቅቱ አስፈላጊውን ስልጠና፤ ድጋፍና ክትትል እያደረገ ይገኛል። በግብዓት ረገድም ቢሆን ኢባትሎ ከሀገራዊ ድርጅቶች ጋር በአንጻራዊነት ሲታይ በተሻለ ደረጃ ሆነው ከሚታዩት መካከል ነው ለማለት ይቻላል::

**አዲስ ዘመን ፤- የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ በዘርፉ ዓለም ከደረሰበት አኳያ ያለው አቅም እንዴት ይታያል ? ሌሎች ሀገራት ወደ ደረሱበት ደረጃ ለማሸጋጋር ምን እየተሰራ ነው ?**

**ዶ/ር በሪሶ፤-** በመሰረቱ የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ተወዳዳሪነቱና ተፎካካሪነቱ ሀገር ውስጥ ካሉ ድርጅቶች ጋር አይደለም:: ዓለም ዓቀፍ ዕውቅና ካተረፉት እንደ Maersk, Mediterranean Shipping Company (MSC), COSCO Shipping Corporation, CMA CGM Group እና Hapag-Lloyd ከመሳሰሉት ጋር ነው:: በእርግጥ እነዚህ በሰው በሃብት ኃይል አደረጃጀት፣ በሃብት ምጣኔ እና በአገልግሎት ስፋትም ከፍታ ላይ ያሉ ናቸው::

ይሁን እንጂ ብዙዎች በአህጉሪቱ ያሉ ስመጥር የመርከብ ድርጅቶች ከዘርፉ ተደነቃቅፈው እና በግዙፎቹ ተውጠው እንደመውጣታቸው የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሃብት የሆኑት መርከቦቻችን በብዙ ፈተናዎች ውስጥ አልፈው ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገራት የራሳቸውን ባንዲራ እያውለበለቡ በኩራትና በክብር 345 የወደብ መዳረሻዎች ላይ ማገልገል መቻላቸው እንደ ትልቅ ድል የሚቆጠር ነው:: ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ አቅሙ እንዲያድግና በስመጥርነቱ እንዲቀጥል የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቶ በቅርቡ በአገልግሎት ስፋትና በአሰራር ጥራት ላይ ተመስርቶ ወደ ልሕቀት ያመራ ዘንድ የሚያስችለው ሥራ እየተሰራ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን ፤- የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ዘርፍ ለሙስና ተጋላጭ እንደሆነ ይነሳል ይህንን ለመቅረፍ እንደ ተቋም ምን ምን ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ ?**

**ዶ/ር በሪሶ ፤-** የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ለሙስና ተጋላጭ ስለመሆኑ እንደሚነሳ አሁን ከእናንተ እየሰማን ነው:: በድርጅቱ ውስጥ ሥራዎች የሚከናወኑት ሕጋዊ መርህና አሰራር ተከትሎ ነው:: ይህም ሆኖ ለሙስና ሊያጋልጡ ይችላሉ ብለን የሰጋንባቸውን ከባቢዎች በዘመናዊ አሰራር ታግዘን (አሰራራችንን ዲጂታላይዝ) እየሰራን እንገኛለን:: ምንም እንኳ የዲጂታላይዜሽን ሥራችን በተወሰነ መልኩ ያልተጠናቀቀ እና በመጠናቀቅ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በአስጊ ደረጃ ለሙስና ተጋላጭ የሚያደርጉ አሰራሮች የሉም:: ይሁንና ሙስና በባህሪው ከሁኔታዎችና ከአሰራሮች ጋር የሚለዋወጥ በመሆኑ አሰራሮችን በማዘመንና ግልፀኝነት በማስፈን ሥራዎች እንዲከናወኑ ማድረግ ላይ በተቋሙ የሥነምግባር ክፍል አማካይነት የክትትልና የቁጥጥር ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

**አዲስ ዘመን፤- በቅርቡ የጭነት መርከቦች ግዢ እንደሚፈጸም ተገልጿል እነሱን ቢያብራሩልን? በተጨማሪ የእነዚህ መርከቦች ወደ አገልግሎት መግባት የሚኖረው ፋይዳና የሚያመጣው ለውጥ ቢገለጽ ?**

**ዶ/ር በሪሶ ፤-** የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ቀደም ሲል የመጫን አቅማቸው 27 ሺህ ቶን የሆነ ዘጠኝ መርከቦችና አንድ ዓባይ ሁለት የተሰኘች 63 ሺህ ቶን የምትጭን ግዙፍ አልትራማክስ መርከብ ባለቤት ነው:: አሁን ደግሞ በተያዘው የበጀት ዓመት ሁለት 62 ሺህ ቶን የመጫን አቅም ያለው አልትራማክስ መልቲፐርፐዝ መርከብ፣ ሁለት ከ 3000-4000 ቲኢዩ ኮንቴይነር የመጫን አቅም ያላቸው መርከቦች፣ እና ሁለት አልትራማክስ 63 ሺህ ቶን የሚጭኑ የደረቅ ጭነት መርከቦች በአጠቃላይ ስድስት መርከቦች ግዥ በሂደት ላይ ይገኛል:: እነዚህ ስድስት መርከቦች ወደስራ ሲገቡ አጠቃላይ የመርከቦቻችንን ቁጥር ወደ 16 ያደርሰዋል:: ይህ ማለት 94 በመቶ የሚደርሰውን የሀገሪቱ የወጪ ገቢ ጭነት ከማሳለጥ አኳያ ዓይነተኛ ሚና የመጫወት ዕድሉን ከፍ ያደርገዋል::

**አዲስ ዘመን ፤- የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ በቀጣይ እንደ አጠቃላይ ምን እቅድ ይዟል? መዳረሻውስ ምንድን ነው ?**

**ዶ/ር በሪሶ ፤-** ተወዳዳሪ የሺፒንግና የሎጀስቲክስ አገልግሎት በማቅረብ በ2022 ዓ.ም ተመራጭና ስመጥር አፍሪካዊ ተቋም የመሆን ራዕይን ይዞ እየሰራ ያለው ድርጅታችን በቀጣይ የዲጂታል አሰራርን ሙሉ በሙሉ መተግበር የመርከቦቹን እና የከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎቹን ቁጥር መጨመር፣ የሀገር ውስጥ ወደብና ተርሚናሎችን ማዘመን እና ማስፋፋት፣ የተሽከርካሪዎቹን እና የወደብ መሳሪያዎችን ቁጥር መጨመር እና ዓለም አቀፍ ተደራሽነቱን ማስፋት ለአብነት የሚጠቀሱ ቀጣይ ዕቅዶቹ ናቸው::

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

# ከወርቅ ወርቅ...

በሩብ ዓመቱም ከወርቅ የወጪ ንግድ ከ500 ሚሊዮን ዶላር በላይ መገኘቱን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በበጀት ዓመቱ ከወርቅ ብቻ እስከ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት መታቀዱ መገለጹም ይታወቃል፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በወርቅ ላይ ለታየው የገቢ ለውጥ አስተዋጽኦ ማድረጉን የዘርፉ ባለሙያዎች ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ከሚላክ ወርቅ ለማግኘት ያቀደችውን ለማሳካት በርካታ ሥራዎች መሠራት እንደሚኖርባቸው ያመላክታሉ፡፡

የሥነ ምድር ተመራማሪው (ጂኦሎጂስቱ ) አቶ ሳዲቅ ከቢር የወርቅ ዋጋ ከውጭ ምንዛሪ ጋር አብሮ እንደሚሄድ ጠቅሰው፤ በውጭ ምንዛሪ ላይ የተደረገው ማሻሻያ ወደ ብሄራዊ ባንክ የሚገባውን የወርቅ ምርትንም ሆነ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ቀደም ሲል ከነበረው በእጥፍ እንዲጨምር ማድረጋቸውን ይገልጻሉ፡፡ በመንግሥት በኩል በወርቅ የኮንትሮባንድ ንግድ ላይ እየተወሰደ ያለው ሕጋዊ እርምጃና ቁጥጥር መጠናከሩ ሌላኛው ምክንያት መሆኑን አንስተዋል፡፡

በተለይ ብሔራዊ ባንክ ያደረገው ማበረታቻ ብዙ ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ እንዲገባ ማድረግ ማስቻሉን ገልጸው፣ ባንኩ ወርቅ ለሚያቀርቡ አካላት ያደረገው ማበረታቻ ብዙዎች ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ እንዲያስገቡ የሚያተጋ ነው ይላሉ፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ወደ ብሄራዊ ባንክ የሚገባው ወርቅ መጠን እንዲጨምር ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል ያሉት አቶ ሳዲቅ፤ እርምጃው በሀገሪቱ ያለው የወርቅ ዋጋ ከጎረቤት ሀገራት ሳይቀር የተሻለ እንዲሆን ሳያደርገው እንዳልቀረም ያብራራሉ፡፡

አሁን ከጎረቤት ሀገራት ሳይቀር ወርቅ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ስለመኖራቸው አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያመላክቱ ይገልጻሉ፡፡

መንግሥት በወርቅ ላይ የሚፈጸመውን ህገወጥ ንግድ ለመቆጣጠር ወርቅ አምራች በሆኑ ክልሎች ግብረ ኃይል በማቋቋም ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ እርምጃ ሲወስድ መቆየቱን ይገልጻሉ፡፡ ክልሎችም ባህላዊና አነስተኛ ወርቅ በሚያመርቱ ማህበራት ላይ ግዴታ ማስቀመጣቸውን አቶ ሳድቅ ጠቁመዋል፡፡

አንድ ማህበር በዓመት ምን ያህል ወርቅ ማስገባት አለበት የሚለው የወርቅ መጠን እንደ ግዴታ የተቀመጠ መሆኑን ጠቅሰው፤ ማህበራቱ ይህንን ግዴታቸውን እንዲወጡ ክትትልና ቁጥጥር እያደረጉ መሆናቸውን ያመላክታሉ፡፡

‹‹አሁን ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን በእጥፍ መጨመሩ የምርት መጠን ከመጨመሩ ጋር የተያያዘ አይደለም›› ሲሉም አመልክተው፣ ወርቅ እየተመረተ በህገ ወጥና በኮንትሮባንድ ንግድ ሳቢያ ምርቱ ወደ ውጭ ሲወጣ እንደነበር ጠቁመዋል፡፡ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው፣ የግብረ ኃይሉ ቁጥጥር እና ክልሎች ያስቀመጡት ግዴታ ለብሄራዊ ባንክ የሚቀርበውን የወርቅ ምርት በእጥፍ እንዲጨምር ማድረጋቸውን አስታውቀዋል፡፡

በወርቅ ላይ እየተከናወኑ ያሉ ተግባሮች ዘንድሮ ከወርቅ ወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) ለማግኘት የታቀደው ሁለት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት እንደሚያስችልም አቶ ሳድቅ አስታውቀዋል፡፡ ‹‹በኢትዮጵያ የወርቅ ምርት ችግር የለም፤ ክምችቱም በደንብ አለ፤ በደንብ ከተሰራና ቁጥጥሩ ተጠናክሮ ከቀጠለ ከታቀደው በላይ ሊገኝ ይችላል›› ነው ያሉት፡፡

በሌላ በኩል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በጋምቤላ ክልል የተገነባውን የወርቅ ፋብሪካ መርቀው በከፈቱበት ወቅት፤ ፋብሪካው የወርቅ ምርት በእጥፍ እንዲጨምር እንደሚያደርግ ጠቅሰው፤ ሌሎችም ወርቅ በከፍተኛ ደረጃ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ወደ ሥራ ሲገቡ ከታቀደው በላይ ገቢ ለማግኘት እንደሚረዳ አመላክተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በባህላዊና በአነስተኛ አምራቾችም የሚመረተው የወርቅ መጠን ቀላል የሚባል አይደለም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በተለይ ከፍተኛ አቅም ያላቸው አካላት በወርቅ ልማት ላይ እንዲሰማሩ ቢያደርግ በወርቅ ኤክስፖርት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን ማስገኘት እንደሚቻል ጠቅሰው፤ በወርቅ አምራቾች ላይ የሚደረገው ቁጥጥርና የሚሰጠው ማበረታቻ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

ወርቅ ከእስከ አሁኑም በላይ ብዙ የውጭ ምንዛሪ እንደሚገኝበት ተናግረው፣ መንግሥት ፈቃድ በተሰጣቸው አካላት ላይ ጭምር ጥብቅ ቁጥጥር ቢያደርግ ከዚህም በላይ ምርት ማግኘት እንደሚቻልም አመልክተዋል፡፡

የወርቅ ማእድን ከሚቆፈርበት ቦታ ጀምሮ ባሉ ሰንሰለቶች ላይ የሚደረገው ጥብቅ ቁጥጥር ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አቶ ሳዲቅ ያስገነዝባሉ፡፡ ‹‹እንደ ሀገር ከወርቅ እየተጠቀምን ነው ማለት አይቻልም፡፡ አሁን ካለው አምቅ አቅም 50 በመቶ ያህሉ ብቻ ነው እየተመረተ ያለው፡፡ 70 እና 80 በመቶ ቢመረት ብዙ መጠቀም እንችላለን›› ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሥነ ምድር ትምህርት ክፍል ዳይሬክተር አሸብር ሰውአለ (ዶ/ር) ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን ሊጨምር እንደሚችል ጠቅሰው፣ ለእዚህም ብዙ ምክንያቶችን መጥቀስ እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡ ከምክንያቶቹ መካከል የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው፣ ሕገ ወጦችን ለመቆጣጠር እየተሰራ ያለው ሥራ እና በጸጥታ ምክንያት አንዳንድ አካባቢዎች ሥራ አቁመው የነበሩ አምራቾች ወደ ሥራ መመለሳቸው እንደሚጠቀሱ ተናግረዋል፡፡

ወርቅ በከፍተኛ ደረጃ ሊያመርት የሚችል አዲስ የወርቅ ፋብሪካ ሥራ መጀመሩና ሌሎች በቅርቡ የሚጀምሩ መኖራቸው ሌሎች ምክንያቶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ከጸጥታ ጋር በተያያዘ ከሚጎዱ ዘርፎች መካከል አንዱ ማዕድን ነው የሚሉት አሸብር (ዶ/ር)፣ አብዛኞዎቹ ማዕድን የሚወጣባቸው አካባቢዎች ከዚሁ ከጸጥታ ጋር በተያያዘ ችግር እንዳለባቸው ጠቅሰው፤ ይህ ችግር እንዲፈታ መስራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

በመንግሥት በኩል ማዕድን የሚገኝባቸውን ቦታዎች ሰፊ ጥናትና ምርምር በማድረግ መለየትና ለኢንቨስትመንት ምቹ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ በዘርፉ ግልጽ የሆነና የተረጋጋ የሕግ ማሕቀፍ ሊኖር እንደሚገባም አመላክተዋል፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያ ለውጭ ገበያ የሚቀርበው የወርቅ መጠን በእጥፍ እንዲጨምር ከማድረግ በዘለለ የማዕድን ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል የሚሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ ሕገ ወጥነትን በመከላከል ረገድ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ከተደረገ ለውጭ ገበያ ከሚቀርበው ወርቅ የታቀደውን የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት ያስችላል ነው ያሉት፡፡

የማዕድን ሚኒስቴር መረጃ እንደጠቆመው፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የማዕድናት ምርታማነትን በተለይ የወርቅ ምርትን በከፍተኛ ሁኔታ እያሳደገ ነው። ማሻሻያው በአነስተኛ ደረጃ ይመረት የነበረውን የማዕድን ምርት በከፍተኛ መጠን እያሳደገው ነው፤ በተለይም የወርቅ ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ እያሳደገ ይገኛል፡፡

ሚኒስቴሩ በተያዘው በጀት ዓመት ስምንት ነጥብ ስድስት ቶን ወርቅ ለማምረት አቅዶ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ብቻ የእቅዱን 70 በመቶ ማሳካት ችሏል፡፡ ማሻሻያው የማዕድናት አምራቾችን ተጠቃሚ በማድረጉ አምራቾቹ የተሻሉ ማሽነሪዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ገዝተው ወደ ምርት ሥራ እየገቡ ናቸው።

በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ወደ ብሄራዊ ባንክ የሚገባው ወርቅ መጠን ጨምሯል፤ በሩብ ዓመቱ ባለፈው በጀት ዓመት ዓመቱን ሙሉ ወደ ባንኩ ከገባው አራት ቶን በእጅጉ የላቀ ሰባት ቶን ወርቅ መግባቱ ይታወቃል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ብቻ አምስት መቶ ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን አስታውቀዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ወርቅ ላይ ከፍተኛ ሥራዎች ሲሰሩ መቆየታቸውን ጠቅሰው፣ በ2017 በጀት ዓመት ከወርቅ ብቻ እስከ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት መታቀዱንም ጠቁመዋል፡፡



## በአምስቱ አውሮፕላኖች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ኢኮኖሚዋ የተደገፈው ግብርና ላይ ነው፡፡ ይሁንና የአንበጣ መንጋ፣ የግሪሳ ወፍ እና መሰል ችግር ሲያጋጥም በቶሎ ለመከላከል የሚያስችል ጻረ ተባይ ኬሚካል ርጭት የሚያከናውን አውሮፕላን የሌላት እንደነበረች ገልጸው፤ አውሮፕላኑን ከሌላ ሀገር ማስመጣቱ ሌላ ተጨማሪ ወጪ ሲያስወጣ የቆየ ነበር ብለዋል፡፡

ይሁንና ለኬሚካል ርጭት የሚያስፈልገውን አውሮፕላን ለማግኘት ብዙ ወጪ እያወጡ ሌላ ሀገር ሔዶ ማምጣቱ አዋጭ ባለመሆኑ አውሮፕላኖችን ለመግዛት ችለናል ያሉት የግብርና ሚኒስትሩ፤ የተገዙትም ዘመናዊ የሆኑ አምስት አውሮፕላኖች በአሁኑ ወቅት ለሚደርሰው ችግር በቀላሉ መጠቀም እያስቻሉ በመሆኑ እፎይታን ማስገኘታቸውን አመልክተዋል፡፡

እንደ ግርማ (ዶ/ር) ገለጻ፤ አውሮፕላኖቹ በተገዙ ወቅት ከኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር በመሆን ሥራ ካስጀመሯቸው በኋላ ከግብርና ሚኒስቴር ሥራ ባለፈ ለንግድ አገልግሎት ሁሉ መዋል እንዲችሉ ተደርገዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ በቅርቡ የምርጥ ዘር ድርጅቶች የኬሚካል ርጭት አካሂደውበታል፡፡

አውሮፕላኖቹ ሌሎችንም ተዛማጅ ሥራዎችን እየሠሩ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ በአሁኑ ወቅት ደግሞ የአየር ንብረቱ እንደሚያመላክተው ከፍተኛ ተባይ የሚፈጠርበት ወቅት ነውና አውሮፕላኖቹ በመኖራቸው ኢትዮጵያም ለዚያ ራሷን አዘጋጅታለች ማለት ነው ብለዋል፡፡ ኢትዮጵያ ከዚህ አኳያ የራሷን አቅም የፈጠረች በመሆኑ ይህም እንደ አንድ ቴክኖሎጂ የሚታይ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ከሜካናይዜሽን፣ ከግብዓት፣ ከምርጥ ዘር አቅርቦት አጠቃላይ ከሰብል ጥበቃ አንጻር ግብርናውን ለማዘመን የሚያግዙ የቴክኖሎጂ አቅርቦቶች ለማሟላት እየተሰሩ እንደሚገኙ አመልክተው፤ ይህ ግን በቂ አይደለም፤ እያደገ መሔድ አለበት፡፡ ይሁንና ጅምሩ መልካም የሚባል ነው በማለት ግርማ (ዶ/ር) ገልጸዋል።

ግብርና ሚኒስቴር፣ በአንበጣ መንጋ እና በግሪሳ ወፍ አማካይነት በሰብል ምርት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመከላከል የሚያስችሉ አምስት አውሮፕላኖችን ከገዛ ወራት መቆጠሩ የሚታወስ ነው፡፡ በወቅቱ አውሮፕላኖቹ የሰደድ እሳትን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባር ላይ እንደሚሰማሩ መነገሩ ይታወሳል፡፡

## በዓሉ ጥቃቅን ልዩነቶችን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አሳምሮ በማጠናቀቅ ለበዓሉ ዝግጁ እንዲሆን መደረጉን አስረድተዋል፡፡

በዓሉን ለማክበር አንድ ዓብይ ኮሚቴ እና ስምንት ንዑሳን ኮሚቴዎች መቋቋማቸውን የገለጹት አቶ ጥላሁን፤ ከንዑሳን ኮሚቴዎች አንዱ የሆነው የሰላምና የጸጥታ ንዑስ ኮሚቴ የሰላሙን ጉዳይ ከማህበረሰቡ ጋር በመተባበር እንግዶች በሰላም በዓሉን አክብረው እንዲመለሱ በቂ ዝግጅት ማድረጉን ጠቁመዋል፡፡

የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ትልቁ ትሩፋት የመሰረተ ልማቶችን ሥራ እና የልማት እንቅስቃሴዎችን የሚያነቃቃ እንዲሁም ፖለቲካዊ ስኬቶችን ይበልጥ የሚያጎላ መሆኑ ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በዓሉ በተለያዩ ዝግጅቶች ሲከበር ከሀገር ውስጥ እንግዶች በተጨማሪ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች አከባበሩን እየጎበኙ በመሆኑ ለቱሪዝም ዘርፉ ትልቅ መነቃቃትን የሚፈጥር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በኢኮኖሚው ዘርፍም የተከፈተው የንግድ ትርዒትና ባዛር በኢትዮጵያ የተመረቱ ምርቶችን በማቅረብ ረገድ ለአምራቹ ገበያ በመፍጠር ትልቅ እድል የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ጥላሁን ገለጻ በዓሉ ከታህሳስ 25 ቀን ጀምሮ በተለያዩ ኩነቶች በክልሉ መከበር ጀምሯል፡፡ ታህሳስ 25 "የወንድማማችነት ቀን" በማለት በአርባ ምንጭ ከተማ ታላቁ ሩጫ እና የህብረት ስፖርት መደረጉን አውስተው፤ ታህሳስ 26 "የአብሮነት ቀን" በሚል ስያሜ ከ32 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ያሉት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልልን ባህል እና እሴቶች የሚያሳይ ኤግዚቢሽን መከናወኑን አውስተዋል፡፡

ትናንት ታህሳስ 27 "የደቡብ ኢትዮጵያ" ቀን ስያሜ ተሰጥቶት ነጠላ ትርክትን አስወግዶ ገዢ ትርክትን ከማስረጽ አኳያ ተግባቦት ላይ ባተኮሩ በተለያዩ ሁነቶች እንደተከበረ የጠቆሙት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ዛሬ ታህሳስ 28 "የምክክር ቀን" ህገ መንግስቱ ስላበረከታቸው ትሩፋቶች ሲምፖዚየም ተከናውኖ ታህሳስ 29 ቀን መላው የብሔር ብሔረሰቦች ተወካዮች በተገኙበት "የኢትዮጵያ ቀን "በሚል ስያሜ ይከበራል ብለዋል፡፡

በዓሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሰብሰብ ብለው በአንድነት ስለ ሀገራቸው የሚወያዩበት "ብሔራዊ መግባባት ለሕብረብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል የሚከበር ትልቅ በዓል ነው ያሉት አቶ ጥላሁን፤ በዓሉን አስመልክተውም ለመላው ኢትዮጵያውያን እንኳን አደረሳችሁ ብለዋል፡፡

## "የሕዝቡ ስቃይ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መስዋዕትነት እየከፈለ ነው ብለዋል፡፡

የሰላም ስምምነቱ ለሕዝቡ እፎይታን እንደሚያስገኝ ገልጸው፤ ስምምነቱን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ የድርሻቸውን እንደሚወጡና ለተግባራዊነቱም ሦስት ኮሚቴዎች መቋቋማቸውን ጠቁመዋል፡፡

ሕዝብ ከጦርነት ይልቅ ከሰላም አትራፊ መሆኑን ጠቅሰው፤ የፖለቲካ ልዩነቶችን በውይይት መፍታት የሰለጠነ መንገድ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የሰላም ስምምነቱን አስመልክተው በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ እየተሰራጩ ያሉ አሉባልታዎች መሠረተ ቢስ መሆናቸውን የገለጹት ጃል ሰኚ፤ የሰላም አማራጭን የወሰዱት የሕዝቡን ጥያቄ ለመመለስና ሰላምን በመምረጣችን ነው ብለዋል፡፡

አሁን ወደ ካምፕ እየገባ ያለው የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት መሆኑን ጠቅሰው፤ አሉባልታውን ከሚያሰራጩት አካላትም እንዴት ወደ ሰላም መመለስ እንደሚችሉ ጥያቄ እየቀረበላቸው መሆኑንም አንስተዋል፡፡

የወደሙ መሠረተ ልማቶችን በጋራ መልሶ መገንባት እና ቅራኔ የተፈጠሩባቸውን አካባቢዎችም ማስታረቅ የስምምነቱ አካል መሆናቸውንም ጠቁመዋል፡፡

በሰሞኑ ቆይታቸውም በአዲስ አበባ እና በተለያዩ አካባቢዎች የተሠሩ የልማት ፕሮጀክቶችን መጎብኘታቸውን ያነሱት ጃል ሰኚ፤ የተጀመሩ የልማት እንቅስቃሴዎች መልካም መሆናቸውን እና ከዚህ በተሻለ መሥራት እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በመግለጫውም ሌሎች የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት አመራሮች የተገኙ ሲሆን፤ ባለፈው እሁድ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ እና የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት አመራር በነበሩት ጃል ሰኚ ነጋሳ መካከል የሰላም ስምምነት መፈረሙ ይታወሳል።

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

**ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአሥራ አምስት ቀኑ ቅዳሜ የሚታተም**

# ሀገር አቀፍ ትኩረት የተሰጠው የወባ በሽታ

**ሔርሞን ፍቃዱ**

የወባ በሽታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሕብረተሰብ ጤና ችግር መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ጤና ሚኒስቴር በሀገር አቀፍ ደረጃ ትኩረቱን በወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር እንዲሁም በመጀመሪያ ጤና እንክብካቤ ላይ ያደረገ የተቀናጀ ድጋፋዊ ክትትልና ምልከታ እያካሄደ ይገኛል፡፡

በጉዳዩ ላይ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በበይነ መረብ መደበኛ ውይይት አድርገዋል። በውይይቱ ላይ የተቀናጀ ድጋፋዊ ክትትልና ምልከታ የሚያከናውኑ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች የሚመሩ ቡድኖች መቋቋማቸው የተጠቆመ ሲሆን፤ ድጋፋዊ ክትትሉ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚካሄድ ይሆናል፡፡ በዚህ ድጋፋዊ ክትትል የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና የተጠሪ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ተሳታፊ እንደሆኑ ተገልጿል፡፡

ድጋፋዊ ክትትልና ምልከታው በዋናነት በወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር፣ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና እንክብካቤ፣ የግብዓት አቅርቦት እና የተቀናጀ የአካባቢ ቁጥጥር እንዲሁም የቅኝትና ምላሽ አሰጣጥ ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ የጤና ሚኒስትሯ ዶ/ር መቅደስ ዳባ ተናግረዋል። ድጋፋዊ ክትትሉም በትኩረት እንደሚሠራ እና በዳሰሳ ለተገኙት ግኝቶች ከክልሎች ጋር በመቀናጀት አስፈላጊው ምላሽ እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡

ድጋፋዊ ክትትሉና ምልከታው ለሁለት ወር ያህል በክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች እና ጤና ኬላዎች እንዲሁም እስከ ታችኛው ማህበረሰብ ድረስ የሚካሄድ ሲሆን፤ በዳሰሳው ግኝት መሰረት በየደረጃውና በአጠቃላይ መድረኮች ላይ የማጠናከሪያ ግብረ መልሶች እንደሚሰጥ ሚኒስትሯ ጠቁመዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር አየለ ተሾመ የሚመራ የከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ቡድን የተቀናጀ ድጋፍዊ ጉብኝት ለማድረግ የሚያስችል ውይይት ከኦሮሚያ ጤና ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ጋር አካሂዷል።

በውይይቱ ሚኒስትር ዴኤታው ዶ/ር አየለ እንዳሉት፤ ድጋፋዊ ክትትሉና ምልከታው በዋናነት ትኩረቱ ወቅታዊ የወባ ወረርሽኝ መከላከልና መቆጣጠር ሥራውን አስመልክቶ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችን፣ ወረርሽኙን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ ጤና እንክብካቤ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በአካል ተገኝቶ ቅኝት በማድረግ ምላሽ ለመስጠት እንደሆነ አስታውቀዋል። በተጨማሪም ምልከታው በወባ ወረርሽኝ መከላከል ላይ ንቅናቄ በመፍጠር ወረርሽኙን መቆጣጠር የሚያስችል ቅንጅታዊ አሠራሮችን ለመፍጠር እንደሚያግዝ ጠቁመዋል።

የኦሮሚያ ጤና ቢሮ ኃላፊ ፕሮፌሰር ነፃነት ወርቅነህ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ እንደ ኦሮሚያ ክልል የወባ በሽታ ወረርሽኝ መከላከልና መቆጣጠር ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተከናወነ ነው። ሆኖም አሁንም ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ገልፀው፤ ድጋፍ የሚያደርግ ቡድን በጤና ሚኒስቴር በኩል ተዋቅሮ ወደ ክልል መውረዱ እንዳስደሰታቸው ገልፀዋል።

ምልከታው በክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች እና ጤና ኬላዎች እንዲሁም እስከ ታችኛው ማህበረሰብ ድረስ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

በዚህም መሰረት በጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር አየለ ተሾመ የሚመራ የከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ቡድን በአራት ክልሎች ማለትም በኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች የተቀናጀ ድጋፍዊ ጉብኝት እንደሚያደርግ ተጠቁሟል።

በድጋፋዊ ቡድኑ የጤና ሚኒስቴር ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የተጠሪ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ተሳታፊ እንደሚሆኑ የተገለፀ ሲሆን፤ ክልሎቹ ይህን አውቀው ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ጥሪ ቀርቧል።

በጤና ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራሮች የሚመሩ ድጋፋዊ ቡድኖች ተቋቁመው በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ድጋፋዊ ጉብኝት ማድረግ መጀመራቸው ተመላክቷል።

በጤና ሚኒስትር ዴኤታ በወይዘሮ ፍሬሕይወት አበበ የሚመራ የተቀናጀ ድጋፍና ክትትል ቡድን በሲዳማ ክልል ሥራውን እንደጀመረ ታውቋል። በሚኒስትር ዴኤታዋ የሚመራ የተቀናጀ ድጋፋዊ ክትትል ቡድን ከሲዳማ ክልል ጤና ቢሮ እና ከተጠሪ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ጋር አጠቃላይ ስለድጋፋዊ ክትትሉ ዓላማና አካሄዱን አስመልክቶ ውይይት አድርጓል።

የተቀናጀ ድጋፋዊ ክትትልና ምልከታ የሚያደርገው የጤና ሚኒስቴር ልዑክ ቡድኑ በሲዳማ ክልል ሥር በሚገኙ አራት ዞኖች፣ አራት ወረዳዎች፣ አራት ሆስፒታሎች፣ ስምንት ጤና ጣቢያዎች እና ስምንት ጤና ኬላዎች እንዲሁም እስከ ነዋሪው ህብረተሰብ ድረስ በመውረድ በክልሉ በበጀት ዓመቱ እስካሁን በተለይ የወባ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተሠሩ ሥራዎችን ምልከታ እንደሚያደርግ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገልጸዋል።

የተቀናጀ ድጋፋዊ ክትትል ቡድኑ በመስክ ምልከታው የወባ መከላከልና ቁጥጥር፣ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና እንክብካቤ አሃድ፣ የሥራ ሁኔታ፣ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶችንና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦትና አያያዝ እንዲሁም የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አተገባበር ላይ ምልከታ እንደሚያደርግ ሚኒስትር ዴኤታዋ ወይዘሮ ፍሬሕይወት አበበ ተናግረዋል።

የሲዳማ ክልል ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ሰላማዊት መንገሻ በበኩላቸው ባስተላለፉት መልዕክት፤ የጤና ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራሮች እና ከፍተኛ ባለሙያዎች በክልሉ በየጊዜው እየተገኙ የሚያደርጉት ድጋፍና ክትትል የሚደነቅና እንደ ክልል ውጤታማ የሆነ ሥራ እንዲሠራ በእጅጉ የሚያግዝ እንደሆነ ገልጸዋል።

ቡድኑ በክልሉ ከሚያደርገው ድጋፍና ምልከታ ተነስቶ ማጠናከሪያ ግብረ መልሶችን በየደረጃው እና በማጠቃለያ መድረክ የሚሰጥ ይሆናል ብለዋል ዶ/ር ሰላማዊት።

የጤና ሚኒስቴር እና የተጠሪ ተቋማት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተካተቱበት የተቀናጀ ድጋፍና ክትትል ቡድኖች በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወደ ሥራ እየገባ ነው፡፡

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ከጥቃቅን ንግድ ወደ ሆቴል ኢንቨስትመንት

ፍሬሕይወት አወቀ



አቶ ወላንሳ ኤንጋሞ

ለቤተሰቡ ስድስተኛ ወንድ ልጅ ናቸው:: አባታቸው ሴት ልጅ እየጠበቁ እያሉ ነው እሳቸው ይህችን ምድር የተቀላቀሉት:: ይህም ለአባታቸው ጥሩ ዜና አልነበረም:: ሁኔታው እናትና ጨቅላውን ከቤት አስከመውጣት አደረሳቸው::

እናታቸው እቅፍ እንዳሉ ከወላጅ አባታቸው ቤት የተባረሩትና አጎታቸው ዘንድ ለማደግ የተገደዱት የዕለቱ እንግዳችን አቶ ወላንሳ ኤንጋሞ ይባላሉ:: በወቅቱ ያጡትን ፍቅር፣ እንክብካቤና ድጋፍ ለማግኘት እንዲሁም በራሳቸው ለመቆም በብዙ ተንገዳግደዋል:: በብዙ መንገዳገዳቸውም ብርቱና ጠንካራ እንዲሆኑ አግዟቸዋል:: ለዚህም ነው ‹‹ትናንት መገፋቴ ዛሬ ለደረስኩበት ደረጃ መሠረት ጥሎልኝ አልፏል›› በማለት ትናንትናቸውን “በኩራት የሚናገሩት::

ከልጅነት እስከ ዕውቀት በብዙ ትግልና ውጣ ውረድ ያለፉት አቶ ወላንሳ፤ በሲዳማ ክልል ሸበዲኖ ወረዳ ሆርሶ ቀበሌ ነው የተወለዱት:: ከወላጅ እቅፍ ወጥተው በማደጋቸው ትምህርት ቤት ለመሄድ አልታደሉም:: ‹‹ከትምህርት ያጣሁትን ዕውቀት በሕይወት ውጣ ውረድ አግኝቼያለሁ›› የሚሉት አቶ ወላንሳ፤ ሥራ ሳይንቁ የሚሠሩ ጠንካራ ሠራተኛ መሆናቸውን ያስረዳሉ::

የዕድሜ እኩዮቻቸው ወደ ትምህርት ቤተ ሲሄዱ እርሳቸው ገንዘብ ማግኘት የሚችሉበትን መንገድ ያነፈንፉ ነበር:: ገና በለጋ ዕድሜያቸው ጀምረው በሥራ የተጉት አቶ ወላንሳ፤ ከወጣትነት ዕድሜያቸው ጀምረው አሁንም ድረስ ኑሯቸውን በሲዳማ ሰሜናዊ ዞን ሃዋሳ ዙሪያ ወረዳ ዶሬ ባፈኖ ከተማ አድርገዋል:: ኑሮን ለማሸነፍ የተለያዩ ሥራዎችን ሠርተዋል፤ ፍላጎታቸው ዕለት ዕለት እያደገ ሲመጣ ፍጥነት ጨምረው ከላይ ታች ብለዋል:: በወቅቱም በሃዋሳ ከተማ ዙሪያ በተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውረው ሠርተዋል::

የመጀመሪያውን የንግድ ሥራቸውንም በሃዋሳ ዙሪያ ሸመና ከተማ በማድረግ የንግድ ሥራን ተቀላቅለዋል:: የንግድ ሥራን ‹‹ሀ›› ብለው ሲጀምሩ ቡና በትከሻቸው ተሸክመው ረጅም ርቀት በመጓዝ ነው:: ቡና ከሸበዲኖ ወረዳ እየገዙ በትከሻቸውና በእህያ ጭነው ከተማ ወስደው ይሸጡ እንደነበር ያስታውሳሉ::

ከቡና ቀጥለው በቆሎ ነግደዋል:: ቡና አላዋጣ ሲል በቆሎ፤ በቆሎም ደከም ሲል ወደ ቡና መለስ ቀለስ እያሉ በትከሻቸው፣ በአህያና ከፍ ሲል በመኪና ጭምር ከቦታ ቦታ አዘዋውረው ነግደዋል::

አቶ ወላንሳ፤ የቡና ንግድን በጨው ቁምጣ እየሰፉ በትከሻቸው ተሸክመው ብዙ ኪሎ ሜትሮችን በእግራቸው ተጉዘዋል:: ይሁንና የቡና ንግድን ከመጀመራቸው አስቀድሞ ሳንቡሳ ከመሸጥ ጀምረው ትናንሽ የሚባሉ ማንኛውንም ሥራ ሳይንቁ ሠርተዋል:: ሳንቡሳ ከመጥበስ ጀምሮ ጨው፣ ሸንኮራና በሎቄ ሲሸከሙና በችርቻሮ ሲሸጡ እንደነበር አስታውሰው፤ ከልጅነት እስከ ዕውቀት በብዙ ልፋትና ትጋት በሥራ እንዳደጉና በሀቅ ሠርተው ዛሬ ላይ እንደደረሱ ይናገራሉ::

በአህያ የተጀመረው የበቆሎ ንግድ ቀስ በቀስ በመኪና አለፍ ሲልም የግላቸው አይሱዙ በመግዛት እራሳቸው ሹፌር በመሆን በቆሎ ከቦታ ቦታ ኦሮሚያ ክልል ድረስ ተጓጉዘው ነግደዋል:: ችግርን ተቸግረው፤ ርሃብን ተርበው፤ ያደጉና መከራን ማሸነፍ የቻሉ ናቸው::

ከሲዳማ ክልል ባለፈ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች ቡና እንዲሁም በቆሎ ሲነግዱ የኖሩት አቶ ወላንሳ በዚህ ሁኔታ የተጀመረው ንግድ አዋጭ እየሆነ የመጣላቸው ሲሆን፤ ‹‹ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል›› እንደሚባለው አንድ ሁለት እያሉ የንግድ ሥራቸውን አስፋፉ::

ከቡና እና በቆሎ ንግዳቸው ጎን ለጎን በሆቴል ኢንቨስትመንት በመሰማራት በሃዋሳ ዙሪያ ወረዳ ዶዮ ጨሌ ከተማ አነስተኛ ሆቴል ከፈቱ:: የሆቴል ሥራቸውን አጠናክረው በመቀጠል በ2007 ዓ.ም በሃዋሳ ከተማ ሌላ ሆቴል ጨመሩ::

የሆቴል ገበያው ቀዝቀዝ ሲል ቀድመው ወደሚያውቁት ቦታ ሃዋሳ ዙሪያ ወረዳ ዶሬ ከተማ እንዲሁም ሸመና ከተማ ላይ በስማቸው የተሰየሙትን ወላንሳ ሆቴሎች ከፍተው ቤተሰባቸውን መምራት ችለዋል:: በአካባቢው ታዋቂ ከሆኑት ወላንሳ ሆቴሎች

**ከቡና እና በቆሎ ንግዳቸው ጎን ለጎን በሆቴል ኢንቨስትመንት በመሰማራት በሃዋሳ ዙሪያ ወረዳ ዶዮ ጨሌ ከተማ አነስተኛ ሆቴል ከፈቱ:: የሆቴል ሥራቸውን አጠናክረው በመቀጠል በ2007 ዓ.ም በሃዋሳ ከተማ ሌላ ሆቴል ጨመሩ**

በተጨማሪ በሃዋሳ ከተማ የህንጻ መሣሪያ አቅራቢም ናቸው::

በሕይወት መውጣትና መውረድ ውስጥ ያጋጠማቸውን ፈተና ሁሉ ተጋፍጠው ማለፍ የቻሉ ናቸው:: መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲሉ ከልጅነት እስከ ዕውቀት ሥራ ሳይመርጡ በመሥራት በሥራ አድገዋል:: በዚህም ኑሯቸውን አሻሽለዋል:: ከራሳቸው አልፈው ልጆቻቸውን ጨምሮ ለሌሎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ለአካባቢው ማህበረሰብ አርዓያ ሆነዋል::

በአሁኑ ወቅትም ልጆቻቸው የሚሠሩበት የህንጻ መሣሪያን ሳይጨምር በሁለቱ ወላንሳ ሆቴሎች ብቻ 60 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል:: አቶ ወላንሳ፤ በሥራ የሚያምኑ ጠንካራ ሠራተኛ ሲሆኑ፤ ከጠንካራ ሠራተኝነታቸው ባሻገር በአካባቢያቸው አንቱ ከተባሉ የሀገር ሽማግሌዎች መካከል ተጠቃሽ ናቸው::

እርሳቸው እንዳሉት፤ በደረሱበት ቦታ ሁሉ አንድ ዐሻራ አስቀምጠው መውጣት ያስደስታቸዋል:: በተለይም ኃይማኖታዊ አስተምሮን በመከተል ሰዎች ህብረት እንዲፈጥሩና አንድ ሆነው ጊዜ፣ ጉልበትና አቅማቸውን ሁሉ በመልካም ሥራ ላይ እንዲያውሉ የማስተባበር ሥራ በመስራታቸው ውጤታማ ሆነዋል::

ይህም ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ ከሚሠሯቸው በጎ ሥራዎች መካከል ተጠቃሽ ሲሆን፤ በትውልድ አካባቢያቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲገነባ ምክንያት ሆኗቸዋል:: ትምህርት ቤቱ እንዲገነባ ጥቂት የአካባቢውን ማህበረሰብ አባላት በማስተባበር በኃላፊነት ይሠራሉ:: ለዚህም አደናቅሬ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲገነባ ያደረጉት አስተዋጽኦ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም::

በአሁኑ ወቅትም ትምህርት ቤቱ 600 የሚደርሱ ተማሪዎችን የሚማሩበት ሲሆን፤ ትምህርት ቤቱ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የቀለም ትምህርት የሚሰጥበት ነው፤ ህጻናት የነገ ሀገር ተረካቢ እንደመሆናቸው ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ በሥነምግባር ታንጸው እንዲያድጉ ጽኑ ፍላጎት አላቸው:: ልጆች በጥሩ ሥነምግባር ካደጉ የምንሰራት ሀገር ሰላማዊ እንደምትሆን ያምናሉ::

ለዚህም ነው ቀን ከሌት ከመደበኛ ሥራቸው በተጨማሪ በማህበራዊ ጉዳዮች የነቃ ተሳትፎ የሚያደርጉት:: በተለይም የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተስማምተው በጋራ በሚኖሩባት ሲዳማ ክልል ውስጥ ሰላም እንዲፈጠር ሰዎች በጋራ ተስማምተውና ተግባብተው እንዲኖሩ ብዙ ሠርተዋል:: ላለፉት 30 ዓመታት አካባቢ የሻመና ከተማ ቀበሌ ሊቀመንበር ሆነው ያገለገሉበት ወቅት አንድ ማሳያ እንደሆነ ይጠቅሳሉ::

በአሁኑ ወቅትም የሲዳማ ብሔራዊ ክልልዊ መንግሥት እንዲሁም በሃዋሳ ዙሪያ ወረዳ የምክር ቤት አባል የሆኑት አቶ ወላንሳ፤ ከግል ሥራቸው በተጨማሪ ማህበረሰቡ የጣለባቸውን ኃላፊነት በመወጣት በርካታ ሥራዎችን እየሠሩ ይገኛሉ:: የማህበረሰቡን የመልማት ጥያቄ ለመመለስ በተለይም ሌብነትን በመጸየፍ ከመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጋር በጋራ በመሆን ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው እየሠሩ ይገኛሉ:: ለማህበረሰቡ ጠቃሚ ናቸው በተባሉ ማንኛቸውም የልማት ሥራዎች ገንዘባቸውን፣ ዕውቀታቸውን፣ ጊዜና ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ እየሰጡ እንደያሚሠሩ የገለጹት አቶ ወላንሳ፤ በቅርቡም ክልሉ በማህበረሰብ ተሳትፎ አስገንብቶ ካስመረቃቸው የፖሊስ ጽህፈት ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ የጸጥታ ማዕከላት መካከል ግንባር ቀደም ተሳታፊ ነበሩ::

የክልሉ ጸጥታና ሰላም ቢሮ በሰላምና ጸጥታ ዙሪያ እየሠራ ባለው ሥራ ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው አቶ ወላንሳ፤ በዚህ ሥራ ላይ አሻራቸውን ካኖሩ የማህበረሰብ አካላት መካከል አንደኛው በመሆን ከክልሉ መንግሥት ዕውቅናን አግኝተዋል:: ለማዕከሉ ግንባታ በግላቸው 100 ሺህ ብር በማዋጣት ማህበረሰቡን በማሳተፍ ሌት ተቀን ሳይሉ ሥራቸውን ወደጎን በመተው ማዕከሉን ለመገንባት ከተሰጣቸው 90 ቀናት አስቀድመው በ54 ቀናት ውስጥ ማጠናቀቅ ችለዋል::

‹‹ሀገርን እየጎዳ ያለው ሃሳብ ማጣት እንጂ ገንዘብ ማጣት አይደለም›› የሚሉት አቶ ወላንሳ፤ ሰላም ከሌለ ማንም ሰው በሰላም ወጥቶ በሰላም መግባት አይችልም:: ንበረታችንን የሚጠብቁ ፖሊሶች ውጭ እያደሩ እኛ ቤታችን ማደር የለብንም:: በማለት የጸጥታ አካላት ለሥራ ምቹ በሆነ ቦታ ላይ ሆነው መሥራት እንዳለባቸው ይናገራሉ::

ይህ ምቹ የፖሊስ ጽ/ቤት 1200 ካሬ መሬት ስፋት ባለው ቦታ ደረጃውን በጠበቀ መንገድ የተገነባ ሲሆን፤ ግንባታውም በጥሬ ገንዘብ ብቻ ሰባት ሚሊዮን ብር ወጪ የጠየቀ ነው:: አጠቃላይ ማዕከሉ በ35 ሚሊዮን ብር ወጪ የተገነባ መሆኑን ተናግረዋል:: ማዕከሉ ደረጃውን የጠበቀና የደህንነት አጥር ያለው ሲሆን፤ አጠቃላይ ማህበረሰቡ ለዚህ ሥራ ከፍተኛ ተነሳሽነት የነበረው እንደሆነ ያመለክታሉ::

ትናንትን አሸንፈው ዛሬ በሆቴል ኢንቨስትመንትና በኮንስትራክሽን ግብዓቶች ንግድ የተሠማሩት አቶ ወላንሳ፤ በቀጣይም የተለያዩ ዕቅዶች እንዳላቸው ይጠቅሳሉ:: መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት በሰጠው ለየሌማት ትሩፋት በመሳተፍ ለሆቴል ግብዓት የሚሆኑ እንደ እንቁላል፣ ወተትና ስጋ የመሳሰሉትን በራሳቸው የማምረት ዕቅድ አላቸው:: በሆቴል ኢንቨስትመንት እንደመሰማራታቸውም በተጓዳኝ ለሆቴሎች ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን ማቅረብ ከቻሉ ተጨማሪ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚያስችላቸው ይሆናል:: ከዚህ ባለፈም ጉልህ አበርክቶ ያለው ነው:: ለዚህም መንግሥት ማስፋፊያ እንዲሰጠኝ ጥያቄ እያቀረብኩ ሲሆን በቀጣይ ይህንኑ ተግባራዊ አደርጋለሁ ይላሉ::

ከዚህ በተጨማሪም በአይነቱ ለየት ያለ ሁለገብ ህንጻ በሃዋሳ ከተማ የመገንባት ዕቅድ አላቸው:: ህንጻው ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል ነው:: ለዚህም አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ የክልሉ መንግሥት የግንባታ ቦታ እንዲፈቅድላቸው ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን፤ ጥያቄቸው መልስ ሲያገኝ በቀጥታ ወደ ግንባታ የሚገቡ ይሆናል:: በሃዋሳ ከተማ የሚገነቡት ህንጻ የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጥ እንደመሆኑ ለከተማዋ የሚኖረው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም::

በመጨረሻም ሥራ ሳይመርጡ ዝቅ ብሎ መሥራትን ወጣቶች መለማመድ እንዳለባቸው የመከሩት አቶ ወላንሳ፤ አሁን አሁን ምንም ሳይሠሩ በአንድ ጊዜ ብዙ ገንዘብ ለማግኘት የሚያልሙና አቋራጭ መንገድ የሚፈልጉ በርካታ ወጣቶች እንዳስተዋሉ ጠቅሰዋል:: ይህ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ገልጸው፣ ወጣቶች ለሥራ እራሳቸውን ዝግጁ ማድረግ እንዳለባቸው ይመክራሉ፤ ሰዎች ሥራ ሳይንቁ ያገኙትን ሥራ መስራት ከቻሉ በሀገሪቱ ብዙ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ይላሉ:: ለዚህም ከትንሽ ተነስተው ትልቅ ደረጃ የደረሱ በርካታ ሰዎችን በአብነት ማንሳት እንደሚቻል ነው ያስገነዘቡት::

# ተናጋሪው ዶሴ

# የአምባጓሮ ውጤት



**ምሕረት ሞገስ**

ተሰማ ታመነ ታደለ በደቡብ ክልል በወቅቱ ቦዲቲ ተብሎ በሚጠራው ወረዳ አሎ ጎጥ ከአቶ ታመነ ታደለ እና ከአለቴ አይሳ በ1984 ዓ.ም ሲወለድ፤ እዚህ ይደርሳል ብሎ የገመተ አልነበረም:: አዲስ አበባ ሲገባ ቤተሰቦቹ በእጅጉ ሕይወታችንን ይቀይራል ብለው ተስፋ አድርገውት ነበር:: በልጅነቱ ድል በትግል 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርቱን እስከ አምስተኛ ክፍል ሲከታተል ቆይቶ፤ ብዙም ሳይዝልቅ አቋረጠ::

ትምህርቱን ብዙም ባይቀጥልም አዲስ አበባ ውስጥ ዕድል ቀንቶት የባሕል ልብሶችን በመሸጥ ምርጥ ነጋዴ ሆኖ ትዳር መስርቶ ቤተሰቡን ማስተዳደር ጀመረ:: አንዳንዴ የሕይወት ስኬት በትምህርት ብቻ አይወሰንም ቢባልም፤ አለመማሩ ስሜቱን እንዳይቆጣጠር አድርጎት በመጨረሻም ሕይወቱ ተበላሸ::

የአንድ ወንድ ልጅ አባት የሆነው ተሰማ፣ ከጓደኞቹ ጋር መዝናናት ያበዛል:: በተለይ ደጉ ጮማ ስጋ እና ግሮሰሪ ቤት እየጠጣ መዝናናት መለያው ነው:: ገንዘብ ቢያገኝም ከማስቀመጥ ይልቅ እየተዝናና ያለውን ገንዘብ ይረጫል:: በወረሃ ጥቅምት ገበያው ደርቶ ከፍተኛ ገቢ ያገኝ የነበረው ተሰማ፤ እንደተለመደው ከጓደኞቹ ሳሬ ሳልፈቶ፣ ታሪኩ በቀለ እና መርካቶ አድነው አለሬ እንዲሁም ከደምመላሽ ዳታ ጋር አብረው እየጠጡ ሲጫወቱ ቀን ስምንት ሰዓት በግሮሰሪው የገቡ ምሽት አራት ሰዓት ሆነ::

ገና በጊዜ ወደ ስጋ ቤቱ የገቡት እነ ተሰማ፣ ሞቅ ብሏቸው ወደ ስካር አምርተዋል:: ነገር ግን ከምሽቱ አራት ሰዓት ቢሆንም ቤታቸው መግባት አልፈለጉም:: ስካር ነውረኛ ድርጊትን ከመፈፀም አልፎ፤ ሕይወትን እስከ ወዲያኛው የሚያበላሽ ድርጊትን ለመፈፀም እንደሚገፋፋ አልተረዱም:: ተሰማ፣ ቤተሰቡን ረስቶ እየጠጣ ሲያውካካ ከደጅ ፉሲካ እንግዳሰው የተባለ ሌላ ደንበኛ ወደ ግሮሰሪው ገባ::

ፉሲካ፣ እንደገባ የእነ ተሰማን ጓደኛ ደመላሽን ‹‹ አንተ ዶርዜ›› ሲል ሰደበው:: ሳሬ ተቆጣ፤ ፉሲካ ላይ እያፈጠጠ ‹‹ ለምን እንዲህ ብለህ ትሰድበዋለህ?›› ብሎ ተጠጋው:: ነገሩ ተባብሶ ሕይወት የመጠፋፋት ደረጃ ላይ ይደርሳል ብሎ ያልገመተው ፉሲካ፤ ‹‹ እኛ ጓደኛሞች ነን፤ ለምን በእኛ መሃል ትገባለህ?›› ብሎ ፉሲካ ለሳሬ ጥያቄውን በጥያቄ መለሰለት::

ተሰድቦ ሁኔታውን ችላ ብሎ ያለፈው ደመላሽ የጠጣውን ለማስወጣት ወደ መፀዳጃ ቤት ሔደ:: ሳሬ ጓደኛው መሰደቡ ቆጭቶታል:: ፉሲካ ችላ ቢለውም እርሱ ግን ነገር ነገር አለው:: መጠጡም እየገፋፋው ስሜቱን መቆጣጠር አቅቶት ወደ ፉሲካ ቡጢ ሰነዘረ:: ሁለቱም ተያያዙ፤ የሳሬ ጓደኞች ተነስተው የቢራ ጠርሙስ እና ብርጭቆ መወራወር ጀመሩ:: ተሰማ ቤተሰቡን ረስቶ ከእርሱ ጋር አብረው በነበሩ ጓደኞቹ መካከል ፀብ ሲነሳ፤ የቢራ ጠርሙስ እና ብርጭቆ ከመወራወር ያለፈ ከባድ ድርጊት ፈፀመ::

ተሰማ ዘሎ በግሮሰሪው ባንኮኒ ውስጥ ለሎሚ መቁረጫ ተቀምጦ የነበረውን ቢላዋ አንስቶ፤ ፉሲካ እንግዳሰውን መውጋት ጀመረ:: በስካር ውስጥ የነበረው ተሰማ የያዘውን ቢላዋ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ደጋግሞ መሰንዘር ቀጠለ:: የሕክምና ማስረጃው እንዳረጋገጠው ፉሲካ በተሰማ የቀኝ ደረቱ፣ የቀኝ ሆዱ፣ የግራ አንገቱ እንዲሁም የግራ ጭኑ ተወጋ:: ፉሲካን በቢላዋ የወጋው ተሰማ፤ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ላይ እንደገለፀው፤ ደጋግሞ መውጋቱን እንጂ በየትኛው የፉሲካ የሰውነት ክፍል ላይ እንደሰነዘረ አያስታውስም::

ሁለተኛውና የፀቡ አነሳሽ ሳሬ ሳልፈቶም በ1980 ዓ.ም የተወለደ ሲሆን፤ እርሱም በተመሳሳይ መልኩ ከደቡብ ክልል ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ሥራ ጀምሯል:: የካ ክፍለ ከተማ የሚኖረው ሳሬ፣ ፉሲካን በቦክስ ከመምታት አልፎ የቢራ ጠርሙስ ወርውሮበታል::

ሌላኛው በ1973 ዓ.ም አዲስ አበባ የተወለደው እና እንጦጦ አምባ ትምህርት ቤት እስከ ስምንተኛ ክፍል ትምሕርቱን የተከታተለው ታሪኩ በቀለም፤ በተመሳሳይ መልኩ የቢራ ጠርሙስ እና ብርጭቆ ወርውሯል:: ይህ ሁሉ ሲሆን ተሰዳቢው ደመላሽ ግን ስድቡን ከቀመሰ በኋላ ወደ መፀዳጃ ቤት ሔዷል::

ደመላሽ ከመፀዳጃ ቤት ሲመለስ ግሮሰሪው በብርጭቆ እና በቢራ ጠርሙስ ስብርባሪ ተሞልቶ ፉሲካ መሬት ላይ ወድቆ ደሙ እየፈሰሰ ነበር:: አብሮ ከእነ ተሰማ ጋር ሲጠጣ የነበረው ታደሰ ካቡሬ ግን ከመመልከት ውጪ ሚና አልነበረውም:: በመጨረሻም የቢራ ጠርሙስ ስባሪ እና ብርጭቆ ሲወረወርበት እንዲሁም በስለት ሲወጋ የነበረው ፉሲካ የሚያግዝለት፤ ተከላክሎ በፍጥነት ሕክምና ቦታ የሚያደርሰው በማጣቱ ሕይወቱ አለፈ::

ወንጀል መፈፀሙን መረጃ የደረሰው የፖሊስ ምርመራ ቡድን ተጎጂውን ሃኪም ቤት ከመውሰድ አልፎ የወንጀል ድርጊቱን ማን እንደፈፀመው ማጣራት ጀመረ:: ድርጊቱን የፈፀሙት እነ ተሰማ ፉሲካ ላይ ከባድ ጉዳት ካስከተሉ በኋላ ሁሉም ጠፍተው ነበር:: ሆኖም የፖሊስ ምርመራ ቡድን ከፍተኛ ክትትል በማድረግ የወንጀል ድርጊት የፈፀሙትን በሙሉ በቁጥጥር ሥር አዋላቸው::

የፖሊስ ምርመራ ቡድኑ ወንጀሉ መፈፀሙን የሚያመለክቱ መረጃዎችን በሙሉ አደራጅቶ ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሠርት አቀረበ:: ከምርመራ ቡድኑ የተደራጀ መረጃ ያገኘው ዐቃቤ ሕግም የወንጀል ድርጊቱን በዝርዝር ለፍርድ ቤት አቀረበ::

### የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሽ ነዋሪነታቸው የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የሆኑት ተሰማ ታመነ ታደገ፣ ሳሬ አልፈቶ፣ ታሪኩ በቀለ እንዲሁም በጉለሌ ክፍለ ከተማ ነዋሪነቱን ያደረገው መርካቶ አድነው በተጠረጠሩበት ወንጀል ከሳሽ የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ሆኖ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ አደረገ::

ክሱ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1) (ሀ)፣ 35 እና 577 (3) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ መሆኑን የወንጀል ዝርዝሩ ላይ በግልፅ ተቀምጧል::

ተከሳሾች ጥቃትን ለመመለስ ራስን ወይም ሌላውን ለመከላከል ወይም ጠበኞችን ለመገላገል በማሰብ ሳይሆን፤ በሰኔ 17 ቀን 2015 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት አራት ሰዓት ከሰላሳ፤ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ልዩ ቦታው ደጉ ስጋ ቤት እና ግሮሰሪ ውስጥ ደመላሽ ዳታ የሚባለው አንደኛው መስካሪ ወደ ግሮሰሪው ውስጥ ሲገባ ሟች ፉሲካ እንግዳሰው ምስክሩን ደመላሽን ስለሚተዋወቁ በቀልድ መልክ ‹‹ አንተ ዶርዜ›› በሚል ይሰድበዋል::

ሁለተኛ ተከሳሽ ማለትም ሳሬ ሳልፈቶ ‹‹ለምን እንደዚህ ብለህ ትሰድበዋለህ?›› ሲለው፤ ‹‹ ጓደኛሞች ነን ለምን በእኛ መሃል ትገባለህ›› የሚል ጥያቄ ሟች ፉሲካ እንግዳሰው አቀረበ:: ተከሳሽ ሟች ላይ ቦክስ ሰንዝሮ ሲመታው ተያያዙ:: ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር አብረው መጠጥ ሲጠጡ የነበሩት 1ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ማለትም ተሰማ ታመነ፣ ታሪኩ በቀለ እና መርካቶ አድነው የቢራ ጠርሙስ እና ብርጭቆ በመወርወር ሟችን የተለያዩ የሰውነት ክፍሉን መትተውታል::

አንደኛ ተከሳሽ ተሰማ ታመነ በድጋሚ በስለት ሟችን የቀኝ ደረቱን ፣ የቀኝ ሆዱን፣ የግራ አንገቱን እንዲሁም የግራ ጭኑን በመውጋት ሕይወቱ እንዲያልፍ አድርጓል:: በመሆኑም በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆኑ በፈፀመው የአምባጓሮ ወንጀል እርሱ እና ግብርአበሮቹ ተከሰዋል::

ሁለተኛው ክስ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ ሲሆን፤ ወንጀሉ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 539(1) (ሀ) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ነው:: ተከሳሽ ሰውን ለመግደል በማሰብ በሰኔ 17 ቀን 2015 ዓ.ም በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ልዩ ቦታው ደጉ ስጋ ቤት አካባቢ በተነሳ ፀብ ምክንያት ተከሳሹ ከእነ ግብርአበሮቹ ለሎሚ መቁረጫነት አገልግሎት የሚውል የነበረውን ቢላዋ የግሮሰሪው ባንኮኒ ውስጥ ዘሎ ገብቶ በመውሰድ ጨካኝነቱን እና ነውረኛነቱን በሚያሳይ ሁኔታ የሟችን ወሳኝ አካላት ወግቷል::

የቀኝ ደረቱን በስተጀርባ የግራ ደረቱን፣ የቀኝ ሆዱን፣ በግራ በኩል አንገቱን እና ጭኑን ደጋግሞ በስለት በመውጋት ሕይወቱ በአሰቃቂ ሁኔታ እንዲያልፍ ያደረገ በመሆኑ ከባድ የግድያ ወንጀል ፈፅሟል ሲል ዐቃቤ ሕግ ክስ መስርቷል::

### የማስረጃ ዝርዝር

ክሱ ሲመሠረት የተለያዩ ማስረጃዎች የቀረቡ ሲሆን፤ አስራ አራት የሰው ምስክሮች ቀርበው ግድያው መፈፀሙን እና በምን መልኩ እንደተፈፀመ ምስክርነት ሰጥተዋል :: በተጨማሪ የሰነድ ማስረጃም ቀርቦ በፍርድ ቤቱ ታይቷል:: ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል የሕክምና ኮሌጅ የፎረንሲክ ሜዲስንና ቶክሲኮሎጂ ትምህርት ክፍል በሰኔ 29 ቀን 2015 ዓ.ም በቁጥር ጳሀ8/4820 የተላከ የአስክሬን ምርመራ ውጤትም በማስረጃነት ቀርቧል::

የካቲት 12 ሆስፒታል በሐምሌ 26 ቀን 2015 ዓ.ም ሟች ላይ የደረሰውን ጉዳት የሚያመለክት የሕክምና ማስረጃም ቀርቧል:: በተጨማሪ የሟችን ማንነትና የደረሰበትን ጉዳት የሚየሳይ 31 ፎቶግራፍም ለፍርድ ቤት ቀርቧል::

### ውሳኔ

ተከሳሽ ተሰማ ታመነ ታደሰ፣ በተከሰሰበት ወንጀል ጉዳይ በክርክር ላይ የነበረና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት የነበረው ክርክር መቋጫ አግኝቶ በሕዳር 4 ቀን 2017 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ተሰጥቷል። ፍርድ ቤቱ ክስና ማስረጃውን ከሕግ ጋር አገናዝቦ ድርጊት ፈፃሚዎቹን ያርማል ሌሎችን ያስተምራል በሚል በሰጠው ውሳኔ አንደኛ ተከሳሽ ማለትም ተሰማ ታመነ በአስር ዓመት ፅኑ እስራት፤ 2ኛ ተከሳሽ ሳሬ ሳልፈቶ በአስር ዓመት ፅኑ እስራት፤ እንዲሁም 3ኛ ተከሳሽ ታሪኩ በቀለ በአስር ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት በተጨማሪ 4ኛ ተከሳሽ በነፃ ይሰናበት ሲል ውሳኔ አሳልፏል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

# ፊልሞች እና የዘመን ዓውድ

**ዋሰልኝ አየለ**

ፊልሞቻችንና ድራማዎቻችን ዛሬም በ20ኛው ክፍለ ዘመን አስተሳሰብ ላይ ያሉ ይመስለኛል:: በእርግጥ ብዙ ፊልሞች ዘመንን ቀድመው በመሄድ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት የሚሰሩም አሉ:: በተለይም የቴሌቭዥን ድራማዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሀሳባዊና ቀልብን ያዝ የሚያደርግ ይዘት ያላቸው እየሆኑ እንደመጡ ከዚህ በፊት አድንቀናል:: የተቀሩትም ቢሆን የ20ኛው ክፍለ ዘመን አስተሳሰብን እያንፀባረቁ ያሉት ለማስተማር ብለው መሆኑ ግልጽ ነው፤ ዳሩ ግን የሚያስተምሩበት መንገድ በዚህ ዘመን በሌለ እምነትና በዚህ ዘመን በሌለ አስተሳሰብ ላይ ነው::ነገሩን በምሳሌ ግልጽ ላድርገው መሰለኝ!

ቀደም ባሉት ዘመናት ሥራ ይናቅ ነበር፤ የመደብ (የደረጃ) መለያ ይደረግ ነበር ማለት ነው:: እንደ ብረታ ብረት ማቅለጥ፣ እንጨት መፋቅ፣ ወንበርና ጠረጴዛ የመሳሰሉትን መገጣጠም፣ ልብስ ስፌትና የመሳሰሉት የዕደ ጥበብ ሥራዎች ብዙም ክብር የሌላቸው ሥራዎች ተደርገው የሚታዩ ነበሩ:: ጋብቻ ሁሉ ያስቀራሉ ተብሎ ይታመን ነበር:: በእነዚህ የሥራ ዘርፎች የተሰማሩ ሰዎች ለሚስትነት የሚጠይቋት ሴት ትንቃቸዋለች ተብሎም ይፈራ ነበር::

በዚህ አመለካከት በመሄድ እና የዚህ ልማድ ተፅዕኖ ይመስላል ፊልሞቻችን ላይ አንድ የምናየው ነገር አለ:: የሆነ ወንድ የወደዳትን ሴት ሲተዋወቃት ሥራውን በግልጽ አይነግራትም፤ ‹‹እሺ!›› አትለኝም በሚል ፍርሃት መሆኑ ነው:: ወይም ክብር አለው የሚባል የሥራ ዘርፍ ይነግራትና ይዋሻታል:: በመጨረሻ ግን በሆነ አጋጣሚ የሚሰራውን ሥራ ታየዋለች:: ይህኔ ይጣላሉ:: የሚጣሉት፤ በአንዳንድ ፊልሞች ሥራውን በመናቅ ሳይሆን ለምን ዋሸኸኝ በሚል ነው፤ በአንዳንዶቹ ፊልሞች ደግሞ ሥራውን በመናቅ ነው፤ የገሃዱን ዓለም ነፀብራቅ ለማሳየት መሆኑ ነው::

የዚህ ተቃራኒ ደግሞ አለ:: የሆነ ባለሀብት ይወዳትና እምቢ ትላለች:: ቀደም ሲል በነበረው ዘመን አመለካከት ዝቅተኛ ሊባሉ የሚችሉ የሥራ ዘርፎች ላይ የተሰማራ ወንድ ታፈቅራለች:: የሚሰራበት ሥራ ቦታ እየሄደች ታየዋለች:: የሚኖርባት ደሳሳ ጎጆ ውስጥ ትሄዳለች:: ይሄኛው ይዘት ብዙ ጊዜ ‹‹ድሃ ወንድ የሚወደደው በፊልም ብቻ ነው›› እየተባለ የሚቀለድበት ነው:: ለማስተማር ተብሎ መሆኑ ያስታውቃል::ፊልሙን የምትተውነው ተዋናይት በገሃዱ ዓለም ሕይወቷ ግን ድሃ ባል አግብታ አላየንም:: ቢያንስ በልቦለድ እንኳን እንዲህ ብናደርግ ብሎ የመመኘት ይመስላል::

ከላይ የተገለጹት ሁለቱም አይነት መንገዶች ዘመን ያለፈባቸው ይመስለኛል:: በዚህ ዘመን ሊታይ የሚችለው ምናልባትም የሚያገኘው የገቢ መጠን እንጂ የሥራው አይነት አይደለም:: ምናልባት በህግ የተከለከለ እና ከኢትዮጵያዊነት ባህል አንፃር ‹‹ነውር›› የሚባል ካልሆነ በስተቀር፤ ሥራ የሚናቅበት ዘመን በተጨባጭ ያለፈበት ይመስለኛል:: ዘመድ አዝማዶቼ እልም ያለ ገጠር ውስጥ ስለሆኑና አሁናዊ ሁኔታውን ስለማውቀው ይህን ለመመስከር እችላለሁ:: ማንኛውም የገጠር ሰው ዛሬ ላይ ብረታ ብረት የሚያቀልጥ፣ እንጨት የሚገጣጥም፣ ልብስ የሚሰፋ ሰው እና ሸማኔ አይንቅም:: በከተሞች ደግሞ የትኛውም ሥራ የማይናቅ መሆኑ ለዘመናት የቆየ ልማድ መሆኑ ይታወቃል::

ዛሬ ላይ አንዲት ሴትና አንድ ወንድ በሆነ አጋጣሚ ቢተዋወቁና ሥራ ቢጠያየቁ፤ ምናልባት የገቢው መጠን እንጂ የሥራው አይነት የሚያናንቅ አይሆንም:: የወር ደሞዝተኛም ይሁን የቀን ሠራተኛ፣ ነጋዴም ይሁን ባለሥልጣን፣ ጠጋኝም ሆነ አቅላጭ.... ዋናው የሚያገኘው ገቢ ነው::

በሌላ በኩል አሁን ያለው ዘመን ነፃ አስተሳሰብና አመለካከት ያለበት ዘመን ነው:: ሴቶች ራሳቸውን ችለው የሚያስቡበትና የራሳቸውን ነፃ ውሳኔ የሚወስኑበት ነው:: ምን ይሉኛል ተብሎ እንደ ድሮው ዙሪያ ገባው ብቻ የሚታይበት ሳይሆን፤ የራስ ፍላጎትንና ነፃ ምርጫን የሚከተሉበት ነው:: የማይካደው ሀቅ ግን የገቢ መጠን አሁንም ቢሆን ተፅዕኖ ማድረጉ አይቀርም:: ከዚያ ውጭ ግን የሥራው አይነት በዚህ ዘመን ጉዳይ የሚሆን አይመስለኝም::

ብዙ ጊዜ የምታዘበው ግን ቀደም ሲል የተሰሩ ፊልሞችን ሳይቀር አንድ ትዕይንት (ሲን) በመቁረጥ መልዕክት ለማስተላለፍ ማህበራዊ ገጾች ላይ አያለሁ::ሥራ አይናቅም የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ መሆኑ ነው:: በዚህ ዘመን ሥራ የማይናቅ መሆኑን የማያውቅ አለ ወይ ነው ጥያቄው!

አንዳንድ እምነቶችና አመለካከቶች ነባራዊና ዓውዳዊ ሁኔታው ተቀይሮም ባሉበት ይቀጥላሉ:: ብዙ ጊዜ የሚገርመኝን ነገር ልንገራችሁ:: ቀደም ባለው ዘመን ሾፌርነት የጥቂት ሙያተኞች ሥራ ነበር:: መኪና የሚያሽከረክር ሁሉ ‹‹ሾፌር›› ተብሎ ይጠራል:: ታዲያ በዚህ ሁኔታ እንደ ልማድ የተያዙ የሾፌር ባህሪያት አሉ:: ለምሳሌ፤ ችኩልነት፣ ተሳዳቢነት፣ አግባብ ያልሆኑ ቃላትን መናገር የመሳሰሉት የሾፌር ባህሪ ተደርገው ይታያሉ:: በዚህም ምክንያት የሚያሽከረክር ሰው ሁሉ የሚያደርገውን ነውር ነገር ‹‹ድሮስ ከሾፌር›› የሚባል ልማድ አለ፡፡

አሁን ግን እንደዚያ ለማለት አያስችልም:: ‹‹ሾፌር›› የሚባሉት እስከ ዛሬ ድረስ የስንቱን ነውረኛ ነውር ተሸክመው ኖረዋል ለካ! አሁን ብዙ አሽከርካሪዎች በነውር ቃላት ሲሳደቡ እየሰማን ነው:: እነዚህ ሰዎች በሙያቸው ‹‹ሾፌር›› አይደሉም:: በየትኛውም ሙያ ውስጥ የተሰማራ ሰው መኪና መያዝ ይችላል፤ ብዙ ሰዎችም ባለመኪና ሆነዋል:: በየመንገዱ አንገቱን አሾልኮ ሲሰዳደብ የምታዩት ሁሉ በሾፌርነት ሙያ የተቀጠረ ነው ማለት አይደለም:: ወይስ የራሱን መኪና የሚያሽከረክር ሰው ‹‹ሾፌር›› መባል አይችልም?

አንድ በሌላ ሙያ ላይ የተሰማራ ሰው እያሽከረከረ ወደ ሥራው እየሄደ ነው እንበል:: ይህ ሰው አንገቱን አሾልኮ ዜብራ የሚሻገሩ ሰዎችን ተሳደበ እንበል:: ስለዚህ በተለመደው ልማድ እግረኞቹ ‹‹ድሮስ ከሾፌር...›› ሊሉ ይችላሉ ማለት ነው:: ሰውየው ግን በሙያው ሾፌር ሳይሆን፤ የተቋም ኃላፊ ሊሆን ይችላል፣ ሐኪም ሊሆን ይችላል፣ ጠበቃ ሊሆን ይችላል፣ መሃንዲስ ሊሆን ይችላል፣ ነጋዴ ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ ችግሩ የጥቂት ሰዎች ሳይሆን እንደ ሕዝብ ያለብን ችግር ነው ማለት ነው::

ይህ ልማድ የመጣው ቀደም ባለው ዘመን ሾፌር የጥቂት ሰዎች ሙያ ስለነበር ነው:: እንደ ሀገር አቋራጭና ሌሎች ከባድ ተሽከርካሪዎችን ለሚያሽከረክሩ ባለሙያዎች የተሰጠ ዘርፍ ስለመሰለ ነው:: በዚህ ዘመን ግን መኪና ያለው እና ራሱ የሚያሽከረክር ሰው ሁሉ ሾፌር ነው ማለት ነው:: ወይስ ተቀጥረው ሲሰሩትና የራስን መኪና ሲሾፍሩ ይለያይ ይሆን?

ወደ ፊልሞችና ድራማዎች ስንመለስ፤ በዚህ ዘመን ሥራ የሚናቅበት አመለካከት ያለ አይመስለኝም:: ምናልባት በጣም በጥቂቱ በግለሰቦች ደረጃ ሊኖር ቢችል እንኳን እንደ ባህል ግን አለ ለማለት አያስደፍርም::

አሁን ላይ ያለው ትውልድ ‹‹እነዚህ ሥራዎች ለካ ነውር ነበሩ እንዴ!›› የሚል ስሜት ሊፈጠርበት አይገባም:: ምክንያቱም በተግባር ነውር ሲደረጉ አላየምና! ስለዚህ ለማስተማር ተብሎ የሚደረጉ የፊልምና ድራማዎች ይዘት የዘመኑን ዓውድ ያገናዘበ ይሁን!

## ዓለም አቀፍ

# አሜሪካዊው ባለሀብት እንዴት ተገደለ ?


የኒውዮርክ ፖሊስ የጤና ኢንሹራንስ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ግድያ በተመለከተ ተጠርጣሪ ያለውን አንድ ጭምብል ያላደረገ ግለሰብ ሁለት ፎቶዎችን አውጥቷል። የዩናይትድ ሄልዝኬር ኃላፊው ብሪያን ቶምፕሰን ህዳር 25 ቀን 2017 ዓ.ም ማንሃተን ከሚገኘው ሂልተን ሆቴል ውጭ ጀርባው ላይ በጥይት ተመትቶ ህይወቱ አልፏል።

ገዳዩ የቶምፕሰንን ንብረት ሳይወስድ ከቦታው ሸሽቷል። ሟች አስቀድሞ በተደረገ ዕቅድ ዒላማ መሆኑን ፖሊስ ያምናል። መርማሪዎች ተጠርጣሪውን ለመከታተል ፊትን ለይቶ የሚያሳውቅ ቴክኖሎጂ እና በጥይቶቹ ላይ በምስጢር የተፃፉ መልዕክቶችን ተጠቅመው እየመረመሩ ነው። የግድያውን ምክንያት እስካሁን ይፋ አላደረጉም።

ጥቃቱ የተፈፀመው ጠዋት 1፡00 ሰዓት ገደማ በታይምስ ስኩዌር እና በሴንትራል ፓርክ አቅራቢያ በሚገኘው ማንሃተን ውስጥ ነው። ቶምፕሰን በዕለቱ በባለሀብቶች ኮንፈረንስ ላይ ተገኝቶ ንግግር እንዲያደርግ ቀጠሮ ተይዞለት ነበር። እንደ ፖሊስ ገለጻ ከሆነ፤ ተጠርጣሪው ጥቁር የፊት ጭንብል እና ቡናማ ወይም ክሬም ቀለም ያለው ጃኬት ለብሶ ቶምፕሰን ንግግር ያደርግበታል ተብሎ በሚጠበቅበት ሂልተን ሆቴል ደጃፍ ለአምስት ደቂቃ ያህል የጠበቀው ይመስላል።

በእግሩ በቦታው የደረሰው ቶምፕሰን ጀርባው እና እግሩ በጥይት ተመትቶ በአካባቢው በሚገኝ ሆስፒታል ከደረሰ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ህይወቱ ማለፉ ተነግሯል። የተጠርጣሪው መሳሪያ አልተኩስ ያለ ቢመስልም በፍጥነት አስተካክሎ መተኮስ መቀጠል መቻሉን የኒውዮርክ ፖሊስ ዲፓርትመንት (ኤንዋይፒዲ) የመርማሪዎች ዋና አዛዥ ጆሴፍ ኬኒ ገልጸዋል።

ከደህንነት ካሜራ ቀረጻዎች እንደተገኘ ተንቀሳቃሽ ምስል ከሆነ፤ ገዳዩ ሽጉጡ ላይ ድምጽ ማፈኛ እንደገጠመ የሚያሳይ ይመስላል ሲል ገልጿል። የኒውዮርክ ከተማ ከንቲባ ኤሪክ አዳምስ ለኤምኤስኤንቢሲ እንደተናገሩት፤ ድምጽ ማፈኛ መጠቀም ታይቶ የማይታወቅ ነገር ነው።





“ድምጽ ማፈኛ ከዚህ በፊት አይቼ አላውቅም። ይህ በእውነት ለሁላችንም አስደንጋጭ ነገር ነበር” ሲሉ የቀድሞው የኤንዋይፒዲ ባልደረባ ተናግረዋል።

መርማሪዎች ሽጉጡ ቢቲ ስቴሽን ስድስት 9 ነው ብለው እንደሚያምኑ ተዘግቧል። ይህ መሳሪያ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዘመን የልዩ ዘመቻ ኃይሎች ይጠቀሙበት የነበረው የሽጉጥ አይነት ነው። ፖሊስ መሳሪያው የት እንደተገዛ ለማወቅ በኮነቲከት የሚገኙ የመሣሪያ መደብሮችን ጎብኝቷል ተብሏል። ከተኩሱ በኋላ ተጠርጣሪው በእግር ሲሸሽ በቪዲዮ ላይ ታይቷል። ባለስልጣናት ተጠርጣሪው የሊፍት ንብረት የሆነውን ኤሌክትሪክ ብስክሌት ተጠቅሟል የሚል እምነት መጀመሪያ ላይ ነበራቸው።

እስካሁን በቶምፕሰን ግድያ ዙሪያ የሚደረገው ምርመራ ፖሊስ ተጠርጣሪውን ለመለየት ጥቂት ፍንጮች ላይ ብቻ ያተኮረ ሆኗል። ሐሙስ ዕለት ጭንብል ያላደረገ ግለሰብ ሁለት ፎቶዎችን ይፋ ያደረጉት ባለስልጠናት ኤንዋይፒዲ ከግድያው ጋር በተያያዘ “ለጥያቄ ይፈለገዋል” ብሏል።

የሕግ አስከባሪ ምንጮች ለሲቢኤስ እንደተናገሩት ከሆነ፤ ግለሰቡ በአካባቢው በሚገኝ ሆስቴል ውስጥ ለመግባት የሃሰተኛ መታወቂያ ተጠቅሟል ተብሎ ይታመናል። ጥቅም ላይ የዋለው ስም የእውነተኛ ሰው ነው ተብሎ አይታመንም። መርማሪዎች እንደሚያምኑት ግለሰቡ ከጥቃቱ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ከአትላንታ፣ ጆርጂያ ወደ ኒውዮርክ በአውቶቡስ እንደተጓዘ ስለምርመራው አጭር መግለጫ ያገኙ ግለሰብን ጠቅሶ ሲቢኤስ ዘግቧል። ግለሰቡ የአውቶቡስ ጉዞ መነሻው አትላንታ ይሁን መንገድ ላይ ይሳፈር ለጊዜው ግልጽ አይደለም።

ከተጠርጣሪው ጋር ተመሳሳይ አይነት ሰው ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም። ተጠርጣሪው ጥቃት ከማድረሱ ከደቂቃዎች በፊት በአቅራቢያው በሚገኝ ስታርባክስ ፎቶ መነሳቱን ፖሊስ ገልጿል። በምስሉ ላይ በጭንብል ቢሸፈንም ጭምብሉ በበቂ ሁኔታ ወደ ታች በመጎተቱ ዓይኖቹ እና የአፍንጫው ክፍል እንደሚታዩ የፖሊስ ምንጮች ለሲቢኤስ ተናግረዋል።

ምስሉን ተጠቅመው መርማሪዎች በፊት መለያ ሶፍትዌር ማንነቱን ለመለየት እየሞከሩ ነው። ምንም እንኳን ገዳዩ የቶምፕሰንን ንብረት ሳይወስድ ቢሸሽም መርማሪዎች እስካሁን ስለ ግድያው ምክንያት አላወቁም።ፖሊስ በቦታው የተገኙ ሦስት የጥይት ቀለሃዎችን እና ሦስት ጥይቶች ላይ ዲኤንኤ ምርመራ ለማድረግ እየሞከሩ ነው። “መካድ”፣ “መከላከል” እና “ማስቀመጥ” የሚሉት ቃላት በቀለሃዎቹ ላይ ተገኝተዋል ሲሉ ሁለት የሕግ አስከባሪ ምንጮች ተናግረዋል።

በተጠርጣሪው ማምለጫ መንገድ ላይ ተንቀሳቃሽ ስልክ ተገኝቷል። ፖሊስ ስልኩን “እየመረመርኩ ነው” ብሏል። በተጠርጣሪው ተጥሏል ተብሎ የሚታመን የቡና ኩባያም ለጣት አሻራዎች ምርመራ በሚል ወደ ኤንዋይፒዲ ወንጀል ላብራቶሪ ተልኳል። ቀደም ሲል ግለሰቡ ሲገባበት በነበረው በማንሃታን አፐር ዌስት ሳይድ በሚገኝ ቦታ ላይ ፍተሻ መደረጉን መርማሪዎቹ ገልጸዋል።


ቦታው በፍሬድሪክ ዳግላስ የመኖሪያ ቤት ፕሮጀክት አቅራቢያ ሲሆን፤ ተጠርጣሪው ወንጀሉ በተፈጸመበት ዕለት ጠዋት 11፡00 ሰዓት ላይ ከቤት ውጭ በደህንነት ካሜራዎች ታይቷል ተብሏል። ግድያው የተፈጸመበት ጎዳና አቅራቢያው በሚገኘው ማሪዮት ሆቴል የሚገኘውን የቶምፕሰን ክፍል እንደሚፈትሽ ፖሊስ ተናግሯል።

ቶምፕሰን በአውሮፓውያኑ 2004 ከፕራይስዋተርሃውስኮፐርስ የአካውንቲንግ ድርጅት የአሜሪካን ትልቁን የግል መድን ተቋም ወደ ሆነው ዩናይትድሄልዝ ተቀላቅሏል። የቶምፕሰን ባለቤት ከኤምኤስኤንቢሲ ጋር ባደረገችው ቃለ ምልልስ፤ ቀደም ሲል አንዳንድ ዛቻዎች እንደነበሩ ተናግራለች። ዝርዝር መረጃ ከመስጠት ግን ተቆጥባለች።

“እሱ ሲያስፈራሩት የነበሩ አንዳንድ ሰዎች እንዳሉ መናገሩን አውቃለሁ” ብላለች። በቶምፕሰን የትውልድ ከተማ ማፕል ግሮቭ፣ ሚኒሶታ በ2018 በቤቱ አንድ አጠራጣሪ ክስተት ነበር ሲል ፖሊስ መግለጹን ቢቢሲ ዘግቧል።

# አብዝቶ ማሰብና መጨነቅን ማቆም

**አስናቀ ፀጋዬ**



አብዝቶ ማሰብና መጨነቅ የብዙ ሰው ችግር ነው:: እድሜህ 13 ዓመት ሆኖህ የሕይወት ጥያቄ መጠየቅ ከጀመርክ ጀምሮ እስከትሞት ድረስ እንደጥላ የሚከተልህ ፀባይ ነው:: ማሰብ! ፤መጨነቅ! በጣም አብዝተን የምንጠቀምባቸው ፀባያት ናቸው:: መጠኑ ይለያይ እንጂ አብዝቶ የማያስብና የማይጨነቅ ሰው የለም:: ማሰብ መልካም ነገር ነው:: ሕይወት የሚቀይር ነገር ነው:: ሲበዛ ነው መጥፎነቱ:: አብዝተህ ስትጨነቅ እንቅልፍ ታጣላህ:: አንዳንዴ የምትችለውን ሁሉ አትሠራም:: ወይ ደግሞ ብዙ ከማሰብህ የተነሳ አቅም ታጣለህ:: ስታስብ ጊዜው ይሄድብሃል::

አንዳንዴ አስበህ! አስበህ! አይደክምህም? ያውም ተመሳሳይ ሃሳቦች:: እዚህ ግባ የማትላቸው ተደጋጋሚ ሃሳቦች:: በተደጋጋሚ መልሰህ መላልሰህ ታስባለህ:: ወይ የትናንት ትዝታ ነው፣ ወይ ቁጭት ነው፣ ወይ የሚያስጨንቅህ ጉዳይ ነው፣ ወይ ደግሞ አታውቀውም:: አንዳንዴ ምን እንደምታስብ ራሱ አታውቀውም:: ግን ጊዜህን እየተሻማ ነው:: ጉልበትህን እየመጠጠው ነው:: ከሰው በታች እያደረገህ ነው:: ጭንቀታም እያደረገህ ነው:: ምን ይሻላል ታዲያ?

በዚህ ዓለም በጣም ከፍ ያለ የስኬት ደረጃ ላይ የደረሱ የሃይማኖት ወይ የቢዝነስ አልያም የምናከብራቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚያስቡት በፕሮግራም ነው:: ምን ማለት መሰላችሁ? ሥራ እየሠሩ ከሆኑ ሥራቸው ላይ ነው መቶ ከመቶ ትኩረታቸው:: ከቤተሰባቸው ወይም ከፍቅረኛቸው ጋር ከሆኑ መቶ ከመቶ እዛ ቦታ ላይ ናቸው:: ቅፅበቱ ላይ ነው የሚያተኩሩት:: ማሰብ ሲፈልጉ ደግሞ ቁጭ ብለው ያስባሉ:: እኛ የከበደን እሱ ነው:: በምንፈልገው ሰዓት አይደለም የምናስበው:: ሥራ እየሠራን ሃሳቦች አሉ:: የምንፈልገውን እያደረግን ሃሳቦች ይመጣሉ:: ልንተኛ ስንልም እንዲሁ::

ታዲያ ምን ይሻላል? አስበህ ሃሳብን መቆጣጠር ብትችል ተአምር እኮ ነው የምትሠራው:: ብዙ ነገር ነው ሕይወትህ ላይ የምትቀይረው:: ምን ይሻልሃል ታዲያ? እነሆ ቀላልና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት ሳይንሳዊ መፍትሄዎችን ጀባ ልበልህ::

**1ኛ.ራስን ማድመጥ**

አንዳንዴ ምን እንደምታስብ እንኳን አታውቀውም:: እንደውም አንዳንድ ሰው ሃሳብ ውስጥ በጣም ይሰምጥና የሚነቃው ወይ ስልኩ ሲጠራ ነው፣ ወይ ደግሞ «አንተ! የት ሄድክ በሃሳብ» ሲባል ነው:: ከዛ ምን እያሰብክ ነው? ሲባል ምን እንደሆነ አያውቀውም:: ስለዚህ አሁን ራስህን ለማድመጥ ሞክር:: ምንድን ነው የምታስበው? ልክ ስታስብ ንቃ:: የሆነ ሃሳብና ጭንቀት ውስጥ ስትገባ አሁን እያሰብኩ ነው በል:: የሆነ ሰው መጥቶ እስኪቀሰቅስህ አትጠብቅ:: ከዛ ትነቃና ምንድን ነው እያሳሰበኝ ያለው? የምትለውን ለይተህ አውጣው::

በእርግጠኝነት በጣም አብዝተህ የምታስባቸው ነገሮች ከሁለትና ሶስት አጀንዳዎች አይበልጡም:: ወይ ኑሮ ነው፣ ወይ ትዳር ነው፣ ወይ ሥራ ነው፣ ወይ ትምህርት ነው፣ ወይ ቢዝነስ ነው፣ ወይ ገንዘብ ነው አልያ ደግሞ የፍቅር ግንኙነት ነው:: ከእነዚህ አያልፍም:: ስለዚህ ምን እንደምታስብ ነቃ ብለህ ራስህን ለማድመጥ ሞክር:: እንደዚህ የማድረግህ ዓላማው ጫፉን ለመያዝ ነው:: ስለምን እያሰብክ እንደሆነ ለማወቅ ነው:: አየህ! ያስጨነቀህን ጉዳይ ለይቶ ለማወቅ ነው:: ስለዚህ ከጭንቀትና አብዝቶ ከማሰብ መውጣት ከፈለክ ራስህን አድምጠውና ልክ ሃሳብ ውስጥ ስትገባ ነቃ ለማለት ሞክር:: «ይህን እያሰብኩ» ነበር በል::

**2ኛ.አምስት መፍትሄዎችን ፃፍ**

ምን እንደሚያሳስብህ ማወቅ ከጀመርክ አሁን ወረቀት ላይ ማሰብ መጀመር አለብህ:: ወረቀት ላይ የሚያስቡ ሰዎች ሃሳባቸውን መቆጣጠር ይችላሉ:: ስለዚህ ይህ ችግር በጣም እያሳሰበኝ ነው ብለህ ትፅፍና ወደ አዕምሮህ የሚመጡትን መፍትሄዎች መዘርዘር ጀምር:: አምስት መፍትሄዎችን ፃፍ:: ለምን መሰለህ አዕምሮህ ትኩረቱን ከችግሩ ላይ አንስቶ ወደ መፍትሄው ማምጣት አለበት:: ስለመፍትሄው ማሰብ አለብህ:: ስለጨለማው አብዝቶ ማሰብ ብርሃን አይሰጥህም:: ችግሩ ላይ ጊዜ አታጥፋ::

አየህ! በዚህ ምድር ሁለት አይነት ሰዎች አሉ:: የመጀመሪያዎቹ ስለችግሩ ሲነገራቸው ለምሳሌ ኑሮ ተወደደ ተብሎ ሲነገራቸው «አቤት! አቤት! ይሄኔ ዘይቱን ደብቀውት ነው፤ ሊገሉን ነው፣ እንደው ምን አደረግናቸው የሚያስርቡን እኛ ምን በደለን፣ በላባችን ሰርተን በገባን እንደው ምን አድርጉ ነው የሚሉን» ይላሉ:: ችግሩ ላይ ይራቀቁበታል:: አብዝተው ስለችግሩ ያስባሉ:: ሁለተኞቹ ግን ኑሮ ተወደደ ሲባሉ፣ ችግሩን ሲሰሙ «ምን ይሻላል ይበልጥ ሳይወደድ ቶሎ እንግዛ እንዴ» ይላሉ:: ወደ መፍትሄው በቶሎ ይገባሉ:: «ምንድን ነው የሚሻለው ገቢዬን ላሳድግ፣ ሁለት ሶስት ሥራ ልሥራ ኑሮ ከተወደደ» ይላሉ::

አንተ የትኛው ላይ ነህ? ችግሩ ላይ ነው አብዝተህ ጊዜህን የምታጠፋው ወይስ መፍትሄው ላይ? የመፍትሄ ሰው መሆን አለብህ:: ቴሌቪዥን ላይ የማትፈልገው ፕሮግራም ሲመጣ ምንድን ነው የምታደርገው? ሪሞቱን አንስተህ ትቀይራለህ አይደል! አየህ አሁንም ስለችግሩ ማሰብ ስትጀምር ትፅፈውና ስለመፍትሄው ማሰብ ትጀምራለህ:: ወደ መፍትሄው ማተኮር አለብህ:: ስለዚህ ወረቀት ላይ አምስት መፍትሄዎችን ዘርዝር::

**3ኛ. ጥድፊያውን አቁም**

ከጊዜ ጋር አትታገል:: ከጊዜ ጋር ስለምትታገል ነው አብዝተህ የምታስበው፤ የምትጨነቀው:: መቼም ገጥሞህ ያውቃል ለምሳሌ ፈተና ክፍል ውስጥ አስተማሪው «አሁን አስር ደቂቃ ነው የቀራችሁ እስቲ ፈጠን ብላችሁ አሰርክቡኝ» ሲል ትደነግጣለህ:: ለምን? ያለህ አስር ደቂቃ ነው:: አንተ የቀረህ ደግሞ ብዙ ጥያቄ ነው:: ስለዚህ ትደናበራለህ:: ቶሎ ለመሥራት ስትል ጥድፊያ ውስጥ ትገባለህ:: ሁሉንም ለመመለስ ስትል የምታውቀው ሁሉ ይጠፋብሃል:: ጥድፊያ ውስጥ ትገባና «ምን ነበር አውቀዋለው እኮ» ትላለህ:: ሳታውቀው ግን ሁሉንም ገምተህ ትወጣለህ:: መጨረሻ ላይ ጥሩ ውጤት አይመጣም::

ሕይወትም እንደዛ ነው:: አንዳንዴ አንተ የምታስበው ነገር በምትፈልገው ፍጥነት አለመሳካቱ አብዝተህ እንድታስብ ያደርግሃል:: አንዳንድ ሰው እኔ በ25 ዓመቴ፣ በ26 ዓመቴ ጥሩ ቢዝነስ ገምብቼ ጥሩ ገቢ ይኖረኛል ይላል:: ልክ 25 ዓመቱን ሲያከብር ራሱን

**አሁን ግን ጊዜ መድበህለታል:: የማትፈልገውን ስልክ እንደማታነሳ ሁሉ የማትፈልገውን ሃሳብ አሁን አላስብህም፤ በኋላ እንገናኝ ትለዋለህ**

ሲያየው እንኳን ጥሩ ቢዝነስ ሊገነባ ተቀጥሮ እንኳን እየሠራ አይደለም:: እሱን የሚቀጥረው ሰው እንኳን የለም:: ግራ ይገባዋል በጣም ይጨነቃል:: አንዳንድ ሴቶች በ30 ዓመቴ አገባለሁ፤ እወልዳለሁ ብለው ያቅዱና 30 ዓመታቸው ላይ እንኳ አግብተው ሊወልዱ ይቅርና ቅርፅ ያለው የፍቅር ግንኙነት ውስጥ አይገቡም::

ሁላችንም የሆነ ነገር እንፈልግና በምንፈልገው ፍጥነት ካልተሳካ አብዝተን እናስባለን፤ አብዝተን እንጨነቃለን:: የጭንቀታችን ጉዳይ ጥድፊያ ነው:: ሕይወት ፎቅ ይመስል ስለሊፍት እናስባለን:: አቋራጭ አጭር መንገዶችን እናስባለን:: ይሄኔ እኮ ተረጋግተንና እጃችን ላይ ያለውን ነገር አስተካክለን ብንጓዝ ነገሮች ቶሎ ተስተካክለው በምንፈልገው ፍጥነት ልንደረስ እንችላለን:: ግን ጥድፊያ ላይ ነን:: ወዳጄ ከጊዜ ጋር አትወዳደር:: የፈጀውን ይፍጅ እንጂ እኔ በሂደትም ቢሆን የምፈልገበት ደረጃ እደርሳለሁ በል::

አየህ! ትዕግስት ማለት የምትችለውን ሁሉ እያደረክ የሚሮጠውን ጊዜ ማሳለፍ መቻል ነው:: ጊዜው ይሮጣል:: ከአቅምህ በላይ ነው:: አንተ ግን የምትችለውን ትሠራለህ:: በዛ ውስጥ ግን ትጠብቃለህ:: ትታገሳለህ:: አቋራጭ ማሰብ የለብህም:: አየህ! አሁን መታገስ ስትጀምር አዕምሮህ ነፃ መሆን ይጀምራል:: አቅምህን መጠቀም ትጀምራለህ:: እንደውም ነፃ ስትሆን በምትፈልገው ፍጥነት ማደግ ትችላለህ:: ጊዜን እቆጣጠረዋለሁ፤ እንዴትም ብዬ በአቋራጭ የምፈልግበት እደርሳለሁ ስትል፣ አብዝተህ ስታስብ፣ ስትጨነቅ ጊዜ ካንተ በላይ ሃያል ነው:: ይጥልሃል:: መታገስ አለብህ::

ደስ የሚለው ጊዜ የሚወስድብህ መጀመሪያ አካባቢ ነው:: መለወጥ እስከትጀምር ነው:: በጣም ጊዜ የሚወስድብህ መሠረት እስከትዘረጋ ነው:: መሠረቱ ላይ ከተጨነክ ፎቁን ወደላይ መዘርጋቱ በጣም ቀላል ነው:: ሕይወት እንደዛ ነው:: ስለዚህ አቋራጩን ተወው:: ጥድፊያውን አቁም:: አብዝተህ የምትጨነቀው፣ አብዝተህ የምታስበው ከጊዜ ጋር እየተወዳደርክ፣ እየታገልክ ስለሆነ ነው:: መታገስ አለብህ ወዳጄ!

**4ኛ.የማሰቢያ ጊዜ መድብ**

በዚህ ሰዓት ለሃያና ሰላሳ ደቂቃ አስባለው በልና ፕሮግራም ያዝ:: ልክ ያ ሰዓት ሲደርስ አላርም ሙላ:: ከዛ ማሰብ ጀምር:: የባጥ የቆጡን የፈለከውን አስብ:: ከዛ ሰላሳ ደቂቃ ሞልቶ ልክ አላርሙ ሲጮህ ወደ ሥራህ ተመለስ:: ወደራስህ ተመለስ:: አሁን ለሃሳብህ ቦታ ሰጥተኸዋል:: ስለዚህ በጣም ወሳኝ ሥራ እየሠራህ ሃሳብ አይመጣብህም:: አየህ! አንዳንድ ጊዜ ለማሰብ የሚሆን ጊዜ ስላልመደብክ ወሳኝ ሰአት ላይ ጭንቀትና ሃሳብ ይመጣል:: ልትተኛ ስትል ሃሳቦች ይመጣሉ:: እንቅልፍ አይወስድህም:: በጣም ወሳኝ ሥራ ልትሠራ ስትል ሃሳብ ይመጣብሃል::

አሁን ግን ጊዜ መድበህለታል:: የማትፈልገውን ስልክ እንደማታነሳ ሁሉ የማትፈልገውን ሃሳብ አሁን አላስብህም፤ በኋላ እንገናኝ ትለዋለህ:: ለማሰብ ቀጠሮ ማስያዝ፣ ጊዜ መመደብ በጣም የሚገርም መፍትሄ ነው:: ጭንቀትህንና አብዝቶ ማሰብህን ታቆማለህ::

**5ኛ.ትንንሽ ሃሳቦችን አስቀይስ**

አዘርግ የተባለ ደራሲ «ትንንሽ ሃሳቦች ሁሌም ትንንሽ ናቸው:: ነገር ግን የትልቁን ቦታ ይይዛሉ» ይላል:: አንዳንዴ ትንንሽ የሚባሉ ሃሳቦች አዕምሮህን ይቆጣጠሩታል:: ምንም ስለማይጠቅምህ ሰው አብዝተህ ትጨነቃለህ:: ወይም ደግሞ ከሰዎች ጋር ራስህን እያወዳደርክ ረጅም ሰዓት ታጠፋለህ:: እንደነዚህ አይነት ሃሳቦች በጣም ትንንሽ ናቸው:: ግን አዕምሮህ ላይ ትልቅ ቦታ ይይዛሉ:: ጊዜ ይሻሙብሃል:: ጉልበትህን ይመጡታል:: እንደዚህ አይነት ሃሳቦችን ማስቀየስ ነው ያለብህ:: መሸሽ ነው ያለብህ:: በድርጊትና በተግባራዊ ነገሮች መሸሽ:: ለምሳሌ ትናንሽ ሃሳቦች ወደ አዕምሮህ ሲመጡብህ ተነስተህ ቤትህን አስተካክል:: አልጋህን አንጥፍ፤ አፀዳዳ:: በአንዴ ትረሳዋለህ ያንን ሃሳብ:: ወይ ስፖርት ሥራ፤ ተራመድ ወይ ደግሞ በጎ ፍቃደኛ ሁንና የሆነ ቦታ አገልግል:: አልያ አጠገብህ ያለ ህፃን ልጅ አንሳና አጫውት:: ይህን ስታደርግ ትናንሽ ሃሳቦች ካንተ መራቅ ይጀምራሉ:: ትልልቅ ሃሳቦችን መሸሽ የለብህም:: ለትልልቅ ሃሳቦች ቁጭ ብለህ መፍትሄ ነው የምትፅፈው:: ትንንሽ ሃሳቦችን ግን መሸሽ አለብህ:: መፍትሄ የላቸውማ!

ስለዚህ ትንንሽ ሃሳቦች ሲመጡብህ «ኧረ! ይህን ማሰብ ለእኔ አይመጥንም በጣም የወረደ ሃሳብ እኮ ነው» ማለት አለብህ:: አንዳንዴ ሥራ ስለፈታህ ይሆናል እንደነዚህ አይነት ሃሳቦች አዕምሮህ ውስጥ የሚመጡት:: «ሥራ የፈታ ሰው የሰይጣን መጫወቻ ይሆናል» ይባላል:: አየህ ሥራ ስለፈታህ የማይረቡ ሃሳቦች አዕምሮህን ይሞሉታል:: ስለዚህ ወደ ሥራህ ተመለስ:: የሆነ ሥራ መሥራት ጀምር:: ያኔ ትንንሽ ሃሳቦችን ታስቀይሳቸዋለህ::

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሙስናን የሚጠየፍ ትውልድ ለመፍጠር ብዙ መሥራት ያስፈልጋል!

ሙስና በሀገራችን ስር የሰደደ ፣ አጠቃላይ በሆነው የሀገሪቱ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መስተጋብሮች ላይ ፈተና ሆኖ የተጋረጠ የከፋ ችግር ነው። ችግሩ ትናንት ላይ ብቻ ሳይሆን ዛሬም ሀገርን ከፍያለ ዋጋ እያስከፈለ የሚገኝ፤ ለጀመርነው ለውጥም ትልቅ ተግዳሮት የሆነ ነው።

የሙስና ችግር በኢትዮጵያ ከኑሮ ውድነትና ሥራ አጥነት ቀጥሎ የሀገር ደህንነት ስጋት ስለመሆኑ በመንግሥት ይፋ ከሆነ ውሎ አድሯል። በአንድ በወቅት መንግሥት ቀይ መስመር ብሎ የሰየመውን የሌብነት ተግባር ሙሰኞች ቀይ ምንጣፍ በማድረግ ሲረማመዱበት እንደነበር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መናገራቸው፤ ችግሩን ለመግታትም ብሔራዊ ፀረ ሙስና ኮሚቴ መቋቋሙም ይታወሳል።

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ ሙስና የማኅበረሰቡን የሞራል፣ የሕግና ፍትህ እሴቶች የሚያፈርስ ፣ ነባር የግብረገብ እሴቶችን የሚያደበዝዝ ፣ አጠቃላይ ለሆነው የማኅበረሰብ ህልውና አደጋ እንደሆነ ይታመናል፡፡ የተጋነነ ምኞት፣ የስግብግብነትና ራስ ወዳድነት መንፈስ የተጠናወተው እኩይ ምግባር መላበስ ነው። በጥቂቶች ብዙኃኑን የሚበክል አጥፊ ድርጊት ነው። ኢ-ፍትሐዊነት፣ የግል ጥቅም አሳዳጅነት፣ ነውረኝነት፣ አድልዎ እና የሞራል ዝቅጠት እንዲለመዱ የሚያደርግ ነው።

በመንግሥት ተቋማት እንደሚዘወተር በብዛት ቢገለጽም ከአነስተኛ ሀገር በቀል እስከ ድንበር ተሻጋሪ ኩባንያዎች እንዲሁም መንግሥታዊ ባልሆኑና በግል ድርጅቶችም የሚስተዋል የከፋ ችግር ነው። ድህነትን የሚያባብስ ፣ ሰብዓዊ መብትና ክብርን የሚጋፋ፣ ዕድገትን የሚኀትት ፣ በሀገር ውስጥ እና በሀገራት መካከል ግጭት የሚቀሰቅስ ፤ የመንግሥትን ቅቡልነት እና ዴሞክራሲን የሚፈታተን ነው ።

ጠንክሮ መሥራትን የሚኮንን፣ ሳይሰሩ መብላትን የሚያጀግን፣ የአጋርነትን ሞራል የሚሰብር፣ ሀገርን ለውጫዊ ደህንነት ስጋት አደጋ የሚጥል፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን የሚያቀጭጭ፣ ውስጣዊ ሰላምንና መረጋጋትን የሚፈትን፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እና አጠቃላይ ዘላቂ ልማትን የሚገታ ነው። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ሀገራት ሙስና ይዞት ሊመጣ የሚችለው መዘዝ የከፋ እንደሚሆን ይታመናል።

የሙስና ችግር ቀደም ባለው ሥርዓት ምን ያህል ሀገር እና ሕዝብን መጠነ ሰፊ ዋጋ እንዳስከፈሉ የሚታወስ ነው። የመንግሥት ባለስልጣናት በተናጠል እና በተደራጀ መንገድ የሀገርን ሀብት ከመቀራመት ባለፈ፤ ሀብትን ከሀገር በማስወጣት ወንጀሎች በስፋት ሲሳተፉ መቆየታቸውም የአደባባይ ምስጢር ነው። ችግሩ በለውጡ ማግስትም ለሀገር ህልውና ተጨባጭ አደጋ በመሆን ሀገርን እና ሕዝብን ብዙ ያልተገባ ዋጋ አስከፍሏል።

ችግሩ ዛሬም ቢሆን፤ በታችኛው መዋቅርና በመካከለኛ ደረጃ ባሉ ተቋማት ሠራተኞች ላይ የሚስተዋል ነው ፤ በተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አገልግሎት ፍለጋ የሚሄዱ ዜጎች ከሙስና ጋር በተያያዘ በሚያጋጥሟቸው እንግልቶች ዙሪያ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲጮኹ መስማት የተለመደ ነው። አገልግሎቶችን ለማግኘት ተጨማሪ ክፍያ የሚጠየቁበት ሁኔታም እንዳለ በስፋት ሲነሳ ይስተዋላል።

ችግሩን ለመቅረፍ መንግሥት በየወቅቱ የተለያዩ ርምጃዎችን እየወሰደ ቢሆንም፤ ከችግሩ ስፋት እና ጥልቀት ከዚያም ባለፈ ወንጀሉ ዕለት ተዕለት እየተወሳሰበ መምጣቱ የመከላከል ሥራውን ፈትኖታል። በተለይም ቀደም ባለው ጊዜ በሙስና ዙሪያ የነበረው የተዛባ አተያይ አሁን ላይ ችግሩ እንዲገነግን ፣ ሕዝቡም ከሙስና ጋር እንዲላመድ እና ችግሩን አቅሎ እንዲያይ አድርጎታል።

እንደ ሀገር ሁለንተናዊ ብልፅግናን እውን ለማድረግ ከፍ ባለ መነቃቃት ውስጥ ባለችው ሀገራችን ሙስና ትልቁ የለውጡ ፈተና መሆኑ የማይቀር ነው። የመከላከሉን ሥራ ለመንግሥት ብቻ ትቶ ፤ መንግሥት እንዳደረገ ያድርገው የሚባል አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ የሁሉንም ዜጋ ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው።

ችግሩን ለዘለቄታው ለመከላከል ፣ በተለይም ሀገር ተረካቢው ትውልድ ሙስናን የሚጠየፍ ሆኖ እንዲወጣ ብዙ መሥራት እና መድከም ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ወላጆች ፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፣ የፖለቲካ ተዋናዮች ... ወዘተ ትልቁን ኃላፊነት ወስደው ሊንቀሳቀሱ ይገባል።

ችግሩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የመንግሥት እና የሕዝብ ተቋማትም የሙስናን አስከፊነት ማኅበረሰቡ እንዲገነዘብ ከማስቻል ጀምሮ የአሠራር ህጋዊነት እና ተጠያቂነትን ማስፈን፤ በቴክኖሎጂ የታገዙ የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት ሙስናን ለመከላከል የተጀመሩ ሥራዎችን በኃላፊነት መንፈስ በቁርጠኝነት ማስቀጠል ይኖርባቸዋል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በስፖርት ማህበራት ምርጫ ላይ ተጠያቂነት ሊኖር ይገባል!

**ልዑል ከካምቦሎጆ**

የኢትዮጵያን ስፖርት ወደ ኋላ እየጎተቱ ከሚገኙ ጉዳዮች አንዱ የስፖርት ማህበራትና ፌዴሬሽኖች አስተዳደራዊ ጉዳይ የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል። አስተዳደራዊ ጉዳይ ሲባል ደግሞ በቀጥታ የሚገናኘው ስፖርቱን በፍቃደኝነት ለመምራትና ለማገልገል ካለ ምንም ክፍያ ወደ ኃላፊነት ከሚመጡ ሰዎች ጋር ነው:: እነዚህ ሰዎች ስፖርቱን በመሪነት ለማገልገል ወደ ኃላፊነት የሚመጡት የስፖርት ማህበራትና ፌዴሬሽኖች በሚያደርጉት ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በሚደረጉ የፕሬዚዳንትና ሥራ አስፈፃሚ አባላት ምርጫ መሆኑ ይታወቃል::

በዚህ መንገድ ተመርጠው ወደ ኃላፊነት የሚመጡ ሰዎች ስፖርቱን ለማገልገል እውቀት፣ ልምድና ገንዘባቸውን ለማውጣት ፍቃደኛ የሆኑ ናቸው የሚል በመርህ ደረጃ የተቀመጠ ነገር አለ:: ነገር ግን እነዚህ ሰዎች አብዛኞቹ በትክክል በዚህ መርህ መሰረት ስፖርቱን ለማገልገል ነው ወደ ኃላፊነት የሚመጡት? የሚለው ጥያቄ የብዙዎች ነው::

በሀገር አቀፍ፣ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የስፖርት ማህበራትና ፌዴሬሽኖች የተለያዩ ስፖርቶችን ለማገልገል ተመርጠው ወደ ኃላፊነት ከሚመጡ ግለሰቦች መካከል በትክክልም እውቀት፣ ልምድና ገንዘባቸውን ለማውጣትና ዘርፉን ለማሳደግ የሚጥሩ የሉም ማለት አይቻልም:: በተቃራኒው እውቀቱም፣ ልምዱም የሌላቸውና እንኳን የገዛ ገንዘባቸውን ሊያወጡ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ተጠቅመው ኪሳቸውን ለመሙላት ሲጥሩ የሚታዩትን ቤቱ ይቁጠራቸው:: በእነዚህ ሰዎች ላይ ግን መፍረድ አይቻልም:: ከእነሱ ይልቅ ተጠያቂ መሆን ያለበት መርጦ ለኃላፊነት ያበቃቸው ጠቅላላ ጉባዔ ነው:: እንዲመረጡ እጩ አድርጎ የሚያቀርባቸው አካልም ከዚህ ተጠያቂነት ሊያመልጥ አይችልም::

ከሀገር አቀፍ እስከ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የተለያዩ ስፖርት ማህበራትና ፌዴሬሽኖች በኃላፊነት እያገለገሉ የሚገኙና ወደ ኃላፊነት ለመምጣት መንገድ ላይ የሚገኙ አብዛኞቹ ግለሰቦች ከስፖርቱ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው፣ እውቀቱም ልምዱም ያልደረሰባቸው እንደሆኑ የአደባባይ ሀቅ ነው:: የኢትዮጵያን ስፖርት መቀየርና ማሳደግ ከተፈለገ ይህን መሸፋፈን አያስፈልግም::

ሰሞኑን የአዲስ አበባን እግር ኳስ ፌዴሬሽን ለመምራት የተመረጡ ግለሰቦችን ማየት ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው:: የከተማዋ ፌዴሬሽንን ለመምራት ሁለት ሴት አርቲስቶች በምክትል ፕሬዚዳንትነትና በአቃቤ ንዋይነት መመረጣቸው ዛሬም ድረስ አነጋጋሪና በብዙዎች እየተተቸ የሚገኝ ጉዳይ ነው:: ሁለቱ አርቲስቶች ከዚህ ቀደም ከእግር ኳስ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም:: ስፖርቱን ለመምራት እውቀቱም ይሁን ልምዱ እንደሌላቸው ለማንም ግልፅ ነው:: ታዲያ ስፖርቱን በምን መልኩ እንዲያገለግሉ ተመረጡ? የብዙዎች ጥያቄ ነው:: የስፖርት ቤተሰቡ ይህን ጥያቄ በማንሳቱ አንዳንዶች ጉዳዩን ‹‹ሴት ስለሆኑ ነው›› በሚል ለመጠምዘዝ ይሞክራሉ:: ጥያቄው ሴትነታቸው ወይም ፆታ ላይ አይደለም:: ስፖርቱን ለመምራት እንዴት መጡ የሚለው ነው:: እንዲመረጡ የወከላቸውና የመረጣቸው ጉባዔ ምን አይቶ፣ ምን መዝኖ ነው? እውነት የአዲስ አበባን እግር ኳስ ለመምራት ከአርቲስቶቹ ይልቅ ለስፖርቱ ቅርብ የሆኑ እውቀቱም፣ ልምዱም ያላቸው ሰዎች ጠፍተው ነው?

ይህ ብቻ አይደለም ጥያቄው፣ ከተመረጡት አርቲስቶች አንዷ ስለ ምርጫው እንደማታውቅ በማህበራዊ ትስስር ገጿ ላይ አሳውቃለች። አርቲስቷ በፌስቡክ የማህበራዊ ትስስር ገጿ ባሰፈረችው መልዕክት “መመረጤን ያወቅኩት እኔም በማህበራዊ ሚዲያ ተሰራጭቶ ነው›› በማለት ምርጫው ሲደረግ በቦታውም እንዳልነበረችና ጥሪም እንዳልደረሳት በመግለፅ፤ በስፖርቱ ላይ ምን እየተሰራ እንደሚገኝ እንድንጠይቅ አድርጋናለች:: በዚህ ልትደነቅ ይገባታል:: በማያውቁትና በማይወጡት ጉዳይ ላይ ኃላፊነት ስለተሰጠ ብቻ መቀበል እንደማይገባ ትምህርት ነው:: የአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የአንድ ከተማ ጉዳይ አይደለም፣ እንደ ሀገር ያለው ተፅዕኖ ከፍ ያለ ነው:: አዲስ አበባ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ኢትዮጵያ ቡና፣ መቻል፣ ኢትዮ ኤሌክትሪክ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ሌሎችም በሚሊዮን የሚቆጠር ደጋፊ ያላቸው የሀገሪቱ ትልልቅ ክለቦች መዲና መሆኗ መረሳት የለበትም:: እነዚህ ክለቦች በኢትዮጵያ እግር ኳስ ላይ ትልቅ አሻራ የሚያሳርፉ በብሔራዊ ቡድንም ድርሻቸው የጎላ መሆኑን ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል:: የአዲስ አበባን እግር ኳስ መምራት ማለት ቀላል ነገር አይደለም::

> **ስፖርቱን በመሪነት ለማገልገል ተወክለው ወደ ምርጫ የሚመጡ ሰዎች የግዴታ ስፖርተኛ ወይም ከዚህ ቀደም በስፖርት ያለፉ ይሁኑ ማለት አይደለም። ቢያንስ ስፖርቱ ምን ይፈልጋል፤ አሁን የተሳሳተው ነገር ወይም የስፖርቱ ችግር ምንድነው? የሚለውን ጉዳይ አውቀውና ተረድተው የማስተካከል አቅም እንዲሁም የመምራት ችሎታ ያላቸው ሲሆኑ ይገባል**

ይህ የአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፌዝ ብቻ አይደለም:: እንደ ሀገር በስፖርቱ ላይ እየታየ የሚገኘው ኪሳራ ነፀብራቅ ነው:: ከዚህ ቀደም ጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ ይሁንታው ሳይጠየቅ በሌለበትና በማያውቀው ሁኔታ የኦሊምፒክ ኮሚቴ ምክትል ፕሬዚዳንት ተደርጎ መመረጡን ከራሱ አንደበት ሰምተን ጉድ ብለናል:: በብሔራዊም ይሁን በክልልና ከተማ አስተዳደር ደረጃ ያሉ የተለያዩ የስፖርት ማህበራትና ፌዴሬሽኖችን የሚመሩ ሰዎች የመጡበትና እየመጡ የሚገኙበት መንገድ ከዚህ የተለየ አይደለም::

በዚህ መንገድ የሚመጡ ሰዎች ናቸው ስፖርቱን ወደ ቁልቁለት ከመስደዳቸው ባሻገር ስፖርቱ ዘወትር ከውዝግብ እንዳይፀዳ እያደረጉ የሚገኙት:: በአንድ ወቅት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በፓርላማ ንግግራቸው ላይ “ኢትዮጵያ ውስጥ ስፖርት የለም፣ በሌለ ስፖርት ውስጥ ግን ሽኩቻው አለ:: በሌሎች ሀገራት ስፖርቱ አለ ውዝግቡ ግን የለም” በማለት መናገራቸው ይታወሳል። የዚህ ውዝግብ ምንጭ ስፖርቱን ለመምራት እውቀቱም፣ ልምዱም የሌላቸው ገንዘባቸውን አውጥተው ለማገልገል ሳይሆን ለመገልገል የሚመጡ ሰዎች መሆናቸው የሚታበይ አይደለም::

ስፖርቱን በመሪነት ለማገልገል ተወክለው ወደ ምርጫ የሚመጡ ሰዎች የግዴታ ስፖርተኛ ወይም ከዚህ ቀደም በስፖርት ያለፉ ይሁኑ ማለት አይደለም። ቢያንስ ስፖርቱ ምን ይፈልጋል፤ አሁን የተሳሳተው ነገር ወይም የስፖርቱ ችግር ምንድነው? የሚለውን ጉዳይ አውቀውና ተረድተው የማስተካከል አቅም እንዲሁም የመምራት ችሎታ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚልኳቸው ተወካዮች እንዲህ አይነት ሰዎች መሆናቸውን የማረጋገጥ ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ሊያውቁ ይገባል።

ስፖርቱን ለመምራት ተወክለው የሚመጡ ሰዎች ጋር ብቻ ግን አይደለም ችግር ያለው። በምርጫ ወቅት ድምፅ እንዲሰጡ ከክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና የተለያዩ ስፖርት ተቋማት የሚወከሉ ግለሰቦች ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ድምፅ የሚሰጡት ሰው ስፖርቱን ለማገልገል ተገቢ መሆኑን የማረጋገጥ አደራ እንዳለባቸው ማስታወስ ተገቢ ነው። ምርጫዎች ላይ ድምፆች እንደሚገዙና እንደሚሸጡ ለስፖርት ቤተሰቡ የተሸሸገ ጉዳይ አለመሆኑን ማደባበስ አያስፈልግም። ስለዚህ ስፖርቱን ለማገልገል እጩ አድርጎ ሰዎችን ከሚያቀርበው አካል ጀምሮ፣ ድምፅ ለመስጠት ተወክለው በምርጫ ጉባዔ ላይ የሚመጡ ሰዎች እንዲሁም ለስፖርቱ የማይበጁ ሰዎች ወደ ኃላፊነት እንዲመጡ ይሁንታ የሚሰጠው አጠቃላይ ጉባዔ የሕዝብ አደራውን ሳይወጣ ሲቀር የሚጠየቅበት መንገድ ሊኖር ይገባል::

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## አሁን አየ ዓይኔ

ያለፉት ጊዜያት ብዙ ለሚሻው ታዳጊ መልከ ብዙ ሆነው አልፈዋል። እስከዛሬ በጨለማ ሲኖር፣ ሲራመድ ነበር። እስከአሁን ሳይወድ በግድ ከትምህርቱ ታቅቧል፣ ፍጹም ሳይገባውም በብቸኝነት ቆዝሟል፣ በትካዜ አንገት ደፍቷል



ወጣት ወጋየሁ ፈጠነ

ፎቶ- በሃዲስ አብረሃ

መልካምሥራ አፈወርቅ

### እንደመነሻ ...

ትንሹን ልጅ አጥብቃ የያዘችው የኩፍኝ ሕመም እንደዋዛ ጨክናበት ከርማለች። እሱን ጨምሮ የእህቶቹ ፊትና ገላ በሽፍታ ተውርሷል። በእነሱ ግን ክንዷ አልበረታም። እንደነገሩ ከራርማ ተሽልማ ሄዳለች። ሕመሙ ሁሌም በልጆች ላይ ተለምዷልና ማንም ነገሬ ያለው የለም።

ወጋየሁ በኩፍኝ ጉዳይ እንደተቸገረ ነው። የገላው ምልክት ውሎ አድሮ ቢከስምም ሕመሙ አልተወውም። ችግሩ በዚህ ብቻ አልበቃም። ከቀናት በኋላ ዓይኖቹ ሙሉ ለሙሉ ከብርሃን መጋረዳቸው ታወቀ። ትንሹ ልጅ እንደልቡ ማየትና መራመድ ተሳነው።

ኩፍኝ ማለት ለአካባቢው ብርቅ ሆኖ አያውቅም። ሁሌም ልጆች ታመው ይድኑበታል። እስከዛሬም እንደወግ ባሕሉ የተለመደው ተደርጎ ኩፍኝዋ በስንብት ትሸኝ ነበር። በወጋየሁ የሆነው ግን አዲስና ያልተለመደ ነው። ከገላው ለቃ በዓይኖቹ ላይ መዋሏ ሁኔታውን አስደንጋጭ አድርጎታል። አጋጣሚው ቤተሰቡን ሲያሳስብ ሲያስጨንቅ ከረመ። የዛኔ በአካባቢው የረባ ሕክምና አልነበረም። የሐረሯ አንጫር ወረዳ ‹‹በዴ›› ከተማም ሕክምናውን ችላ የምታሽንፈው አልሆነም።

### ጥያቄው ...

ውሎ አድሮ ወጋየሁ ዓይኑን የጋረደው ነጭ ነገር ጥቂት የገፈፈ መሰለ። ይህኔ ትንሹ ልጅ በግምት መራመድና ሰው መለየት ጀመረ። በአቅሙም የቻለውን ለማድረግ እየሞከረ ቆየ። እንዲህ መሆኑ ግን እይታውን አልመለሰም። እኩዮቹ ትምህርት ቤት ሲገቡ እሱ ከዕድሉ ታቅቦ ከቤት ሊውል ግድ አለው። ይህ አጋጣሚ ለወጋየሁ ቀላል አልሆነም።

የእሱ ከቤት መቅረት ሆድ ያስባሰው ብላቴና ለምን ሲል አባቱን ደጋግሞ ጠየቀ። ምላሹ አጭርና ግልጽ ነበር። ወጋየሁ ዓይኖቹ ከእይታ ተጋርደዋል። ከእኩዮቹ እኩል ተቀምጦ ቀለምና ቁጥር መለየት አይቻለውም። ብቸኛው አባወራ ባለቤታቸውን በሞት አጥተዋል። ከእሱ በላይ ብዙ የሕይወት ጥያቄዎች ይጠብቋቸዋል።

አባት በብዙ ምክንያት ልጃቸውን ወደ ተሻለ ሕክምና ለመወሰድ አልፈጠኑም። የቤተሰቡ ሙሉ ኃላፊነት በእሳቸው ትከሻ ወድቋልና ተቸግረዋል። እንዲያም ሆኖ ወጋየሁ ዝም አላለም። አባቱ እንዲያሳክሙት ይወተውታል። እሳቸው ስለእሱ ተስፋ ቆርጠዋል። ዓይኑ ታክሞ እንደማይድን እየነገሩት ነው። የአካባቢው ግንዛቤና የአቅሙ ጉዳይ ደግሞ ማንንም የሚያስወቅስ አልነበረም ።

በጊዜው ኩፍኝ ይሏት ሕመም የበዛ ችግር አላት ብሎ የሚያምን የለም። ጊዜው እየገፋ፣ ቀኑ እየነጎደ ነው። የወጋየሁ ባልንጀሮች ከትምህርት ውለው ይገባሉ። የትንሹ ልጅ ጥያቄ አላቆመም። የትምህርት ጉጉቱ ደጋግሞ ለምን ሲል ጥያቄውን እንዲገፋበት አስገድዷል።

### በሐኪሞች ፊት...

ወጋየሁ ዓይኖቹ ክፉኛ መታመማቸው ሲገባው በአባቱ ላይ ጫና ማሳደር ያዘ። ሁሌም መታከም እንዳለበት እየጨቀጨቀ አስጨነቃቸው። አሁን አባት ጥያቄውን ችላ ብለው ዝም አላሉም። ከሐረር ወጣ ብላ ወደምትገኝ መተሐራ ከተማ ወሰዱት። ከስፍራው ደርሶ ምርመራው ተካሄደ። ጉዳዩ በሆስፒታሉ አቅም የሚቻል አልሆነም። ወደተሻለ ሕክምና ተጻፈለት።

ቀጣዩ ጉዞ አዳማ ላይ ሆነ። የወጋየሁ ሕክምናና ውጤት ተመሳሳይ ሆኖ ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል ሊላክ ግድ አለ። በሚሊኒየሙ 2000 ዓ.ም። አባትና ልጅ አዲስ አበባ ከሆስፒታሉ ደርሰው ሕክምናው ተጀመረ። የተገኘው ውጤት ከቀድሞዎቹ ምርመራዎች የተለየ ነበር። የወጋየሁ ሁለቱም ዓይኖች በዓይን ብሌን ጠባሳ መጎዳታቸው ተረጋገጠ። ይህ እውነት ለእንግዶቹ አባትና ልጅ አዲስ ቃል ነበር። ከዚህ ቀድሞ ዓይኖች በጠባሳ እንደሚጎዱ ሰምተው አያውቁም።

በወቅቱ ወጋየሁ ልጅ ቢሆንም ሐኪሞቹ ስለ ዓይን ብሌን ንቅላ ተከላ በትኩረት ማውራታቸውን ያስታውሳል። ብዙ ታካሚዎች እንዳሉ፣ ብሌኑ ከሌሎች እንደሚለገስና ለጋሾቹም በቂ አለመሆናቸውን ጭምር ሰምቷል።

ስለሕክምናው ጥቂት ግንዛቤ የጨበጠው ልጅ የሰማውን በውስጡ ይዞ ዓይኖቹን መታከምና መዳን እንዳለበት ወሰነ። ከታሰበው ለመድረስ መመዝገብና ወረፋ መያዝ የግድ ይላል። ወጋየሁ ሙሉ ምዝገባውን አጠናቆ ወረፋውን መጠበቅ ጀመረ። ተመልሶ ወደ ትውልድ ሀገሩ አልሄደም። የክርስትና አባቱ አዲስ አበባ ናቸው። ኑሮው በቤታቸው ሆነ።

### ብርሃን አልባው ጉዞ...

ወጋየሁ ውሎአድሮ የመንገዱን ፈታኝ እርምጃዎች መጋፈጥ ያዘ። እግሮቹ ሜዳ ገደሉን፣ ጉድጓድ፣ ጉድባውን ተላመዱት። እየወደቀ፣ እየተነሳ፣ እየሳቀ፣ እያዘነ የብርሃን አልባውን ጎዳና ተራመደበት። አንዳንዴ የአንድ ዓይኑ ፈዛዛ ብዥታ ለጉዞው ያግዘዋል። ያለነጭ በትር ባልተመቸው መንገድ ይመላለሳል።

በመንገዱ ጉቶው፣ ድንጋዩ፣ ግንዱ ይመተዋል። ሲያደናቅፈው ይወድቃል። ሲነሳ ተስፋ አይቆርጥም። የተመታ እግሩን፣ የደማ ጉልበቱን እያሻሸ ጉዞውን ይቀጥላል። ደግሞ በሌላ ቀን ከሌላ መንገድ ይገኛል። አካባቢው ለማንም እግረኛ አያመችም።

ወጋየሁ ብዥ እያለበት በግምት መራመድ ልምዱ ነው። መንገዱ አያዝንለትም። ሳሩ፣ ሰርዶው ይጠልፈዋል። ድንጋይ፣ ጠጠሩ ይመታዋል። የተላጠውን የእግሩን አንጓ አስታሞ፣ ራሱን በራሱ አባብሎ ከወደቀበት ይነሳል። እንደገና መንገዱን መጥኖ፣ ግራ ቀኙን ገምቶ ጉዞ ይጀምራል። ከፊቱ ስለተጎለተው ትልቅ ድንጋይ፣ ስለተቆፈረው ጥልቅ ጉድጓድ አያውቅም።

ጓደኞቹ ከትምህርት ቤት ሲመለሱ እሱ ተቀምጦ ይቆያቸዋል። ሳቅ ጨዋታው ይደራል። ስለውሏቸው ያወጉታል። ስላሰበው ይነግራቸዋል። በወጋየሁ ውስጠት ያለው የኪነጥበብ ፍቅር ለሙዚቃው ያደላል። የግጥም ተሰጥዖው ፈክቶ ይወጣል። ችሎታውን የሚያደንቁለት በቅርበት ያሞግሱታል። ይህን የሚረዳው ታዳጊ ብርሃን አልባ መሆኑን አሳስቦት አያውቅም። ከእነሱ አንዳች ሳያጎድል መሳተፉ ያበረታዋል።

ወጋየሁ ነገሮችን ለመድፈር ወደ ኋላ አይልም። ጓደኞቹ የሚያደርጉትን ሁሉ ይሞክራል። ቢገፉት፣ ቢገፈትሩት አይወድቅም። አብሯቸው እግር ኳስ ይጫወታል፣ ቴሌቪዥኑ ባይታየውም ይዝናናበታል። እንደውም አንዳንዴ ባልንጀሮቹ የዓይኑን ጉዳይ እስኪረሱት ይዘናጋሉ። ከእነሱ ያለው ቅርበት ያለልዩነት በመሆኑ ለእገዛ እጃቸውን ዘርግተውለት አያውቁም።

### የሚሊኒየሙ ስጦታ...

በሚሊኒየሙ መጨረሻ አካባቢ ወጋየሁ ከሆስፒታሉ ድንገቴ ጥሪ ደረሰው። የመጠራቱ ምክንያት በለጋሾች በተገኘው ብሌን በአንድ ዓይኑ ላይ ንቅላ ተከላውን ለማካሄድ ነበር። በወጋየሁ ውስጠት ያደረው ስሜት የተለየ ሆነ። ይህ እውነት ለእሱ ከስጦታ በላይ ነው።

ያለፉት ጊዜያት ብዙ ለሚሻው ታዳጊ መልከ ብዙ ሆነው አልፈዋል። እስከዛሬ በጨለማ ሲኖር፣ ሲራመድ ነበር። እስከአሁን ሳይወድ በግድ ከትምህርቱ ታቅቧል፣ ፍጹም ሳይገባውም በብቸኝነት ቆዝሟል፣ በትካዜ አንገት ደፍቷል።

ዛሬ ደግሞ ዓለምን ተሰናብተው ካለፉ ልበ ቀናዎች ‹‹እነሆ!›› የተባለውን በረከት ሊቀበል ነው። ደስታ፣ ጉጉትና ብሩህ ተስፋ በፊቱ ተመላለሱ። በቀላሉ ሊገልጸው ከማይችለው ስሜት ጋር እጅ ለእጅ ተጨባበጠ። ወጋየሁ በሆስፒታሉ ተገኝቶ ከሐኪሙ ፊት ቀረበ። ሙሉ ምርመራ ተደርጎለት የብርሃን መንገዱን ለመጀመር ተዘጋጀ።

የወጋየሁ ሁለቱም ዓይኖች ከእይታና ብርሃን የታቀቡ ናቸው። ለሕክምናው የቀደመውን ዕድል ያገኘው ግን አንደኛው ዓይኑ ብቻ ነበር። በሕክምናው ተሞክሮ በአንድ ጊዜ ሁለቱንም መሥራት አይቻልም። የሚሆነው ሊሆን ጊዜው ደርሷል። ብርሃን ናፋቂው ልጅ ግራ ዓይኑን ለንቅለ ተከላው ሰጥቶ ውጤቱን በጉጉት ጠበቀ።

### ተናፋቂው ቀን...

በዕለተ ቀጠሮው የሕክምናው ሂደት በልዩ ስኬት ተጠናቀቀ። ወጋየሁ በሆስፒታሉ ለስምንት ቀናት ተኝቶ ነበር። እሽጉ ተፈቶ ቅኝት እንደጀመረ ዓይኑ ማየት የሚሻውን ሁሉ አነጣጠረ። አባቱን፣ እህት ወንድሞቹን፣ ጓደኞቹን ለማስተዋል፣ በአካል ለመተዋወቅ ናፈቀ። ወዲያው የልቡ ሀሳብ ሙሉ ሲሆን ተሰማው።

የብርሃንና የጨለማን ልዩነት ለመረዳት አፍታ አልቆየም። ቀድሞ ፈዛዛ የሚመስለው ቁስ ፍክት፣ ድምቅ ብሎ ታየው። የተፈጥሮን ውበት ለማድነቅ አልዘገየም። በሚያየው እውነት አብዝቶ ተገረመ። የሰዎች ቁንጅና፣ የከተማው ውበት፣ የፎቆቹ ብዛት አስደመመው። ሁሉም አስቀድሞ ከነበረው ግምት የተለዩ ሆኑበት።

በመንገዱ ዞር ብሎ አንድ ነገር ላይ አተኮረ። በትልቁ የተለጠፈ ማስታወቂያ ነበር። እየገረመው ከጽሑፉ ነጥሎ ምሥሉ ላይ አፈጠጠ። ስላልተማረ ፊደላቱን ማንበብ አልቻለም። እንዲያም ቢሆን ደስ አለው።

### አዲስ ትውውቅ ከቤተሰብ ጋር

ከጊዜያት በኋላ ወደ ሐረር ተመለሰ። የናፈቃቸውን ሁሉ እንደ አዲስ አወቃቸው። ከመዳሰስ፣ በድምፅ ከመለየት አልፎ በትኩረት ያስተዋላቸው ያዘ። አባቱን፣ አክስት አጎቶቹን አተኩሮ አያቸው። እህቶቹን በአካል ባገኘ ጊዜ መልከ ቁመናቸው ተለየበት። እስከዛሬ በአዕምሮው እንደሳላቸው አይደሉም። ሁሉም ቀያዮች፣ ውቦች ሆኑበት። መለስ ብሎ የራሱን ፊት አስተዋለ። ከእነሱ ጋር አይመስልም። መልኩ ጠቆር ይላል።

ወጋየሁ ዓይን ይሉት በረከት የሕይወት ዋልታ፣ የመኖር መሠረት መሆኑን ተረዳ። የእግሮቹ ላይ ጠባሳ፣ ያሳለፋቸው ክፉ ደግ ጊዜያት የማንነቱ ማስታወሻዎች ናቸው። ዛሬ የ‹‹አሁን አየ ዓይኔ›› ዜማ ለእሱ ትርጉሙ ይለያል።

### ያሰብኩት ተሳካ...ያለምኩት ደረሰ

ወጋየሁ አሁን የልቡ ደርሷል። ያሰበው ተሳክቷል። ለዓመታት የተነፈገውን ትምህርት ‹‹ሀ..›› ብሎ ሊጀምር ደብተር እስክሪብቶ አዘጋጅቷል። የዓመታት ጥያቄው መልስ ሊያገኝ ነው። እኩያ ጓደኞቹ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል። እነሱ የደረሱበት፣ እሱ ወደ ኋላ የቀረበት ጊዜ አላስቆጨውም። በሆነለት ሁሉ ፈጣሪውን አመስግኖ ለትምህርት ራሱን አዘጋጀ።

አሁን ተማሪው ወጋየሁ ቀለም ሲቆጥር፣ ፊደል ሲለይ ይውላል። ጎን ለጎን የሕክምና ክትትሉን አልተወም። ከሌሎች እኩል በትኩረት ይማራል። በበሰለ አዕምሮ፣ በመልካም ዕድሜ ላይ የያዘው ትምህርት እያዋጣው ነው።

### ከስድስት ዓመታት በኋላ...

ወጋየሁ ካሳለፈው የጨለማ ጉዞ ተላቆ በአንድ ዓይኑ የብርሃን ሕይወትን ከጀመረ ስድስት ዓመታት ተቆጥረዋል። በእነዚህ ጊዜያት የትምህርትን ጣዕም ለይቷል። የብርሃንና ጨለማን ልዩነትን አውቋል። ከምንም በላይ ሊያያቸው የናፈቃቸውን ቤተሰቦቹን በአካል አግኝቶ ፍቅሩን ተወጥቷል። ያለፉት ዓመታት ለእሱ የአዲስ ምዕራፍ አዲስ ዓለም ነበሩ።

2006 ዓ.ም። ይህ ዓመትና ወጋየሁ የተገናኙት ሕይወት የሰጠችውን ሁለተኛ ዕድል በሚጠቀምበት አጋጣሚ ነበር። አሁን የቀኝ ዓይኑ ብርሃን የሚመለስበት ጊዜው ደርሷል። ንቀላ ተከላው እንደተጠናቀቀ ወጋየሁ በሁለቱም ዓይኖቹ ሙሉ እይታውን ቀጠለ። ትምህርቱን በወጉ የያዘው ወጣት ከሥነጽሑፍ ዝንባሌው ሲገናኝ አልዘገየም። እያሰባቸው ያጣቸው፣ እንደ ጓደኞቹ ያልከወናቸው ስኬቶች መምጣት ጀምረዋል።

ወጋየሁ እስከዛሬ ያለፉትን ፍላጎቶች እግር በእግር አሳዶ ያዛቸው። የውስጡ ስሜት ራሱን ፈልጎ ለማግኘት አገዘው። በሚኒሚዲያውና መድረክ በመምራት ታዋቂ ሆነ። አሁን ታስሮ የቆየው ፍላጎቱ ከብርሃን መንገዱ ተገናኝቷል። ፈተና ሆኖ የቆየበት ታሪክ በእሱ ጥረትና ትግል እየታለፈ ነው። ሁለቱም ዓይኖቹ በመነጽር እየታገዙ አጥርተው ያያሉ።

### ብርሃናማው ዛሬ ...

ወጋየሁ ዛሬ በወጣትነት ዕድሜ ላይ ነው። ልጅነቱን ሙሉ ሲመኘው ከነበረው ፍላጎቱ ተገናኝቷል። በማርኬቲንግና ማኔጅመንት ዘርፍ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ነው። እንደእሱ የዓይን ብሌን ተለግሰው ብርሃን ካገኙ ወገኖች ጋር ማኅበር በማቋቋም የድርሻውን ይወጣል። የዛሬ ሕይወቱ ከቀድሞ ማንነቱ የተሻለ መሆኑ ሀሳቡን በተግባር እንዲከውን ምክንያት ሆኗል። በዚህ እውነታ የወጋየሁ ደስታ ልዩ ነው። እሱ የወደፊት የሕይወት አቅጣጫው በዚህ የምዕራፍ መንገድ ተጋምዶ እንደሚቀጥል ያምናል።

### መልዕክት-ለሌሎች

የወጣቱ ጥንካሬ በእጅጉ አስደንቆኛል። በማንነቱ ውስጥ የሰው ልጅን ፍላጎትና ስኬት አስተውዬ እያየሁበት ነው። ከወጋየሁ ፈጠነ ጋር ከመሰነባበቴ በፊት ለአንባቢያን የማደርስለት መልዕክት እንዳለው ጠየኩት። ለምላሹም አልዘገየም።

እሱና መሰል ወገኖች ዛሬ ለደረሱበት የብርሃን ዓለም መሠረቱ የዓይን ብሌን ልገሳ ነው። ይህ ልገሳ የሚገኘው ደግሞ ከበጎ አድራጊ ግለሰቦች እንደሆነ ይታወቃል። በርካቶች ይህን ታላቅ ስጦታ ለማበርከት ፍላጎት ቢኖራቸውም ደፍረው አይወስኑም።

ማንም እንደሚያውቀው ስጦታው በሕይወት ካለፉ በኋላ የሚበረከት ነው። ይህ እውነት በሕይወት ላሉት ብርሃን አልባዎች ሕይወትን እንደመስጠት ይቆጠራል። እናም ሁሉም ብርሃን ለመለገስ ልቡ ይፍቀድ ብሏል። ወጋየሁ በመልዕክቱ።

# ማህደረ ጤና

# ወጌሻ ማነው፤ ሥራውስ ምንድን ነው?

አስናቀ ፀጋዬ

አያሌው ቦሳ/ለዚህ ፅሁፍ ስሙ የተቀየረ/ በሲዳማ ክልል አርቤ ጎና ወረዳ ነዋሪ ነው:: እንደ ብዙዎቹ የአርቤ ጎና ወረዳ ወጣቶች ሁሉ አያሌውም ጫካ ገብቶ የተቆራረጡ ግንዲላዎችን ወደ ተሸከርካሪ ተሸክሞ በመጫን በሚከፈለው ገንዘብ ነበር ራሱንና ቤተሰቡን የሚያስተዳድረው:: ትዳር መስርቶ ጎጆ ቀልሶ አንድ ልጅ ወልዶ መኖር ከጀመረ በኋላም በዚሁ ስራ ገፍቶበታል:: ባለቤቱንና አንድ ሴት ልጁን የሚያስተዳድረውም ግንዲላ ወደ ተሸከርካሪ ተሸክሞ በመጫን ነበር:: አንደ ልማዱ አንድ ቀን ወደ ጫካ ገብቶ የተለመደ ስራውን እያከናወነ እያለ ነበር ድንገት ሳያስበው የተናደ ግንድላ ሰውነቱ ላይ ያረፈበት::

ሲነቃ ራሱን ያገኘው ጀርባው፣ ወገቡና እግሩ ተሰባብሮ ሃዋሳ ሆስፒታል ውስጥ ተኝቶ ነበር:: በሆስፒታሉ ሕክምና አግኝቶ ጥቂት እንደቆየ ተጨማሪ ሕክምና እንደሚያስፈልገው ተነግሮት ከሆስፒታል እንዲወጣ ተደረገ:: ይሁንና ሆስፒታል አልጋ ይዞም ሆነ እየተመላለሰ ለመታከም የሚያስችል በቂ ገንዘብ አልነበረውም:: እናም ሰዎች ‹‹ግድ የለም ባኅላዊ ወጌሻ ጋር ሂድ! ወዲያው ትድናለህ›› አሉት:: እሱም አማራጭ እንደሌለው ተገንዝቦ ወደ ባኅላዊ ወጌሻ አመራ:: እዛ እንደደረሰ ባኅላዊ ወጌሻው ራሱን እስኪስት ድረስ አሸው:: ከዛም ሁለቱንም እግሮቹን በሸምብቆ ጥፍንግ አድርጎ አስሮ ወደ ቤት ላከው::

አያሌው ሸምበቆው በእግሩ ላይ ከታሰረበት ሰዓት ጀምሮ በሕመም እየተሰቃየ እንቅልፍ በዓይኑ ሳይዞር ከረመ:: ከቀናት በኋላ ሸምበቆው ሲፈታ ግን የአያሌው እግሮች እንኳን ሊድኑ ጭራሽ አመርቅዘውና ቆስለው ነበር:: ይባስኑም እግሮቹ ጠቁረውና ሰልስለው ብቻ አላቆሙም:: መጥፎ ጠረን ከማምጣት አልፈው ሕመሙ ከእግሩ ወደ ጀርባው ተዛምቶ ነበር:: በዚህ ቅፅበት ነበር አያሌው እንደገና ወደ ሃዋሳ ሆስፒታል ያመራው:: ነገር ግን አያሌው ዘግይቷል:: ምክንያቱም በእግሮቹ ላይ የተፈጠረው ቁስል ወደ ጋግሪን ተቀይሯል:: ሀኪሞች እግሮቹን ተመለከቱ:: አያሌው ዳግም ቆሞ በእግሮቹ እንደማይራመድባቸው ሲያውቁ አዘኑ::

አሁን የሀዋሳ ሆፒታል የአጥንትና መገጣጠሚያ ሀኪሞች የአያሌውን ሕይወት ከማትረፍ ውጪ ምንም አማራጭ አልነበራቸውም:: ሕይወቱን ለማትረፍ ደግሞ የአያሌው ሁለት እግሮች ከጉልበት በታች መቆረጥ ነበረባቸው:: ስለዚህም እግሮቹ ከጉልበቱ በታች ተቆረጡ:: በአከርካሪ አጥንቱ ላይ የተፈጠረው ችግር ግን በሕክምና ተስተካከለለት:: አያሌው አሁን ቢያንስ ሕይወቱ ተርፏል:: ነገር ግን ዳግም እንደ ሌሎቹ አቻዎቹ በእግሮቹ ዳገት አይወጣም፤ ቁልቁለት አይወርድም:: አይራመድም፤ አይሮጥም:: ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሰው በተሽከርካሪ ወንበር አማካኝነት ነው:: ለዚህ ደግሞ የግድ የባለቤቱ ድጋፍ ያስፈልገዋል:: ሥራም አቁሟል፤ የቤተሰቡ ገቢም ተቋርጧል::

አያሌው ሕክምናውን አቋርጦ ወደ ባኅላዊ ወጌሻ በመሄዱ ሕይወቱ በእንዲህ ያለ ክስተት ተደምድሟል:: ልክ እንደ አያሌው ሁሉ ተመሳሳይ እጣ ፈንታ ደርሷቸው ወደ ባኅላዊ ወጌሻ አምርተው አካላቸው የጎደለና ሕይወታቸውም ያለፈ ጥቂት የሚባሉ አይደሉም:: ይህም በልምድ እግርና እጅ የሚያሹና አጥንት የሚያስተካክሉ ሰዎች ሞያቸውን ሳይለቁ ተገቢውን ስልጠናና ትምህርት ወስደው ወደ ዘመናዊው መስመር በመግባት ተገቢውን አገልግሎት መስጠት እንደሚገባቸው ያመለክታል::

ዶክተር መንግስቱ ገብረ ዮሃንስ የአጥንትና መገጣጠሚያ ስፔሺያሊስትና የጀርባ አከርካሪ አጥንት ሰብ ስቴሺያሊቲ ሀኪም ናቸው:: አያሌውን የመሳሰሉና የባኅላዊ አጥንት ሕክምና ተከታትለው ሕክምናው ለውጥ ሳያመጣ ሲቀር ሕመሙ ሲብስባቸው ወደ ሆስፒታል የሚመጡ ታማሚዎች ቁጥር በርካታ ስለመሆኑ ይናገራሉ:: ሆኖም አብዛኛዎቹ ታማሚዎች ችግሩ ተባብሶና ወደ ሌላ የጤና ጠንቅ ከተለወጠ በኋላ ወደ ሕክምና ቦታ እንደሚመጡም ነው የሚገልጹት:: በዚህ ምክንያት የሚፈለገውን ሕክምና አገልግሎት እንደማያገኙና ከዚህ ይልቅ የአብዛኛዎቹ ታካሚዎች እጣ ፈንታ የአጥንትና መገጣጠሚያ ሕክምና ማግኘት ሳይሆን የእጅና የእግር መቆረጥ መሆኑን ይጠቁማሉ::

> **ወ**ጌሻ ማን እንደሆነ መታወቅ አለበት። ከታወቀ ደግሞ መስራት ያለባቸው ሥራዎች ተለይተው ሊታወቁ ይገባል። መስራት ያለባቸውን ነገሮች ለማወቅ ደግሞ አስፈላጊው ሁሉ ስልጠና ይሰጣል። በዚሁ መሰረት ወጌሻዎች ሥራቸውን ያከናውናሉ። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ግን በጤና ሚኒስቴርም ይሁን በክልል ጤና ቢሮ ደረጃ ወጌሻን የሚገልፅ ይህ ነው የሚባል ነገር የለም

እርሳቸው እንደሚሉት፤ በኢትዮጵያ ወጌሻዎች ወይም ባኅላዊ የአጥንትና መገጣጠሚያ ሀኪሞች ማን እንደሆኑና ራሱ ሕክምናው ምን እንደሆነ በትክክል አይታወቅም:: በስፖርቱ አካባቢም ያሉ ሰዎች ራሳቸውን ወጌሻ ብለው ነው የሚጠሩት:: በእድሜ የገፉ እናቶችና አባቶችም ያሻሉ:: ራሳቸውንም እንደ አጥንትና መገጣጠሚያ ሀኪም ይቆጥራሉ:: ለምሳሌ፡- በወላይታ ዞን ሶዶ ከተማ ማንም ሰው ከመሬት ተነስቶ ወጌሻ መሆን ይችላል:: እንደውም አንዲት የ13 ዓመት እድሜ ያላት የክለብ ታዳጊ እግር ኳስ ተጫዋች በአጋጣሚ ኳስ ስትመታ ትወድቃለች:: ጓደኞቿ እቤት ይወስዷትና አሽተው ቁርጭምጭሚቷ አካባቢ ስለነበር ጉዳቱ በምትለብሰው ሻሽ እግሯን ያስሩታል:: ይሁንና ከሶስት ቀን በኋላ እግሯ ሙሉ በሙሉ በስብሶ ወደ ሀኪም ቤት ሄዳ ለመቆረጥ በቅታለች:: ይህ ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ወጌሻ ማንና ምን እንደሆነ እንደማይታወቅ ያመላክታል::

ወጌሻ ሲባል በአብዛኛው ጭንቅላት ውስጥ የሚመጣው የሆኑ አካባቢዎች ላይ ያሉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ:: ነገር ግን እውነታው እንደዛ አይደለም:: ጥቂት የሚባሉ ወጌሻን ሥራዬ ብለው የያዙ ሊኖሩ ይችላሉ:: ነገር ግን ብዙዎቹ በተለምዶ ሥራውን የሚከውኑ ናቸው:: ለምሳሌ የተሰበረ እንስሳ እግር ያስሩና ሲድን እርሱን ወደ ሰው የማምጣት ሥራ የሚሰሩ አሉ:: አንድ ሰው ሲታሽ ከተመለከቱ ‹‹አይ እንደሱ አይደለም እንደዚህ ነው የሚታሸው›› ብለው የሚያሹም አሉ:: ስለዚህ በዋናነት የሚፈለገው ጉዳይ ወጌሻ እከሌ ነው ተብሎና ራሱ ሚና ኖሮት የሚሰራው ሥራ ታውቆ ለሚሰራው ሥራ ደግሞ ተጠያቂነት እንዲኖረው ማድረግ ነው::

ለምሳሌ የአጥንትና መገጣጠሚያ ሀኪሞች የፅንስና ማሕፀን ሥራ አይሰሩም:: ይህን ሲሰሩ ቢገኙና ችግር ቢፈጥሩ በሕግ ተጠያቂ ይሆናሉ:: ኃላፊነት አለባቸው:: ስለዚህ የባህል አጥንትና መገጣጠሚያ ሀኪሞች/ወጌሻዎች/ ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል:: ሥራው ይሰራ ነገር ግን የሚጎዱ ነገሮች መኖር የለባቸውም:: ምክንያቱም በወጌሻዎች ምክንያት አካላቸውን የሚያጡ ብሎም ለሞትም ጭምር የሚዳረጉ በርካታ ሰዎች በመኖራቸው ነው::

የሚሰራው ሥራ በሚመለከተው አካል ታውቆ፣ የሚሰሩት ሰዎችና ሥራቸውም ተለይቶ በሚሰሩት ልክ ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ከማድረግ አንፃር እንጂ ሌላ ነገር የለውም:: ስለዚህ ወጌሻ ምን እንደሆነና ሥራውን ማን እንደሚከውን አይታወቅም፤ ነገር ግን ብዙ ሰው ወደ ዘመናዊ ሕክምና ቦታዎች ከመምጣቱ በፊት በራሱ፣ በቤተሰቡ ወይም በጎረቤቱ ግፊት ወደ ባኅላዊ አጥንት ሃከሚሞች/ወጌሻዎች/ይሄዳል:: እነዚህ ወጌሻዎች መጠነኛ እርዳታ ካደረጉ በኋላ የጎንዮሽ ጉዳት ሲከተል በርከት ያሉ ሰዎች ወደ ሕክምና ተቋም ይመጣሉ::

ዶክተር መንግስቱ እንደሚያብራሩት፤ ወጌሻዎች የማኅበረሰቡ አንዱ ክፍል ናቸው:: በሌላ ልጅ ላይ የተከሰተው የአካል ጉዳት በእነርሱ ልጆች ላይም ሊከሰት ይችላል:: ስለዚህ እንደማኅበረሰብ እነርሱን የማንቃት ሥራ መስራት ያስፈልጋል:: ከእነርሱ ጋር በቅርበት መነጋገርም ይገባል:: ለምሳሌ በቅርቡ ከወጌሻዎች ጋር የአጥንትና መገጣጠሚያ ሕክምና ያለበትን ደረጃ ለማስገንዘብ እነርሱን ያሳተፈ ወርክ ሾፕ ተዘጋጅቷል:: ከባኅላዊ የአጥንት ሕክምና ጋር ተያይዞ የሚመጡ ችግሮችን በሚመለከት፣ ምን መደረግ እንዳለበትና ምን ቢደረግ ችግሮቹ ሊፈቱ እንደሚችሉም ንግግርና ውይይት ተደርጓል::

ሀኪምም፤ ወጌሻም ይሰራው ሰው ጋንግሪን በእጁ አልያም በእግሩ ላይ የሚከሰተው ጠብቆ ሲታሰር ነው:: ስለዚህ ከወጌሻዎች ጋር አጥብቆ ማሰርና ማሸት መፍትሄ እንዳልሆነ ውይይት ተደርጓል:: አጥንት ከተሰበረ ልክ በቢላ እንደተቆረጠ ቆዳ ነው፤ መታሸት አይፈልግም:: ምክንያቱም አጥንት ስብራት ሲያጋጥመው መጀመሪያ ደም ነው የሚረጋው:: የረጋው ደም ደግሞ በሂደት ወደ አጥንት ይቀየርና አጥንት ወደነበረበት እንዲመለስ ያደርጋል::

ወጌሻ ማን እንደሆነ መታወቅ አለበት:: ከታወቀ ደግሞ መስራት ያለባቸው ሥራዎች ሊታወቁ ይገባል:: መስራት ያለባቸውን ነገሮች ለማወቅ አስፈላጊ ሁሉ ስልጠና ይሰጣል:: ከዛ በዚህ መሰረት ሥራቸውን ያከናውናሉ ማለት ነው:: አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ግን በጤና ሚኒስቴርም ይሁን በክልል ጤና ቢሮ ደረጃ ወጌሻ ይህ ነው የሚል በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም:: ለዚህም ነው የኢትዮጵያ አጥንትና መገጣጠሚያ ሀኪሞች ማኅበር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማለትም ከባለሞያዎችና ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመሆን ሰነድ እያዘጋጀ የሚገኘው::

ይህ ሰነድ ከተዘጋጀ በኋላ በቀጣይ ለወጌሻዎች ስልጠና መሰጠት ስላለበትና ከዛም በቀጣይ እንዴት መስራት አለባቸው የሚለው መታወቅ ስላለበት እነርሱ የሚችሉትን ሰርተው የማይችሉትን ወደ ጤና ተቋማት እንዲልኩ የማድረግ ሥራ ለመስራት እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ይገኛሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ በጤና ተቋም በኩልም ችግሮች ስላሉ ችግሩን ከመቅረፍ አንፃር መደረግ ባለባቸው ጉዳዮች ላይ ሥራዎች እየተከናወኑ ናቸው::

ዶክተር መንግስቱ እንደሚሉት፤ ከባኅላዊ የአጥንት ሕክምና/ወጌሻ/ ጋር በተያያዘ ያለውን የሕብረተሰብ ትክክለኛ ግንዛቤ ለማጎልበት ካስፈለገ ቀድሞ የሚነሳው ሚዲያው ነው:: ምክንያቱም ሚዲያ በሕዝቡ ዘንድ ታማኝና ወደ ማሕበረሰቡ በቀላሉ ተደራሽ በመሆኑ ትክክለኛውን ግንዛቤ በቀላሉ ማስረፅ ይቻላል:: ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ የኢትዮጵያ አጥንትና መገጣጠሚያ ሀኪሞች ማሕበር ከሚዲያዎች ጋር እየሰራ ይገኛል:: ከዚህ ቀደምም በዚሁ ጉዳይ ላይ ማሕበሩ ወርክሾፕና ጋዜጣዊ መግለጫ አካሂዷል:: አሁንም የሚቀጥል ይሆናል::

ከዚህ ውጪ በየሳምንቱ ማሕበራዊ ሚዲያ ላይ አስተማሪ የሆኑ አጫጭር ፅሁፎች በሳምንት ሁለት ግዜ ላለፉት አራት ወራት እንዲለቀቁ ተደርጓል:: አሁንም ሥራው ቀጥሏል:: የአጥንትና መገጣጠሚያ ሀኪሞች በሬዲዮ ቀርበ አስተማሪና ሌሎች መረጃዎችን እንዲያቀርቡ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ:: በቀጣይ ግን የአጥንትና መገጣጠሚያ ሕክምናን በሚመለከት ከተመረጡ ሚዲያዎች ጋር ሰፋፊ ፕሮግራሞች የሚቀርቡበት ሁኔታ ይፈጠራል::

ማሕበረሰቡን የማንቃት ሥራ በሰፊው ተጠናክሮ ይቀጥላል:: በተለያዩ ክልሎች በመሄድ በተለያዩ ቋንቋዎች ሚዲያዎችን በመጠቀም ማሕበረሰብን የማንቃትና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራው ይሰራል:: ይህም ሥራ የሚከናወነው ሁሉንም የሚዲያ አማራጮች በመጠቀም ይሆናል:: ከዚህ ውጪ የጤና ባለሞያዎች ማለትም ነርሶች፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ ማሕበረሰብ ውስጥ ያለው ሰዎችን በማሰልጠን የወጌሻ ሕክምና አገልግሎትን ሰዎች ሳይጎዱ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራዎች በትኩረት ይሰራሉ:: ባሕላዊ የአጥንት ሀኪሞች/ ወጌሻዎች/ ትክክለኛውን ሕክምና አገልግሎት እንዲሰጡ በማሕበሩ በኩል ቪዲዮዎችና ቡክሌቶች እንዲዘጋጁ ተደርገዋል:: ወደፊት ደግሞ ማጣቀሻ የሚሆን መፅሃፍ በማዘጋጀት በሁሉም የጤና ተቋማት ውስጥ ያሉ የዘርፉ ሕክምና ባለሞያዎች እንዲጠቀሙበት ይሆናል::

ከዚህ ውጪ መረጃዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ከማድረግ አንፃር መተግበሪያ በልፅጎ ሰዎች በስልካቸው የሚጠቅማቸው መረጃ እንዲኖራቸው ለማድረግ እየተሞከረ ነው:: እነዚህን አስፍቶ የመስራት ሁኔታዎች ይቀጥላሉ:: በጤና ሚኒስቴር ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር መሬት ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በማሳወቅ ደረጃ በደረጃ ማሕበረሰቡ ጋር ለመድረስ ሙከራም ይደረጋል::

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# የሙስና ወንጀል ምንነትና ልዩ ባህሪያት

በሀገራችን በፍትህ ሥርዓት ከሚታወቀው የሕግ አይነት አንዱ የወንጀል ሕግ ነዉ፡፡ የተለየዩ ድርጊቶችን በሕግ ወንጀል በማድረግ ልዩ ልዩ የወንጀል ሕጎች ያሉ ሲሆን ለምሳሌ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ፤ የፀረ ሽብር ሕግ፤ የሕገ ወጥ ሰዎች ዝውውር ሕግ፤ የሙስና ወንጀሎች ሕግ እና ሌሎች ሕጎች ይገኛሉ፡፡ የዚህ ጽሁፍ ዓላማ አጠቃላይ ወንጀል ምንነትና የሙስና ልዩ ባህሪን የሚመለከት ነው፡፡ ስለሆነም ወንጀል ማለት ምን ማለት ነዉ? የሙስና ወንጀል ትርጉሙ ምንድን ነው? የሙስና ወንጀል ከሌላው ወንጀል አንጻር ልዩ ባህሪያት ምን እንደሆነ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

**ሀ/ የወንጀል ትርጉም**

አንድ ድርጊት ወንጀል ነው ለማለት በወንጀል ሕጉ በተጠቀሰው መሰረት ሶስት ፍሬ ነገሮች መሟላት አለበት፡፡ አንደኛው ፍሬ ነገር (element) በሕግ የተከለከለ ድርጊት መሆን አለበት፡፡ ድርጊቱ በሕግ እንዲያደርግ ወይም እንዳያደርግ የሚገልጽና ይህንን ግዴታ የተላለፈ ሰው ላይ ቅጣት የሚጥል መሆን አለበት፡፡

በ1996 ዓ.ም የወጣ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ስለ ሕጋዊነት መርህ ሲገልጽ የወንጀል ሕግ ስለ ልዩ ልዩ ወንጀሎችና በወንጀል አድራጊዎች ላይ ስለሚፈፀሙት ቅጣቶችና ጥንቃቄ እርምጃዎች በዝርዝር እንደሚደነግግ ይገልጻል፡፡

ፍርድ ቤቱ ሕገወጥነቱ በሕግ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት እንደ ወንጀል ሊቆጥረው እና ቅጣት ሊወስንበት አይችልም፡፡ ፍርድ ቤቱ በሕግ ከተደነገጉት በቀር ሌሎች ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሊወስን አይችልም በማለት ያስቀምጣል፡፡ ስለሆነም አንድ ሰው የፈጸመው ድርጊት በሕግ የተከለከለ ካልሆነና የተከለከለ ሆኖም ቅጣትን የማይወስን ከሆነ የወንጀል ድርጊት አይሆንም፡፡ ሁለተኛው ፍሬ ነገር በሕግ የተከለከለ ድርጊትን መፈጸምን የሚመለከት ነው፡፡

በተመሳሳይ ሕግ አንቀጽ 23 ሕገወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገውን ድርጊት መፈጸም ወንጀል ነው ይላል፡፡ በሕጉ መሰረት ድርጊት ማለት በሕግ የተከለከለውን ማድረግ ወይም በሕግ የታዘዘውን አለማድረግ ነው፡፡ ሶስተኛ ፍሬ ነገር የሀሳብ ክፍል ወይም ሞራላዊ ፍሬ ነገር የሚመለከት ነው፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23(2) ላይ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡ ሞራላዊ ፍሬ ነገር ሲባል የወንጀል ድርጊት የተባለውን ድርጊት አድራጊው ሆን ብለው አስበው ወይም በቸልተኝነት ስለመፈጸሙ የሚመለከት ሲሆን ይህም የሚረጋገጠው ከተፈጸመው ግዙፋዊ ድርጊት አፈጻጸምን በማመዛዘን ነው፡፡

በመሆኑም ወንጀል ድርጊት የሚባለው ድርጊትን የሚከለክል ሕግ፣ በሕግ የተከለከለ ድርጊት መፈጸምንና በሕጉ በተጠቀሰው የሀሳብ ክፍል አይነት አስበው ወይም በቸልተኝነት የተፈጸመ ሲሆን ነው፡፡

**ለ/ የሙስና ወንጀል**

የሙስና ወንጀል ትርጉም በሙስና ወንጀሎች ሕግ ላይ በግልጽ ትርጉም አልተሠጠም፡፡ ማንኛውም የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው በ2007 ዓ.ም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 2 ስር የተመለከተውን የሙስና ባህርይ የሚያሟላ ወንጀል በፈጸመ ጊዜ ለወንጀሉ የተደነገጉ የቅጣት ድንጋጌዎች ይፈጽሙብታል ይላል፡፡

ማንኛውም የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በተሰጠው ኃላፊነት ወይም ተግባር ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት የተሰጠውን ስልጣን ወይም የሕዝብ አደራ ያላአግባብ የተገለገለ እንደሆነ፤

ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ ለመንግስት ወይም ለሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለመስጠት ቃል የገባ፤ ያቀረበ፤ የሰጠ ወይም ለማቅረብ የተስማማ እንደሆነ፤ ወይም በአግባቡ ለተፈጸመ ወይም በአግባቡ ለወደፊት ለሚፈጸም የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግሰት ልማት ድርጅት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሥራ የማይገባ ጥቅም ለማንኛውም ሰው የሰጠ ወይም ከማንኛውም የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ፈጻሚነት ተጠያቂ ይሆናል በማለት ይገልጻል፤ (በአዋጁ አንቀጽ 4(2))፡፡

ሙስና ወንጀልን በተመለከተ በቀጥታ ትርጉም የሚያስቀምጥ ሳይሆን ምን አይነት ድርጊት ሲፈጸም በሙስና ወንጀል ሊያስቀጣ እንደሚችል የሚገልጹ ናቸዉ፡፡ ሆኖም ሙስና ከሌሎች ወንጀሎች የራሱ የሆነ ልዩ ባህርይ ያለዉ በመሆኑ በአዋጅ የተለያየ ድርጊቶችን የሙስና ወንጀል በማድረግ በሕጉ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የተሻሻለው የፀረሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 2(1)(1) የሙስና ወንጀል ማለት የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 የተሰጠው ትርጓሜ እንደሚኖር ይገልጻል፣ የመስና ወንጀሎች ማለት የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 የተጠቀሱት የሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈጸም ወንጀል ነው፡

**ሐ/ የሙስና ወንጀሎች ልዩ ባህሪያት**

1. ተጠያቂ የሚሆኑ አካላት በተመለከተ በሙስና ወንጀል ፈጻሚነት የሚጠየቁት የመንግስት መስሪያ ቤት፤ የመንግስት ልማት ድርጅት እና የሕዝባዊ ድርጅት ሥራ ጋር በተያያዘ በሕጉ የተጠቀሱ ድርጊቶችን በመተላለፍ የሚፈጽም የመንግሰት ሰራተኛ ወይም ኃላፊ ወይም ከእነዚህ ተቋማት ጋር በተያያዘ የሕጉ ድንጋጌ የተላለፈ ማንኛውም ግለሰብ የሚመለከት ነው፡፡

ሕዝባዊ ድርጅት ሲባል በማንኛውም አግባብ ከአባላት ወይም ከሕዝብ የተሰበሰበ ወይም ለሕዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ ንብረት ወይም ሌላ ሀብትን የሚያስተዳድር አካልንና አግባብነት ያለውን ኩባንያ የግል ዘርፍ የሚያካትት ሲሆን፤ የሃይማኖት ድርጅትን የፖለቲካ ፓርቲን የዓለም አቀፍ ድርጅትን እና እድርንና ተመሳሳይ ባሕላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ማኅበርን አያካትትም፡፡

2. ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ጉዳት ለማድረስ በማሰብ የሚፈጸም መሆኑ፤ የሙስና ወንጀሎች ሕግን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በአብዛኛው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ የማይገባ ጥቅም ማለት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም አግባብ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ጥቅም ማለት ነው (በአዋጁ አንቀጽ 2(14))፡፡

2.1 ጥቅም በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 2(13) ጥቅም ማለት የሚከተሉትን ይጨምራል፤

1ኛ. በገንዘብ ወይም በማናቸውም ዋጋ ባለው መያዣ ወይም በሌላ ንብረት ወይም በንብረት ላይ ያለን ጥቅም (መብት)፤ 2ኛ. ማንኛውንም ሹመት፣ ቅጥር፣ ወይም ውል 3ኛ. ብድርን ግዴታን ወይም ማናቸውንም ዕዳ በሙሉም ሆነ በከፊል መክፈልን ማስቀረትን ማወራረድን ወይም ከእነዚህ ነገሮች ነጻ ማድረግን፤ 4ኛ. ከተመሰረተ ወይም ካልተመሰረተ የአስተዳደር፣ የፍትሐብሔር ወይም የወንጀል ክስ ወይም ካስከተለዉ ወይም ከሚያስከትለው ማናቸውም ቅጣት ወይም የችሎታ ማጣት በማዳን ወይም ይህን በመሰለ ዘዴ የሚደረግን አገልግሎት ወይም ውለታ

5ኛ. ማናቸውንም መብት ወይም ግዴታ መፈጸምን ወይም ከመፈጸም መታቀብን፤ 6ኛ. ከተጠቀሱት ውጭ በገንዘብ የማይተመን ማናቸውንም ሌላ ጥቅም ወይም አገልግሎት፣ እና ከተጠቀሱት ውጭ በገንዘብ የማይተመን ማናቸው ሌላ ጥቅም ወይም አገልግሎት፤ እና ከተጠቀሱት ጥቅሞች አንዱን ማቅረብን፤ ጥቅሙ የሚገኝበትን መንገድ ማመቻቸትን ወይም ይሄንኑ በሚመለከት የተስፋ ቃል መግባትን ወይም መቀበልን ያካትታል፡፡

2.2 የሶስተኛ ወገን ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ መሆኑ፤

የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ብቻ ሳይሆን በሚሰራበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ሕዝባዊ ድርጅትን ጥቅም ወይም መብት ወይም የሌላ ግለሰብ ጥቅም ወይም መብት ላይ ሕጉን በመተላለፍ ጉዳት ከደረሰ ጥቅም ባያገኝም በሙስና ወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

3. ጥቅም የማግኘት ወይም ጉዳት የማድረስ ሀሳብ በሕግ ግምት የሚወሰድ ስለመሆኑ፤

ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር የሙስና ወንጀሉ የተፈጸሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት መሆኑ በተደነገገ ጊዜ በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬ ነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ድርጊቱ የተፈጸመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም ሶስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ይገመታል፡፡ በሕጉ መሰረት ክስ የቀረበበት ሰው የሙስና ወንጀል በመተላለፍ የፈጸመው ግዙፋዊ ነገር ወይም ድርጊቱ ከተረጋገጠ፤ ያደረሰው ጉዳት ወይም ያገኘው ጥቅም አስበው እንደሆነ ሕጉ ግምት ይወስዳል፡፡ ሆኖም በሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በሌላ ማስረጃ የቀረበበት ክስ ማስተባበል ይችላል፡፡

4. በሕግ አግባብ ለተሰራው ሥራ ጥቅም መቀበል ወይም መስጠት በሙስና ወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑ ሌላ ልዩ ባህሪይ ነው፡፡ ማንኛውም የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በሕግ የተጣለበት ግዴታ ከመፈጸሙ በፊት ይሁን ከፈጸመ በኋላ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ በሕጉ የማይገባ ጥቅም በመቀበል የሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ግዴታውን ለተወጣው ሰራተኛ ጥቅም የሰጠ ማንኛውም ግለሰብ በሙስና ወንጀል ያስቀጣል፡፡

5. በሙስና ወንጀል ልዩ በሚያደርገው ተጎጂ መንግስት ወይም ሕብረተሰቡ መሆኑ ወይም የአክሲዮን ባለቤቶች መሆናቸው ነው፡፡ ምንም እንኳን ጉቦ መስጠት አይነት ጉዳይ የግለሰብ ተጎጂ ሊኖር የሚችል ቢሆንም በሙስና ወንጀል ቀጥታ ተጎጂ የሚሆነው አብዛኛው ማኅበረሰቡ ነው፡፡

ሙስና ውስብስብ ከሚያደርጉት አንዱ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ ባለመኖሩ ምርመራ፤ ክስ እና የፍርድ ሂደት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ሌላው ጥቅም ሰጪ ይሁን ጥቅም ተቀባይ በስምምነት የሚፈጸሙ በመሆኑ የምርመራም ሆነ የክስ ሂደት አስቸጋሪ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ሕብረተሰቡ የሙስና ድርጊት ሁሉንም ሕብረተሰብ የሚጎዳ ተግባር በመሆኑ መስናን በመዋጋት ሁሉም የድርሻውን መወጣት አለበት፡፡

በአጠቃላይ ወንጀል ለማለት ድርጊትን የሚከለክል ሕግ፤ የተከለከለ ድርጊት፤ መጾምንና በሕግ የተከለከለ ድርጊት የፈጸመበት የሀሳብ ክፍልን በአንድነት ተሟልቶ ሲገኝ ስለመሆኑ ተገልጧል፡፡

የሙስና ወንጀል በሙስና ወንጀል ሕጉ የሚከለከሉ ተግባራት የገለጸ ሲሆን የሀሳብ ክፍል በተመከለተ በሕግ ግምት የሚወሰድ ነው፡፡ የተከለከለ ተግባራት በሕጉ ከተደነገጉት መካከል ስልጣን አለአግባብ መገልገል፤ የመንግስት ሥራ በማይመች አኳኋን መምራት፤ ጉቦ መስጠት ወይም መቀበል እና ሌሎች ይገኛሉ፡፡

**ማንኛውም የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በሕግ የተጣለበት ግዴታ ከመፈጸሙ በፊት ይሁን ከፈጸመ በኋላ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ በሕጉ የማይገባ ጥቅም በመቀበል የሙስና ወንጀል ያስጠይቃል**

# መሠረተ ልማት

## በፕላን የሚመሩና የማይፈርሱ ከተሞችን ለመገንባት

ኃይሉ ሣሕለድንግል

ከተሜነትና ከተማ በዓለም አቀፍ ደረጃም እየሰፋ ይገኛል:: በከተሞች ያሉ መሠረተ ልማቶችንና አገልግሎቶችን ፍሊጋ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትም እየተበራከተ ነው:: ከተሜነት የማይቀር ክስተት ስለመሆኑና ይህን ፍልሰት ለማስተናገድ ከወዲሁ ዝግጁ ሆኖ መገኘት እንደሚገባ የዘርፉ ባለሙያዎች ያስገነዝባሉ::

በሀገሪቱ የከተሞች ብዛትም፤ ስፋትም በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ስለመሆኑ መንግሥትና የዘርፉ ባለሙያዎችም አስረግጠው ይገልጻሉ:: ለማይቀረው ከተሜነትና ከተማ በከተማ ልማት ሥራ በትኩረት መንቀሳቀስ በእጅጉ አስፈላጊ ስለመሆኑም ያሳስባሉ::

በሀገሪቱ እስከ አሁን የታየው ግን የተገላቢጦሽ ስለመሆኑ ባለሙያዎች ይጠቀሳል:: ከተሞች እየቀደሙ እኛ እየተከተለን ነው ያለነው ሲሉ አንድ የዘርፉ ባለሙያ የተናገሩትም ይህንን ያመለክታል:: በትላልቅ ከተሞች አቅራቢያዎች የሚታየው ፕላን ላይ ያልተመሠረተ የከተማ መስፋፋት ይህንኑ ያስገነዝባል::

በከተሞች የሚታየው ሕገወጥ ግንባታ፣ ከፍተኛ የፕላን ጥሰት መስተዋሉ ከተማን ለመምራትም ሆነ ከተሜነትን ለማስተናገድ በአጠቃላይ ከተሞች ስር የሰደደ ችግር ውስጥ እንዲገቡ እያደረጉ ናቸው:: አዲስ አበባን ጨምሮ በርካታ የሀገሪቱ ከተሞች አሁን ለገቡበት የኮሪደር ልማት አንዱ ምክንያት ፕላን መሠረት ተደርጎ አለመገንባታቸው ወይም የፕላን ጥሰት መሆኑ ይገለጻል::

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ባለፈው ሳምንት መጨረሻ በከተማ አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ ላይ ለሚሠሩ አመራሮች በመሬትና ካዳስተር፣ በከተሞች ፕላን፣ በአገልግሎት ማዘመን፣ በከተሞች ገቢና በምግብ ዋስትና ሥራዎች ላይ ባዘጋጀው ችግር ፈቺ ሥልጠና ላይም እነዚህ ችግሮችና ችግሮቹን ለመፍታት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ተጠቁመዋል::

በአዳማ ከተማ በተካሄደውና የሚኒስቴሩ፣ የክልል የከተማና መሠረተ ልማት እና ኮንስትራክሽን ዘርፍ አመራሮች በተገኙበት በዚህ መድረክ ላይ ጽሑፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል:: በዛሬው የመሠረተ ልማት ዓምዳችን በመድረኩ ከተነሱት መካከል በተለይ በከተማ ፕላንና መሬት ላይ የተነሱትን ሀሳቦች ይዘናል::

መድረኩን በንግግር የከፈቱት በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የከተማ አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ፋንታ ደጀን በሀገሪቱ ሰፊ የከትመት ምጣኔ እንደሚታይ ጠቅሰው፤ ‹‹ይህን የሚመጥን ሥራ መሥራት ከእኛ ይጠበቃል›› ሲሉ ያመለክታሉ:: የሀገሪቱ ሕዝብ ብዛት እየጨመረ እንዲሁም ሕዝቡ ወደ ከተሞች እየተሰበሰበ ነው፤ የከተሞቹ ብዛትም ከ2 ሺ 500 በላይ መድረሱንም ይጠቁማሉ::

ከተሞቹ በርካታ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎችና ጥቂት ባለሀብቶች የሚኖሩባቸው መሆናቸውንም አመልክተው፣ ‹‹እነዚህን ከተሞች በተቻለ መጠን ለሰው ልጅ ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግና ለዚህም ከእኛ ብዙ ይጠበቃል›› ይላሉ:: በበጀት ዓመቱ በሚኒስቴሩ ትኩረት ተሰጥቶ ከሚሠራባቸው መካከል ፕላን አንዱ መሆኑን ሚኒስትሩ ጠቅሰው፣ ከተሞች በፕላን መመራት እንዳለባቸው ይናገራሉ:: በሀገሪቱ አሁንም ፕላን የሌላቸው ከተሞች ስለመኖራቸውም ጠቁመው፣ የገጠር የቀበሌ ማዕከላት ጭምር ስኬች ፕላን ሊኖራቸው እንደሚገባ ያስገነዝባሉ::

በ2017 በጀት ዓመት ሌላው በትኩረት መሠራት ያለበት መሬት ነው:: መሬት በሚፈለገው ልክ እየተመዘገበ አለመሆኑ በመድረኩ የተነሳ ሲሆን፣ የመሬት መመዝገብ ከተሞችን ከተለያዩ ያልተገቡ ፍላጎቶች እንደሚያወጡ ተመላክቷል:: በመድረኩ በሀገሪቱ ከተሞች እየተካሄደ ያለውን የኮሪደር ልማት እንደ መልካም አጋጣሚ መጠቀም እንደሚገባም ተጠቁሟል::

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳስታወቁት፤ ከአዲስ አበባ ከተማ ኮሪደር ልማት በከተሞች ላይ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል መገንዘብ ይቻላል:: በኮሪደር ልማቱ ለመጪው ትውልድ ትልቅ ሥራ እየተሠራ ይገኛል:: በከተሞች የሚታየውን ስር የሰደደ ችግር ለመፍታት አንድ ቦታ ላይ ዋጋ መክፈል የግድ ይሆናል፤ አሁን ያለው ትውልድ በከተማ መልሶ ልማቱ ዋጋ እየከፈለ ነው:: ለትውልድ ዕዳ እያወረሱ መሄድ አይገባም፤ የሀገሪቱ ከተሞች ከተማ መምሰል አለባቸው:: አዲስ አበባ በፕላኗ መሠረት ለምታ ቢሆን ኖሮ አሁን የሚታየው ችግር ባልታየ ነበር::

አገልግሎት አሰጣጥን ማዘመን ሌላው ከተሞች በትኩረት ሊሠሩበት የሚገባ ጉዳይ ነው:: በዚህ ዘመን ሰው ቤቱ ሆኖ ጉዳዩን መፈጸም መቻል እንዳለበት



በክልሎች ለሚካሄዱ የኮሪደር ልማት ሥራዎች አዲስ አበባ ተሞክሮ መቀመሪያ ሆናለች

ሚኒስትር ዴኤታው አስገንዝበው፣ በእዚህ ልኩ ካልተሠራ በአገልግሎት አሰጣጥ በኩል እርካታ ማምጣት እንደማይቻል ያመለክታሉ::

ስምንት ከተሞች አገልግሎት ማዘመን መጀመራቸውን ጠቅሰው፣ ሌሎች ይህንኑ መንገድ እየተከተሉ መሆናቸውን ይጠቁማሉ:: አገልግሎት ማዘመን ሰው የተማረረበትን የሥነ ምግባር ችግር ለመፍታት አንድ መሣሪያ በመሆኑ ዲጂታላይዜሽን ላይ በስፋት መሠራት እንዳለበት ነው ያስገነዘቡት::

‹‹ችግር ፈቺ ሥልጠና በመሬትና ካዳስተር እንዲሁም በከተሞች ፕላን ሥራዎች›› በሚል ርዕስ ጽሑፍ ያቀረቡት በሚኒስቴሩ የከተማ ፕላንና አከታተም መሪ ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ገነት ገብረእግዚአብሔር በበኩላቸው፤ የሀገሪቱ ከተሞች የከትመት ምጣኔ 5 ነጥብ 4 በመቶ እየጨመረ መሆኑን ይጠቅሳሉ:: ይህም ፈጣን የሚባል ምጣኔ መሆኑን አመልክተው፤ ይህን እድገት የሚመጥን ሥራ መሠራት እንዳለበትም ያስገነዝባሉ::

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ በአከታተም ሥርዓት ላይ በትኩረት መሥራት ይገባል:: የከተሞች እድገት ተመጣጣኝ አይደለም፤ አዲስ አበባ በሀገሪቱ ሁለተኛ ከተማ ተብለው ከሚታወቁት በአስር እጥፍ ትበልጣለች:: የሀገሪቱ ከተሞች የአከታተም ሥርዓት ሲታይም ልዩነቱ በጣም ሰፊ ነው፤ የአከታተም ሥርዓቱ የገጠር ትናንሽ ከተሞችን ለማፍራትም ትኩረት ሊሰጥ ይገባል:: የገጠር ቀበሌ ማዕከላት ላይ እየተሠራ ያለውም ለዚህ ነው:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ ብዙ ከተሞችን መፍጠር ይቻላል:: የእስከ አሁኑ አካሄድ የተወሰኑ ከተሞች ላይ ያተኮረ ነው:: ይሄ ደግሞ ሃገሪቱ ከምትከተለው ሥርዓት ጋርም አይጣጣምም፤ በመሆኑም በአግባቡ ተደራሽ ማድረግ ላይ መሥራት ያስፈልጋል::

‹‹ይህም በመሠረታዊነት ወደ ከተማ ፕላን ይወስደናል›› ያሉት ወይዘሮ ገነት፣ ከተሞች ወደ ጎን መስፋት እንደሌለባቸው ለእዚህም ያደጉ ከተሞችን ተሞክሮ መመልከት እንደሚገባ ያስገነዝባሉ:: ሕንጻ መሥራት ብቻውን ከተማን ከተማ አያደርገውም፤ ከከተማው መሬት 40 በመቶ ለሕንጻ፣ 30 በመቶው ለአረንጓዴ ስፍራና 30 በመቶው ለመሠረተ ልማት መዋል አለበት ሲሉም ይናገራሉ::

የከተሞች በፕላን አለመሠራት ሀገሪቱን ዋጋ እያስከፈለ ስለመሆኑ እሳቸውም ያመለክታሉ:: ‹‹ፕላኖች መሬት ላይ ወርደው ተሠርቶባቸው ቢሆን አሁን የምናየውን ፈተና ባላየን ነበር›› ይላሉ:: ሚኒስቴሩ ብሔራዊ ፕላን አለው፤ ለዘጠኝ ክልሎች ሠርቶ ሰጥቷል፤ ሦስት ክልሎች ይቀሩታል፤ ለየክልሉ ከተሞች የተሠሩ ፕላኖች መኖራቸውን ይጠቅሳሉ:: ለየክልሎቹ የተዘጋጁ ፕላኖች በተቀናጀ አግባብ መሬት ላይ ከወረዱ የምንፈልጋቸውን ከተሞች እውን ማድረግ እንችላለን ሲሉም ነው የተናገሩት::

ሥራ አስፈጻሚዋ እንዳሉት፤ በሀገሪቱ ከሁለት ሺ 500 በላይ ከተሞች አሉ:: ከእነዚህ ውስጥ 90 በመቶው በፕላን የሚመሩ ሲሆኑ፣ የተቀሩት በፕላን መመራት ላይ ችግር ይታይባቸዋል:: ፕላናቸውም ያልተከለሰ ከተሞችም ይገኛሉ:: ከተሞች ባደጉ ቁጥር በፕላን ካልተመሩ ለማስተዳደርም ያስቸግራሉ፤ ከተሞችን በፕላን ላይ ተመሥርቶ ካልሠራን አሁን የሚገነባው ከተሞች ራሳቸው ነገ የሚፈርሱ ሊሆኑ ይችላሉ:: የገጠር ቀበሌዎችንና ማዕከላትንም በፕላን መምራት ያስፈልጋል:: ፕላናቸው ሲሠራ ነገ ከተማ እንደሚሆኑ ታሳቢ ተደርጎ መሆን ይኖርበታል:: ከተሞች የችግር ምንጭ እንዳይሆኑ፣ አሁን በከተሞች የሚታዩ ችግሮች እንዳይደገሙ ለማድረግ በፕላን ላይ ተመሥርተው እንዲለሙ ማድረግ ይጠበቃል::

በከተሞች ከፕላንና ከመሳሰሉት ጋር ተያይዞ የሚታየውን ችግር ለመፍታት በአዲስ አበባ ተጀምሮ ወደ ክልል የተስፋፋውን የኮሪደር ልማት እንደ መልካም አጋጣሚ መጠቀም እንደሚገባም ሥራ አስፈጻሚዋ ያመለክታሉ:: በአዲስ አበባ እየተካሄደ ያለውን የኮሪደር ልማት ተከትሎ በመላ ሀገሪቱ 30 ከተሞችም እንዲስፋፋ መደረጉ በመድረኩ ይጠቁማሉ:: እነዚህ ከተሞች ወደ ኮሪደር ልማቱ ገብተው እንዲሠሩ ድጋፍ እየተደረገላቸው ነው:: ከተሞቹ እያከናወኑ ያሉትን ሥራ በተመለከተ ሪፖርት በማድረግ ላይ ግን ክፍተት ይስተዋላል፤ 14 ከተሞች ብቻ ናቸው ሪፖርት እያደረጉ ያሉት ይላሉ::

የኮሪደር ልማቱ እየተካሄደባቸው ከሚገኙ ከተሞች መካከል ሀዋሳ፣ ዲላ፣ ይርጋለም፣ ሆሳዕና፣ ዲላ፣ ሻሸመኔ፣ ሮቤ፣ ሸገር ሲቲ ከተሞች፣ ባሕር ዳር፣ ደሴ፣ ጎንደር፣ ደብረ ማርቆስ፣ ደብረብርሃን፣ ድሬዳዋ በኛ ይታወቃሉ ሲሉ ወይዘሮ ገነት ይጠቅሳሉ:: በዚህ ሥራ ፕላን፣ ከተማ መሠረተ ልማት፣ የመሠረተ ልማት ቅንጅት ይከናወናሉ፤ እነዚህ በጋራ መመራት ይኖርባቸዋል ሲሉ ጠቅሰው ልማቱ በአንድ ሚኒስትር ዴዔታ እንዲመራ መደረጉንም ይናገራሉ::

የኮሪደር ልማት መንገድ የማስፋት ሥራ ብቻ አይደለም:: ከመንገድ ጋር ብቻ አያይዞ ማየት የሚለው መታረም ይኖርበታል:: መንገድ ከማስፋት በላይ ነው ሲሉ አስገንዝበዋል:: ይህ ልማት በፕላን መመራት እንዳለበት ገልጸው፣ አንዳንድ ከተሞች ወደ ልማቱ ለመግባት እየፈሩ ናቸው፤ ሥራው በምዕራፍ በምዕራፍ ሊካሄድ የሚችል ነው ሲሉም ያስገነዝባሉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ ከፍተኛ በጀት የመደቡበት ሁኔታ እንደሚታይም ያስረዳሉ::

የኮሪደር ልማቱን አስመልክቶ ያነጋገርናቸው የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴዔታ አቶ ፋንታ ደጀን የኮሪደር ልማት ከተሞች ፕላናቸውን ጠብቀው ለነዋሪዎች ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚሠራ መሆኑን ይገልፃሉ:: የትራፊክ ፍሰታቸው የተሻለ ኢንዲሆን፣ መንገዶቻቸው ውበታቸውን የጠበቁና የተስተካከሉ እንዲሆኑ በተለይ ለተተኪው ትውልድ ጥሩ ከተማ ማስተላለፍን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሰፋ ተደርገው የሚሠሩ መሆናቸውን ያመለክታሉ::

እርሳቸው እንዳሉት፤ በአዲስ አበባ የተጀመረውን ልማት ወደ ሀገሪቱ 30 ከተሞች በማስፋት እየተሠራ ነው:: ከተሞቹም ልማቱን ለማካሄድ ቁርጠኝነቱ አላቸው፤ ልማቱ የተወሰነ ካፒታል የሚጠይቅ መሆኑ ከተሞቹ ሁሉንም ሥራ በአንዴ መሥራት ባይችሉም በአቅማቸው ልክ ለመሥራት የተወሰነውን ለመሥራት ጀምረዋል:: ለእዚህም የአዲስ አበባን ተሞክሮ ቀምረዋል::

ልማቱን ከሚያካሂዱት መካከል ሪፖርት እያደረጉ ያሉት 14 ብቻ ናቸው ተብሏልና ይህ ለምን ሆነ? የትደረሳችሁ አይባልም ወይ? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ‹‹ሪፖርት ማድረግ አንድ ነገር ነው፤ መሥራት ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው፤ ሁሉም እየሠሩ ናቸው፤ ሪፖርት የማያደርጉ ሊኖሩ ይችላሉ፤ ሪፖርት እንዲያደርጉ ሄደን መደገፍ ይኖርብናል›› ሲሉ ይናገራሉ:: በሁሉም ከተሞች ሥራው ተጀምሮ እየተካሄደ መሆኑንም ይገልፃሉ::

ልማቱን የሚያካሂዱበት የፋይናንስ ምንጭ የራሳቸው የውስጥ ገቢ መሆኑንም ጠቅሰው፣ መንግሥት የሚደግፍበት ሁኔታም እንዳለም ይናገራሉ:: አንዳንድ ክልሎች ላይ የክልል መንግሥታት እየደገፉ ያለበት ሁኔታም እንዳለ፤ ዋናው ግን በራሳቸው የውስጥ ገቢ፣ ኅብረተሰቡን በማስተባበር የሚሸፉኑት መሆኑን ነው ያስገነዘቡት::

እንደሚኒስትር ዴኤታው ገለፃ፤ የኮሪደር ልማቱ እየሰፋ እንዲሄድ ይደረጋል፤ እኛ 30 ከተሞች እኛ የምንከታተላቸው ሆነው እንጂ ሁሉም ከተሞች ልማቱን መተግበር ጀምረዋል:: የጀመሩ፣ በእቅድ ላይ ያሉ ሲሆን አቅም የሌላቸው የትናንሽ ከተሞች ማዘጋጃ ቤቶች ይህን መሥራት ሊያቅታቸው ይቻላል:: እንደ ችግኝ ተከላ ያሉትን ግን እየሠሩ ናቸው፤ የሀገሪቱ መንግሥት ይህን የኮሪደር ልማት ሥራ ወጪ ሊሸፍን አይችልም፤ ኅብረተሰቡ በየአቅራቢያው ያለውን አካባቢን የማፅዳት ሥራ ቢሠራ በራሱ ትልቅ ነገር ነው::

ከተሞችን ከፕላን ወጪ ያደረጋቸው ችግር ፕላን ያለመኖር ወይስ በፕላን ያለመሥራት ችግር ነው በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄም ‹‹የችግሩ ምንጭ የፕላን ጥሰት መሆኑን ያመለክታሉ:: ሁሉም ከተሞች ፕላን ቢኖራቸውም ትልቁ ችግር የፕላን ጥሰት ነው:: ከተሞች ሲመሠረቱ ቶሎ በፕላን እንዲመሩ ያለማድረግ ሁኔታም ይታያል:: በተለይ በገጠር ማዕከላት አካባቢ ይሄ ችግር በስፋት ይስተዋላል:: በቀጣይ ከተሞች ሲቆረቆሩ በፕላን እንዲመሩ ማድረግ ላይ በትኩረት ይሠራል::

በመድረኩ በሥልጠና ትኩረት የተሰጠባቸውን ዘርፎች የተመለከቱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ከተሳታፊዎች ቀርበው በሚመለከታቸው አመራሮች ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል:: ከከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ አኳያም ባሉ ችግሮች ዙሪያ ሃሳቦች ተንሸራሽሯል:: የከተማ ፕላን የከተማ እድገትና ልማት የሚያፋጥን የልማት እቅድ መሆኑን በመረዳት ኅብረተሰቡንና ባለድርሻ አካላትን በሚገባ በማሳተፍ አቅምን ያገነዘበ የከተማ ፕላን በጥራት እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ማድረግ ያስፈልጋል ተብሏል፤፤

መድረኩ ከተሰጡ አቅጣጫዎች መካከልም የከተሞችን ፕላን ከክልላዊ ልማት ስፓሻል ፕላን ጋር አናቦ መዋቅራዊ ፕላን በማዘጋጀት መተግበር እንደሚገባ፣ የገጠር ቀበሌ ማዕከላትን የቀጣይ ከተሞች መሠረት ስለሚሆኑ ስኬች ፕላን በማዘጋጀት መተግበር ሽፋንን ማሳደግ፣ የከተማ ፕላን መረጃዎችን ተቋማዊ በሆነ መልኩ ተደራጅተው እንዲቀመጡና ለተጠቃሚ ተደራሽ እንዲሆኑ ማስቻል፤ የኮሪደር ልማትን በፕላን እንዲመራ ማድረግና የፕላን ማስፈጸሚያነት መጠቀም የሚሉት ይገኙበታል::

# ስፖርት



# የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ቡድን ተሸለመ

**ብርሃን ፈይሳ**

ፓሪስ በ2024 ባስተናገደችው 17ኛው ፓራሊምፒክ ጨዋታዎች ተሳታፊ የነበረው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሽልማት ተበርክቶለታል። ቡድኑ በፓራሊምፒክ ውድድሩ ሁለት አሯሯጮችን ጨምሮ በስድስት አትሌቶች ተሳትፎ ሁለት የወርቅና አንድ የብር በጥቅሉ ሶስት ሜዳሊያ እንዲሁም ዲፕሎማ በማስመዝገብ አዲስ ታሪክ መስራቱ ይታወሳል።

ይህን አኩሪ ውጤት ያስመዘገበው የፓራሊምፒክ ቡድን አትሌቶችና ተሳትፎ የነበራቸው የቡድኑ አባላት ከወራት በኋላ የማበረታቻ ገንዘብና እውቅና ከትናንት በስቲያ ተረክበዋል።

በዚህም መሰረት ሙሉ ለሙሉ የዓይነ ስውራን የ1ሺ500 ሜትር ውድድር የዓለምና የፓራሊምፒክ አሸናፊዋ አትሌት ያየሽ ጌቴ የዓለምን ክብረወሰን በመስበሯ ጭምር 7 ሚሊዮን ብር እንዲሁም 50 ግራም ወርቅ ተሸልማለች። ሌላኛዋ የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት አትሌት ትዕግስት ገዛኸኝ 7 ሚሊዮን ብር ስትሸለም፣ የብር ሜዳሊያ ያጠለቀው አትሌት ይታያል ስለሺ ደግሞ 4 ሚሊዮን ብር ተበርክቶለታል። ዲፕሎማ ያስመዘገበው አትሌት ገመቹ አመኑ ደግሞ 200 ሺ ብር ተሸልሟል።

የወርቅና የብር ሜዳሊያዎች እንዲሁም ዲፕሎማ እንዲመዘገብ ምክንያት የሆኑት አሰልጣኝ ንጋቱ ኃይለማርያም የ2 ሚሊዮን ብር ተሸላሚ ሆነዋል። በልኡኩ የተለያየ ኃላፊነት የነበራቸው ባለሙያዎችም የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል።

የሽልማት መርሀ ግብሩን ተከትሎ ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትሯ ሸዊት ሻንካ፣



**የዓለም ክብረወሰን በማሻሻል የወርቅ ሜዳሊያ ያጠለቀችው አትሌት ያየሽ ጌቴ የ7 ሚሊዮን ብርና የ50 ግራም ወርቅ ተሸላሚ ሆናለች፤**

‹‹በሀገራችን ከ17 ሚሊዮን በላይ አካል ጉዳተኞች እንዳሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ። አካል ጉዳተኞችን መደገፍ ሀገር የማልማት አንዱ አካል ነው። ዛሬ በትንሽ ድጋፍ ይህንን ውጤት ያመጣችሁ በብዙ ብንደግፍ ደግሞ ሀገራችንን በዓለም አደባባይ ከፍ ታደርጋላችሁ። በመሆኑም በቀጣይ በሰፊው በመደገፍ አብረን እንሰራለን፤ እናንተም በሰፊው ድል አድርጋችሁ ሀገራችሁን እንደምታኮሩ ተስፋዬ ነው›› ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ ወርቀሰሙ ማሞ በበኩላቸው፤ ስፖርት የሰውን አዕምሮ የሚገነባ፣ በመተባበር የሚሰራ፣ ለድል የሚያበቃ ሰውነትና አዕምሮ የሚያዳብር ትልቅ ዘርፍ መሆኑን ገልጸው፤ ‹‹አካል ጉዳተኛ የሚለው ቃል ስለሚባል ብቻ እንለዋለን እንጂ ልበ ሙሉዎች ናቸው። በስፖርት ዘርፍ የሀገራችሁን ሰንደቅ ዓላማ በዓለም አደባባይ ከፍ ስላደረጋችሁ ክብር ይገባችኋል። ይህንን ሽልማት ያዘጋጀውና ከአካል ጉዳተኞች ጋር በስፋት የሚሰራውን የባህልና ስፖርት ሚኒስቴርም አመሰግናለሁ›› በማለት ተናግረዋል።

አትሌቶች በቂ ስልጠና ወስደው እንዲወዳደሩ ለማድረግ ባለው አቅም ከፍተኛ ጥረት መደረጉን የጠቆሙት የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ዶክተር ጊዮን አሰፋ፤ አትሌቶቹ በፓሪሱ የፓራሊምፒክ ውድድር ውጤታማ የሆኑት በተገቢው ልክ ድጋፍ አግኝተው ሳይሆን በተለያዩ ውድድሮች ተሳትፎ ባዳበሩት ምርጥ አቅማቸው መሆኑን መስክረዋል። ስፖርቱን በበላይነት የሚመራው የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ላደረገው መጠነ ሰፊ ድጋፍም ምስጋና እንደሚገባው ገልጸዋል።

በፓራ አትሌቲክስ ስፖርት በ1ሺ500 ሜትር ሙሉ በሙሉ የዓይነ ስውራን ውድድር አትሌት ያየሽ ጌቴ 4፡27.68 በሆነ ሰዓት የዓለም ክብረወሰን በመስበር አሸናፊ መሆኗ ይታወሳል። በኢትዮጵያ የፓራሊምፒክ ተሳትፎ ታሪክ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ በቶኪዮ 2020 ፓራሊምፒክ ላይ ያስመዘገበችው አትሌት ትዕግስት ገዛኸኝ ደግሞ ፓሪስ ላይም ሁለተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ በ1ሺ500 ሜትር ጭላንጭል መድገም ችላለች። በተመሳሳይ ርቀት በወንዶች ጭላንጭልም አትሌት ይታያል ስለሺ የብር ሜዳሊያ አስመዝግቧል። በዚህም ውጤት መሰረት ኢትዮጵያ በፓሪስ ፓራሊምፒክ ከዓለም 44ኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠች ሲሆን፤ በአፍሪካ ደግሞ ከአልጄሪያ፣ ቱኒዚያ፣ ሞሮኮ፣ ናይጄሪያ እና ግብጽ በመቀጠል ስድስተኛ ሆና ማጠናቀቋ አይዘነጋም።


# ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ

ቢ ስኳር ዋይ ኢንጅነሪንግ ከዚህ በታች ባሉት ክፍት የስራ መደቦች ላይ መስፈርቱን የሚያሟሉ አመልካቾችን አወዳድሮ በቋሚነት መቅጠር ይፈልጋል።

| የሥራ መደቡ መጠሪያ | ተፈላጊ የት/ደረጃ | ተፈላጊ የሥራ ልምድ በሙያው | ብዛት | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|
| ኮንስትራክሽን መሀንዲስ | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ቢ.ኤስ.ሲ ዲግሪ በሲቪል ኢንጅነሪንግ የተመረቀ/ች | በተመሳሳይ ሙያ 7 ዓመትና ከዛ በላይ የስራ ልምድ ያለው/ያላት | 2 | ለፕሮጀክት |
| ሳይት መሀንዲስ | ከታወቀ ዩኒቨርስቲ ቢ.ኤስ.ሲ ዲግሪ በሲቪል ኢንጅነሪንግ የተመረቀ/ች | በተመሳሳይ ሙያ 3 ዓመትና ከዛ በላይ የስራ ልምድ ያለው/ያላት | 2 | ለፕሮጀክት |
| ኦፊስ መሀንዲስ | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ቢ.ኤስ.ሲ ዲግሪ በሲቪል ኢንጅነሪንግ የተመረቀ/ች | በተመሳሳይ ሙያ 2 ዓመትና ከዛ በላይ የስራ ልምድ ያለው/ያላት | 3 | ዋና መስሪያ ቤት |
| ጀንራል ፎርማን | አድቫንስድ ዲፕሎማ ወይም ዲፕሎማ በኮንስትራክሽን የተመረቀች | በተመሳሳይ ሙያ 6 ዓመትና ከዛ በላይ አድቫንስድ ዲፕሎማ/ 8 ዓመትና ከዛ በላይ ዲፕሎማ የስራ ልምድ ያለው ያላት | 3 | ለፕሮጀክት |
| አስተዳደር እና ፋይናንስ | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በማኔጅመንት፣ ኢኮኖሚክስ ወይም በአካውንቲንግ በዲግሪ ወይም ዲፕሎማ የተመረቀች | በተመሳሳይ ሙያ 2 ዓመት እና ከዛ በላይ ዲግሪ 4 ዓመትና ከዛ በላይ ዲፕሎማ ያለው/ያላት | 2 | ዋና መስሪያ ቤት እና ለፕሮጀክት |
| የቢሮ ፀሀፊ (Secratery) | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በሴክሪተሪ በዲግሪ ወይም ዲፕሎማ የተመረቀ/ች | በተመሳሳይ ሙያ 2 ዓመት እና ከዛ በላይ ዲግሪ/ 4 ዓመትና ከዛ በላይ ዲፕሎማ ያለው/ያላት | 2 | ዋና መስሪያ ቤት |
| የተሽከርካሪ ተቆጣጣሪ | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በአውቶመካኒክ በዲግሪ ወይም ዲፕሎማ የተመረቀ/ች | በተመሳሳይ ሙያ 3 ዓመት እና ከዛ በላይ ዲግሪ 5 ዓመትና ከዛ በላይ ዲፕሎማ ያለው/ያላት | 2 | ዋና መስሪያ ቤት |
| ውል አስተዳደር (Contract dominstration) | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ቢ.ኤስሲ ዲግሪ በሲቪል ኢንጅነሪንግ የተመረቀ/ች | በተመሳሳይ ሙያ 8 ዓመትና ከዛ በላይ የስራ ልምድ ያለው/ያላት | 1 | ዋና |
| የኮንስትራክሽን ጨረታ አዘጋጅ( Bid preparation) | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ቢ.ኤስሲ ዲግሪ በሲቪል ኢንጅነሪንግ የተመረቀ/ች | በተመሳሳይ ሙያ 6 ዓመትና ከዛ በላይ የስራ ልምድ ያለው/ያላት | 2 | መስሪያ ቤት |

**ማሳሰቢያ:-**

ደመወዝ: በስምምንት

ሀ. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃችሁን ዋናውን እና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ የሰው ሀይል አስተዳደር በመቅረብ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን።

ለ. አመልካቾች ለመወዳደር የምትፈልጉበትን የሥራ መደብ በመግለፅ በማመልከቻ ማያያዝ ይኖርባችኋል።

ሐ. አድራሻ ገርጂ መብራትኃይል አንበሳ ጋራዥ አለፍ ብሎ አሃዱ ኮምፐሌክስ ፊት ለፊት

**ስልክ ቁጥር:- 0937-027994/09-01-97-10-42/09-46-63-42-68**

**ቢ ስኳር ዋይ ኢንጅነሪንግ**